# የገቢዎች ሚኒስቴር








## የ2015 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ሪፖርት






ሀምሌ 2015 ዓ.ም. 　　　　　　　　　　　　　　　　 አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

1 መግቢያ ........ 1

ክፍል ሁለት ........ 3

2 የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም አፈጻጸሞች ........ 3

2.1 የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ስራዎች አፈጻጸም ........ 3

2.2 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል አፈጻጸም ........ 4

2.3 የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም ........ 10

2.4 የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም ........ 15

2.5 ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረግ ድጋፍና ክትትል ማሻሻል አፈጻጸም ........ 19

2.6 የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ክትትል ሥራዎች ማሻሻል አፈጻጸም ........ 23

2.7 የሴቶችና ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሻሻል አፈጻጸም ........ 24

2.8 የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ማሻሻል አፈጻጸም ........ 26

ክፍል ሦስት ........ 28

3 በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIS) ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና ........ 28

3.1 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ስርዓትን የማጎልበት ስራዎች አፈጻጸም ........ 28

3.1.1 የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልዕቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም ........ 28

3.1.2 የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን የማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም ........ 33

3.1.3 የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም ........ 37

3.1.4 የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም ........ 39

3.2 የግብር ከፋዮች የታክስ ህግ ተገዥነት ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም ........ 44

3.2.1 የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብ ማጠናከር ስራዎች አፈጻጸም ........ 44

3.2.2 የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ስራዎችን ማጠናከር ስራዎች አፈጻጸም ........ 55

3.3 ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት የማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም ........ 62

3.3.1 ከሀገር ውስጥ ታክስ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ ስራዎች አፈጻጸም ........ 62

3.3.2 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አቅም ማጎልበት ስራዎች አፈጻጸም ........ 68

3.4 የገቢዎች ሚኒስቴር የ2015 በጀት ዓመት የግቦች አፈጻጸም ........ 69

ክፍል አራት ........ 74

4. በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 74

4.1 በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ........ 74

4.1 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 74

ክፍል አምስት ........ 75

5 ማጠቃለያ ........ 75

# ሰንጠረዦች

ሰንጠረዥ 1 የሰው ሀብት ሁኔታ ..... 6
ሰንጠረዥ 2 የተሰጡ ስልጠናዎች በስልጠና ዓይነትና በኃላፊነት ደረጃ ..... 6
ሰንጠረዥ 3 የ2015 የበጀት አጠቃቀም በወጪ ሂሣብ መደቦች ..... 10
ሰንጠረዥ 4 የኋላ ዘመናት የፌዴራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም በዝርዝር ..... 11
ሰንጠረዥ 5 የ2014 የፌዴራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም ..... 12
ሰንጠረዥ 6 የኮሙኒኬሽን ስራዎች አፈጻጸም ..... 18
ሰንጠረዥ 7 በ2015 በጀት ዓመት ስልጠና የወሰዱ የክልሎች /ከተማ አስተዳደሮች ..... 19
ሰንጠረዥ 8 የውጭ ምንዛሬ ተፈቅዶ ማሽን ማስመጣት የጀመሩ አቅራቢዎች ..... 34
ሰንጠረዥ 9 ከሽመመ ቁጥጥር የተጣለና የተሰበሰበ መቀጫ ..... 35
ሰንጠረዥ 10 የመረጃ ማጥራት ስራዎች አፈጻጸም ..... 37
ሰንጠረዥ 11 የኢ-ፋይሊንግ ስልጠና እና የይለፍ ቃል አፈጻጸም ..... 37
ሰንጠረዥ 12 የኢ-ፋይሊንግ አፈጻጸም ..... 38
ሰንጠረዥ 13 የኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-PAYMENT) የእስከ አሁን አፈጻጸም ..... 38
ሰንጠረዥ 14 የቴሌብር ኤሌክትሮኒክ ክፍያ(E-PAYMENT) አፈጻጸም ..... 39
ሰንጠረዥ 15 የግብር ከፋዮች ምዝገባ አፈጻጸም ..... 40
ሰንጠረዥ 16 የአገልግሎት ኦዲት አፈጻጸም በማህደር ..... 41
ሰንጠረዥ 17 የተጠቃለለ የተመላሽ አፈጻጸም ..... 42
ሰንጠረዥ 18 የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት አፈጻጸም ..... 42
ሰንጠረዥ 19 በ2015 በጀት ዓመት ዉሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ..... 43
ሰንጠረዥ 20 በ2015 በጀት ዓመት በታክስ ኦዲት ተስተካክለዉ የተመለሱ ፋይሎች ..... 43
ሰንጠረዥ 21 የክስና ጉምሩክ መረጃ፣ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም ..... 44
ሰንጠረዥ 22 የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቅ አፈጻጸም ..... 45
ሰንጠረዥ 23 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም ..... 46
ሰንጠረዥ 24 የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ አሰጣጥ ..... 47
ሰንጠረዥ 25 የኤክሳይዝ ታክስ ለፈቃድ አሰጣጥ ወይም ለክትትል የተካሄደ መስክ ስራ ..... 48
ሰንጠረዥ 26 የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም ..... 49
ሰንጠረዥ 27 የተርንኦቨር ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም ..... 50
ሰንጠረዥ 28 የ2015 በጀት ዓመት አጠቃላይ የስሌት ስራዎች አፈጻጸም እና በልዩነት የተገኘ የገንዘብ መጠን ..... 51
ሰንጠረዥ 29 ዘግይተው በቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ላይ የተሰራ ስሌት እና የተወሰነ ገቢ ..... 52
ሰንጠረዥ 30 በማሳወቂያ ጊዜ ኢ-ፋይል አድርገው ክፍያ ያልከፈሉት ላይ የተሰራ ስሌት ..... 52
ሰንጠረዥ 31 ሌሎች በዴስክ የተሰራ የታክስ ስሌት ..... 53
ሰንጠረዥ 32 መረጃ ወደ ሲስተም መመዝገብ (DATA CAPTURING) እና የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ..... 53
ሰንጠረዥ 33 አጠቃላይ የግብር ከፋዮች ብዛት ለስጋት ዝግጁ የሆኑና ያልሆኑ እንዲሁም የስጋት ደረጃቸው ..... 56
ሰንጠረዥ 34 የኦዲት አፈጻጸም በማህደር ..... 58
ሰንጠረዥ 35 የኦዲት አፈጻጸም በገንዘብ(በፍሬግብር) ..... 59
ሰንጠረዥ 36 የኦዲት ውጤት በኦዲት ዓይነት፣ የቀነሰ ኪሳራ እና የቀነሰ ተመላሽ ..... 59
ሰንጠረዥ 37 በግብይት ወቅት ደረሰኝ የማይቆርጡ ድርጅቶች ላይ የተወሰደ እርምጃ በቅ/ጽ/ቤት ..... 60
ሰንጠረዥ 38 የኢንተለጀንስ ጥናት ተደርጎባቸው ኦዲት እንዲደረጉ ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት የተላለፉ ድርጅቶች ..... 61
ሰንጠረዥ 39. የኢንቨስትጌሽን ኦዲት ሥራዎች አፈጻጸም ..... 61
ሰንጠረዥ 40 አጠቃላይ የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸም ..... 62
ሰንጠረዥ 41 የሀገር ውስጥ ታክስ የገቢ አፈጻጸም በቅ/ጽ/ቤቶች ..... 63
ሰንጠረዥ 42 የሀገር ውስጥ ታክስ ገቢ አፈጻጸም በታክስ ዓይነት ..... 63
ሰንጠረዥ 43 የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ገቢ አፈጻጸም በቅ/ጽ/ቤቶች ..... 64
ሰንጠረዥ 44 የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ገቢ አፈጻጸም በታክስ ዓይነት ..... 64
ሰንጠረዥ 45 ለክልሎች የተላለፈ የጋራ ገቢ ..... 65
ሰንጠረዥ 46 የጋራ ገቢ ትልልፍ በንጽጽር ..... 65

ሰንጠረዥ 47 የውክልና/ዊዝሆልዲንግ/ ታክሶች ገቢ ትልልፍ ....66
ሰንጠረዥ 48 የዊዝሆልዲንግ ታክሶች ንጽጽር ....66
ሰንጠረዥ 49 አጠቃላይ የጋራ ገቢና የዊዝሆልዲንግ ታክሶች ጥቅል ትልልፍ ....67
ሰንጠረዥ 50 የጋራ ገቢ ታክሶች ጥቅል ትልልፍ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃጸር ....67
ሰንጠረዥ 51 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አፈጻጸም ....68
ሰንጠረዥ 52 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ በወሰነው ክፍል ....68
ሰንጠረዥ 53 ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች ....69

# ክፍል አንድ

## 1 መግቢያ

የገቢዎች ሚኒስቴር የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸምን ለማሻሻል ህገወጥ ንግድን በመቆጣጠር በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችሉ ከ10 እና ከ5 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የተመነዘረ የ2015 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ በማቀድ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማሻሻል፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት፣ የግብር ከፋዮችን የታክስ ሕግ ተገዥነት ማሻሻል እና ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ የሚሉ ስትራቴጂክ ግቦችንና ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራትን በማስቀመጥ እንዲሁም ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን በመቅረጽ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት ጉልህ ድርሻ የሚኖራቸው ታክስ በፈቃደኝነት መክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት፣ የታክስ አስተዳደር ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣ የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር እና የዳበረ የስራ ባህል መፍጠር የሚሉትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ተከትሎ መተግበር በመቻሉ ባለፉት አስራ ሁለት ወራት አፈጻጸሙ ከተቀመጡት ግቦች አኳያ ሲመዘን በሁሉም የገቢ ፊሲካል ስራዎቻችን አመርቂ ውጤት የተመዘገበ መሆኑን የአፈጻጸም ሪፖርቱ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የተመዘገበው ውጤት ከተቋሙ ዋነኛ ተልዕኮ ከሆነው የገቢ አሰባበሰብ አኳያ ሲታይ በ2015 በጀት ዓመት ባለፉት አስራ ሁለት ወራት በሀገር ውስጥ ታክስ ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ብር 266.95 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 264.35 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 99.02 በመቶ ሲሳካ ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ብር 183.34 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 177.68 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 96.9 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ ስለሆነም እንደ ተቋም በአስራ ሁለት ወራት ብር 450.29 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 442.03 ቢሊዮን በመሰብሰብ የዕቅዱን 98.16 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከአምና ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ105.32 ቢሊዮን ብር ወይም በ31.28 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

በመጨረሻም ሪፖርቱ የስራ ዘርፎችን፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን እና በስራቸው ያሉትን የታክስ ማዕከላትን በመረጃ ምንጭነት በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን መረጃዎቹም ገላጭ በሆነ መልኩ በሰንጠረዥ እና በመሳሰሉት ተተንትነው ግልጽ በሆነ መልኩ የቀረቡ ሲሆን የሪፖርቱም አደረጃጀት በተመለከተ በክፍል አንድ መግቢያ፣ በክፍል ሁለት የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሃብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎች፣ በክፍል ሶስት በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና በክፍል አራት

በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ሲያካትት የመጨረሻው ክፍል የሪፖርቱን ማጠቃለያ እንዲይዝ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2 የተቋማዊ የማስፈጸም አቅም አፈጻጸሞች

### 2.1 የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ስራዎች አፈጻጸም

**ከዕቅድ ዝግጅት አኳያ** ተቋሙ የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ መነሻ በማድረግ የአንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት መርህን በመከተል ለ2015 በጀት ዓመት የተጣለውን ወደ መንግስት ትሬዡሪ ብር 408,272,964,480.00 ፈሰስ ለማድረግ የሚሰራ ቢሆንም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚሰበሰበው ጥቅል ገቢ ላይ ለክልል የሚተላለፈዉን የጋራ ገቢ እና ሌሎች ተቀናናሽ ሂሳቦችን ታሳቢ በማድረግ ወደ መንግስት ትሬዡሪ ፈሰስ ወደ ሚደረገዉ የተጣራ የገቢ መጠን ላይ ለመድረስ ጥቅል እቅድ ብር 450,292,248,448.14 በማድረግ ይህን የገቢ ዕቅድ በገቢ ርዕሶች በመተንተን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ መግባት ተችሏል:: በዕቅድ ዝግጅቱም ከዋናው መ/ቤት እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ ያሉትን አመራሮችን እና ባለሙያዎችን በማወያየት፣ በዕቅድ ዝግጅቱ ዙሪያ የጋራ መግባባት በመፍጠር እና ዕቅዱን እስከ ፈጻሚ ድረስ በማውረድ ወደ ስራ ተገብቷል::

ከቅርንጫፍ እስከ ዋናዉ መስሪያ ቤት ያሉት አመራረች በ2015 በጀት ዓመት ሊሰሩ በታሰቡ ስራዎች ዙሪያ ግንዛቤ ኖሯቸው ዕቅዱን በባለቤትነት ወስደው እንዲተገብሩት ከማድረግ አንፃር የ2014 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ተደርጓል:: በ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ዙሪያ ተጠሪ ተቋማትን ጨምሮ የዋናው መ/ቤት ዘርፎች እና ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም የቅ/ጽ/ቤቶች አመራሮች የተሳተፉበት ውይይቶች ተደርገዋል:: በዋናው መ/ቤት የስራ ዘርፎችና ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያለፈውን በጀት ዓመት የአፈፃፀም ግብረ መልስ በማቅረብ መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይት ተደርጓል::

**ከሰዉ ኃይልና ዝግጅት አኳያ** ተቋሙ ያስቀመጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች ወሳኝ ሚና ያላቸዉ መሆኑን በመገንዘብ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ 120 በደረጃ ዕድገት እና 133 በቅጥር የስራ መደቦችን በመሙላት የሰው ኃይል ቁጥሩን 4616 በማድረስ የመዋቅሩን 73.43 በመቶ በመሸፈን የበጀት ዓመቱ ተጀምሯል:: የአመራር እና የፈጻሚውን አቅም ለመገንባት የሚያግዙ ስልጠናዎች ለ3453 ሰራተኞች በ2014 በጀት ዓመት የተሰጡ ሲሆን እነኝህ ስልጠናዎች ለ2015 በጀት ዓመት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳላቸው ታሳቢ ተደርጓል::

**ከግብዓት ዝግጅት አኳያ** በሀገር ዉስጥ ታክስ በ2015 በጀት ዓመት ለሥራ ማስኬጃ እና ደመወዝ በጀት ብር 2,021,290,810.00 እና ለካፒታል በጀት ብር 700,000,000.00 በአጠቃላይ ብር 2,721,290,810.00 በማስፈቀድ ወደ ስራ ተገብቷል::

**ባለድርሻ አካላትንና ግብር ከፋዩን ከማዘጋጀት አኳያ** ግብር ከፋዩንና ባለድርሻ አካላትን በዕቅድ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሁም በህግ ተገዥነት ደረጃቸዉ የተሻለ አስተዋጽዎ የነበራቸዉን 724 (400 በአገር አቀፍ እና 324 በቅርንጫፍ) ግብር ከፋዮች እና አስመጪዎች የዕዉቅናና የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷል። እንዲሁም 14 ግብር ከፋዮችና በ3 ጊዜና ከዚያ በላይ በተከታታይ በመሸለማቸው የልዩ ተሸላሚ ሲሆን አንደ(1) ግብር ከፋይ ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በማጋለጥ ተሸላሚ ሆነዋል።

ተቋሙ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ውስጣዊ አቅሙን በማጠናከርና ለአሰራር ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት የማሻሻያ ስራዎችን በመስራት፣ ከአጋር አካላት ጋር ማለትም ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከተቆጣጣሪ እና ተባባሪ አካላት ጋር የተጠናከረ የስራ ግንኙነት በመፍጠር በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ የታክስ ስርዓት ለመገንባት እየሰራ ቆይቷል።

ለግብር ከፋዩ ቀላልና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስራ በመስራት የግብር ከፋዩን ማህበረሰብ የእርካታ ደረጃ ከፍ ማድረግ አንዱ ሲሆን በዚህ ረገድ የታክስ ስርዓቱን በኤሌክትሮኒክ ስርዓት የታገዘ ማድረግ፣ የህግ ማዕቀፎችን የመፈተሽና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እና የታክስ ህግ ማስከበር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት የዕርምት ስራ በመስራት በቀጣይም ግብር ከፋዩ በታማኝነት የቀረጥና ታክስ ግዴታውን አሳውቆ እንዲከፍል መደላድሎች ተፈጥረዋል።

## 2.2 የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል አፈጻጸም

### ➲ የሰው ሃብት አስተዳደር ስራዎች

ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪትን መሰረት በማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያስቀመጠውን የሰው ኃይል መሳብ፣ ማቆየትና የመፈጸም ብቃትን ማሳደግ ግብ ለማሳካት በ2015 በጀት ዓመት በተለያዩ የሥራ መደቦች ላይ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች በማወዳደር በቅጥር ለመሙላት ታቅዶ 492 (ወንድ 241 ሴት 251) ቅጥር በመፈጸም የሰው ሀይል ቁጥሩን 4,794 (ወንድ 2,145 ሴት 2,649) ወይም በሽፋን ደረጃ 74 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የሰራተኞችን ብቃት ከማሳደግ አንጻር በተቋም ደረጃ ለ2015 በጀት ዓመት ወደ ሲቪል ሰርቪስ ዩንቨርስቲ በሁለተኛ ዲግሪ እና ለመጀመሪያ ዲግሪ 94፣ 2 ሰራተኞች ብሄራዊ መረጃና ደህንነት ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፣ 5 ሰራተኞች ቻይና እና 6 ሲቪል ሰርቪስ ዩንቨርሰቲ በዶክትሬት ዲግሪ በድምሩ107 ሰራተኞች ውድድሩን አልፈው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል።

በተጨማሪም 11 ሰራተኞች ጌጅ ኮሌጅ፤ ትምህርታቸውን እንዲማሩ የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል።

ለስራ አስፈላጊነት ሲባል ለ 237 (ወ 125 ሴ 112) ሠራተኞች የውስጥ ዝውውር ተሰጥቷል። እንዲሁም በመደበኛ ዝውውወር 24፣ በማህበራዊ ችግር ምክንያት 13 በቀረበ የዝውውር ጥያቄ መሰረት 37 (ወ 24 ሴ 13) ዝውውር ተሰጥቷል።

በተለያየ ምክንያት በሰራተኞች ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ከመስጠት አንጻር ከደረጃ እድገት የስራ ልምድ አያያዝ እና ከአስተዳዳራዊ በደል ጋር ተያይዞ ቅሬታ ላቀረቡ 159 ሠራተኞች (ወንድ 81 እና ሴት 78) ሙሉ በሙሉ ምላሽ ተሰጥቷል።

በሌላ በኩል ከተቋሙ 252 (ወንድ 155 ሴት 97) ሰራተኞች የለቀቁ ሲሆን በጡረታ 26 (ወንድ 15 ሴት 8) ፣ በሞት 5 ሴት፣ በዲሲፒሊን 1 (ወንድ 1) ፣ በገዛ ፈቃድ 214 (ወንድ 129 እና ሴት 85) ፣ ወደ ጉምሩክ የተዘዋወሩ ወንድ 2፣ ወደ ፕሮጀክት የገቡ ወንድ 2፣ በአንቀጽ 41 ወንድ 1፣ በሀሰተኛ ትምህርት ማስረጃ ሴት 1 የተሰናበቱ ሲሆን ምክንያታቸው 109 የተሻለ ደመወዝ፣ 9 የግል ስራ በመመሪያ ላይ ባለ ቅሬታ 3(የውስጥ ኦዲት) 2(ንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት) 91 ምክንያታቸውን መግለጽ ያልፈለጉ ሲሆን የተሸላ ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም አግኝተው እንደሆነ ይገመታል።

በተለያየ ደረጃ ብቃት ያላቸውን 493 (ወ 210 ሴ 283) ሰራተኞች በማወዳደር ለሰራተኞች የደረጃ ዕድገት ተሰጥቷል። ለመካከለኛ ቁጥር 2 ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት የ219 ሰራተኞች (ወንድ-90፣ ሴት-129) ከዚህ ውስጥ 4ቱ (ወንድ 0፣ ሴት 4) አመራሮች እና ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን በማስተርስ ጨርሰው ለመጡ የ2014 በጀት ዓመት 17 ተመራቂ ሠራተኞች (ወንድ 9፣ ሴት 8) ምደባ የተከናወነ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ በድምሩ የ253 (ወንድ 114፣ ሴት 139) ሠራተኞች ምደባ የተሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 239 አመራሮችና ሰራተኞች በአዲሱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተመደቡ ናቸው።

ከሰው ሃብት ስራ አመራር አኳያ ተሻሽለው የጸደቁ አሰራሮች በሚመለከት የኤች አይቪ፣ ኤድስ አስተዳደር እና የሽልማት አፈጻጸም መመሪያ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቷል። የሠራተኞች የደመወዝ ዕርከን ጭማሪ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 182/2015 ተዘጋጅቶና ጸድቆ ተግባራዊ ተደርጓል እንዲሁም የደንብ ልብስ እና የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 178/2015 ላይ የቀረበውን የማሻሻያ ጥያቄዎች የማስተካከያ ሰርኩላር ተዘጋጅቶ ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። የጸደቀ ሰርኩላርን በተመለከተ የትርፍ ሰዓት ክፍያ አስመልክቶ ከተቋማችን የሥራ ባህሪ አኳያ ተዘጋጅቶ በበላይ አመራር ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ተደርጓል። የሰው ሀብት አገልግሎች ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ለቅ/ጽ/ቤቶች ተሰራጭቷል። እንዲሁም በተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ቁጥር 173/2014 የተዘጋጀው ሰርኩላር የህግ ቅርፅ ይዞ በመጽደቅ ሂደት ላይ ይገኛል።

ሰንጠረዥ 1 የሰው ሀብት ሁኔታ

| ተ. ቁ | የሥራ ቦታ | ለተቋሙ/ለሥራ ክፍሉ የተፈቀደ የሥራ መደብ | የተሞሉ የሥራ መደቦች | | ድምር | የመዋቅር ሽፋን | በፐርሰንት (%) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወ | ሴ | | | ወንድ | ሴት |
| 1 | ዋና መ/ቤት | 1430 | 396 | 440 | 836 | 58.46 | 47 | 53 |
| 2 | ከፍተኛ | 477 | 153 | 210 | 363 | 76.1 | 42 | 58 |
| 3 | ምዕራብ | 583 | 187 | 288 | 475 | 81.48 | 39 | 61 |
| 4 | ምስራቅ | 575 | 167 | 328 | 495 | 86.09 | 34 | 66 |
| 5 | መካከለኛ | 532 | 199 | 249 | 448 | 84.21 | 44 | 56 |
| 6 | ሰሜን ምዕራብ | 580 | 160 | 225 | 385 | 66.38 | 42 | 58 |
| 7 | አዳማ | 315 | 133 | 130 | 263 | 83.49 | 51 | 49 |
| 8 | ባህርዳር | 361 | 143 | 176 | 319 | 88.37 | 45 | 55 |
| 9 | መቀሌ | 334 | 84 | 136 | 220 | 65.87 | 38 | 62 |
| 10 | ድሬዳዋ | 259 | 89 | 114 | 203 | 78.38 | 44 | 56 |
| 11 | ሐዋሣ | 405 | 168 | 130 | 298 | 73.58 | 56 | 44 |
| 12 | ጅማ | 326 | 153 | 103 | 256 | 78.53 | 60 | 40 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 301 | 109 | 118 | 227 | 75.42 | 48 | 52 |
| 14 | በት/ት ላይ ያሉ መደባቸው የተያዘ | | 4 | 2 | 6 | | | |
| **ድምር** | | **6478** | **2145** | **2649** | **4794** | **74.00** | **44.7** | **55.3** |

## የስልጠና ስራዎች አፈጻጸም

የተቋሙን የመፈጸም አቅም ለማጎልበት በበጀት ዓመቱ በ105 የስልጠና ርዕሶች ለ6,974 የአገር ውስጥ ታክስ አስተዳደር፣ የጉምሩክ አስተዳደር እና የክልል የታክስ አስተዳደር አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ሰንጠረዥ 2 የተሰጡ ስልጠናዎች በስልጠና ዓይነትና በኃላፊነት ደረጃ

| ተ.ቁ. | የስራ ዘርፎች | ዕቅድ | ክንውን | | | | | | | | | አፈጻጸም (%) | የተሠጡ ስልጠና ርዕሶች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አመራር | | | ባለሙያ | | | ድምር | | | | |
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 1 | የአገር ውስጥ ታክስ አስተዳደር | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | ታክስ አስተዳደር | 1606 | 179 | 134 | **313** | 785 | 576 | **1361** | 964 | 710 | **1674** | **104** | 30 |
| 1.2 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 758 | 282 | 146 | **428** | 372 | 474 | **846** | 654 | 620 | **1274** | **168** | 39 |
| | ድምር 1 | **2364** | 461 | 280 | **741** | 1157 | 1050 | **2207** | 1618 | 1330 | **2948** | **125** | 69 |
| 2 | የጉምሩክ አስተዳደር | | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | ጉምሩክ አስተዳደር | 1640 | 177 | 28 | **205** | 906 | 481 | **1387** | 1083 | 509 | **1592** | **97** | 20 |
| 2.2 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 1008 | 202 | 114 | **316** | 383 | 395 | **778** | 585 | 509 | **1094** | **109** | 31 |
| | ድምር 2 | **2648** | **379** | **142** | **521** | **1289** | **876** | **2165** | **1668** | **1018** | **2686** | **101** | **51** |

| ተ.ቁ. | የስራ ዘርፎች | ዕቅድ | ክንውን | | | | | | | | | አፈጻጸም (%) | የተሠጡ ስልጠና ርዕሶች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አመራር | | | ባለሙያ | | | ድምር | | | | |
| | | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | |
| 3 | ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች | | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | ታክስ አስተዳደር | 988 | 233 | 71 | **304** | 676 | 360 | **1036** | 909 | 431 | **1340** | **136** | 22 |
| 3.2 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 0 | | | **0** | | | **0** | 0 | 0 | **0** | **0** | |
| | ድምር 3 | **988** | **233** | **71** | **304** | **676** | **360** | **1036** | **909** | **431** | **1340** | **136** | |
| 4 | አጠቃላይ ድምር (1+2+3) | | | | | | | | | | | | |
| 4.1 | ታክስ አስተዳደር | 2594 | 412 | 205 | **617** | 1461 | 936 | **2397** | 1873 | 1141 | **3014** | **116** | **39** |
| 4.2 | ጉምሩክ አስተዳደር | 1640 | 177 | 28 | **205** | 906 | 481 | **1387** | 1083 | 509 | **1592** | **97** | **20** |
| 4.3 | ድጋፍ ሰጪና መረጃ ቴክኖሎጂ | 1766 | 484 | 260 | **744** | 755 | 869 | **1624** | 1239 | 1129 | **2368** | **134** | **46** |
| | ድምር | **6000** | **1073** | **493** | **1566** | **3122** | **2286** | **5408** | **4195** | **2779** | **6974** | **116** | **105** |

በገቢዎች ሚኒስቴር በሀገር ውስጥ ታክስ በሰላሳ የስልጠና ርዕሶች 1674 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከእነዚህ ሰልጣኞች ውስጥ 321 (19 በመቶ) ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 1353 (81 በመቶ) ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው፡፡ በድጋፍ ሰጪ ስራዎችና በመረጃ ቴክኖሎጂ በሰላሳ ዘጠኝ የስልጠና ርዕሶች ለ1274 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ሰልጣኞች 424 (33 በመቶ) የሚሆኑት ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 850 (67 በመቶ) ሰልጣኞች ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው፡፡ በድምሩ በሥድሳ ዘጠኝ የስልጠና ርዕሶች ለ2948 የሚ/ር መ/ቤቱ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በጉምሩክ አስተዳደር በሃያ የስልጠና ርዕሶች ለ1592 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውስጥም 103 (7 በመቶ) የሚሆኑት ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 1489 (93 በመቶ) ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው፡፡ በድጋፍ ሰጪ ስራዎችና በመረጃ ቴክኖሎጂ በሰላሳ አንድ የስልጠና ርዕሶች ለ1094 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ሰልጣኞች 246 (23 በመቶ) የሚሆኑት ከዋናው መ/ቤት ሲሆኑ ቀሪዎቹ 848 (77 በመቶ) ከቅ/ጽ/ቤቶች የተሳተፉ ናቸው፡፡ በድምሩ በሃምሳ አንድ የስልጠና ርዕሶች ለ2686 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሃያ ሁለት የስልጠና ርዕሶች ለ1340 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥተዋል፡፡

የተሰጡ የስልጠና ዓይነቶችን ለማሳየት ያህል ያላስታወቁ ታክስ ከፋዮች መረጃ መመዝገቢያ መከታተያ ሪፖርት ፣ Dispute Resolution and Related with MNC፣ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች (IFRS) ፣ የ3ኛ ወገን መረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ፣ የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) ፣ መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ (Basic Accounting) ፣ የታክስ ህጎች፣ የገቢ ሂሳብና ትልልፍ፣ ታክስ ስሌት (አወሳሰን) እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በማዕከሉ በሚሰጡ ስልጠናዎች ሴቶችና ወጣቶች የተሳትፎ ድርሻን ቢያንስ 40 ከመቶ ለማድረስ ታቅዶ፣ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ስልጠና ከተሠጣቸው 6974 አመራሮችና ባለሙያዎች መካከል 2779 ሴት አመራሮችና ባለሙያዎች ሲሆኑ፤ የተሳትፎ ድርሻቸውም 40 በመቶ ይሆናል። ከአመራሮች አኳያ ስልጠና ከተካፈሉ 1566 አመራሮች መካከል 493ቱ ሰልጣኞች ሴት አመራሮች ናቸው። የአፈጻጸም ድርሻቸው ደግሞ 32 በመቶ ይዟል።
ለአዲስ ቅጥር ተወዳደሪዎች ፈተና ከመስጠት አኳያ በአስራ አንድ ዳይሬክቶሬቶች እና አንድ ቅ/ጽ/ቤት (ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ሰው ሃብት ሥራ አመራር፣ ንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት፣ ህግ አገልግሎት፣ ለኮሙኒኬሽን ጉዳዮች፣ ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ ስጋትና ህግ ተገዥነት ስትራቴጂ፣ ለውስጥ ኦዲት፣ ታክስ መረጃና ሽ/መ/መ አስተዳደር እና ለመካከለኛ ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት ስር በሚገኙ ሃያ አራት የስራ መደቦች ቅጥር ላይ ለመወዳደር ለፈተና ለቀረቡ 379 ተወዳዳሪዎች ፈተና ተሰጥቶ ውጤቱ ለሰው ሃብት ሥራ አመራር ዳ/ሬት ተገልጾለታል።
ለደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪዎች ፈተና ከመስጠት አንጻር የደረጃ ዕድገት ተወዳዳሪዎችን ብቃት ለመመዘን ፈተና እንዲሰጥ ጥያቄ ለቀረበላቸው 76 የስራ መደቦች ለፈተናው ለቀረቡ 314 ተወዳዳሪዎች ፈተና ተሰጥቷል። ውጤቱም ለሰው ሃብት ሥራ አመራር ዳ/ሬት ተገልጾለታል።
ከኢትዮጵያ የሂሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማህበር ጋር በትብብር ለመስራት የተደረገውን ስምምነት መሰረት በማድረግ ከማህበሩ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ማህበሩ አሰልጣኞችን እንዲመድብ ተደርጎ በIFRS እና በመሰረታዊ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ላይ ለ515 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ጋር በአጋርነት ለመስራት የተደረገውን ስምምነት መሰረት በማድረግ በመሠረታዊ የኢንተለጀንስ ኪነ-ሙያ ስልጠና በዩኒቨርሲቲው አሰልጣኞች ከጉምሩክ ኮሚሽን እና ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ 83 አመራሮች እና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።
በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ለገቢዎች ሚ/ር 69 ከፍተኛ አመራሮች በአካዳሚው አሠልጣኞች በአመራር ሰጪነት (leadership) ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ለ32 የክልልና የከተማ የታክስ አስተዳደር ከፍተኛ አመራሮች ስለኢትዮጵያ የታክስ ሥርዓት ለተሠጠ ስልጠና የአካዳሚውን የፋሲሊቲና መስተንግዶ አገልግሎት መጠቀም ተችሏል። በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በResearch Methodology and Statistics ከገቢዎች ሚ/ር እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ለተውጣጡ 29 አመራሮች እና ባለሙያዎች፤ እንዲሁም በአሰልጣኞች ስልጠና (Training of Trainers) ከጉምሩክ ኮሚሽን ለተውጣጡ 19 አመራሮች እና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

ከአሜሪካ (USA) ትሬዠሪ ዲፓርትመንት የቴክኒክ ትብብር ጽ/ቤት በተደረገ የባለሙያ ድጋፍ በአሰልጣኞች ስልጠና (Training of Trainers) ለ25 አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ከገቢዎች ሚ/ር እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ለተውጣጡ 23 መካከለኛ አመራሮች በአመራር ሰጪነት (Leadership) ስልጠና ተሰጥቷል። ከዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት (IMF) በተገኘ የቴክኒክ ትብብር ድጋፍ በሁለት ዙር በDispute Resolution Related with MNC ርዕስ ላይ ለ75 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። በዚሁ መሰረት ለአምስትና ከዚያ በላይ

ለሆኑ ቀናት በተካሄዱ ስልጠናዎች ለተሳተፉ 2317 ሰልጣኞች በስልጠና ማዕከሉ በኩል የተሳትፎ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተሰጥቷል።

## 2.3 የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም

### ➲ የበጀት ስራዎችና አጠቃቀም አፈጻጸም

ሰንጠረዥ 3 የ2015 የበጀት አጠቃቀም በወጪ ሂሣብ መደቦች

| ተ.ቁ | የፕሮግራሞች ስም | የተፈቀደ በጀት | ዝውውር የተደረገባቸው | የተስተካከለ በጀት | እስከ ሰኔ 30 ዕቅድ | እስከ ሰኔ 30 በስራ ላይ የዋለ በጀት | የተጠቀሙት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **ስራ አመራር ፕሮግራም** | **1,060,663,200.00** | **1,017,304,566.42** | **2,077,967,766.42** | **2,077,967,766.42** | **1,924,782,310.34** | **92.63** |
| 2 | **ሀገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ** | **341,047,010.00** | **55,273,514.81** | **396,320,524.81** | **396,320,524.81** | **381,479,585.88** | **96.26** |
| 3 | **የታክስ ህግ ማስከበር** | **304,443,950.00** | **11,121,392.87** | **315,565,342.87** | **315,565,342.87** | **304,835,532.03** | **96.6** |
| 3.1 | የህግ ማስከበር ፕሮግራም | 298,765,350.00 | 9,920,227.17 | 308,685,577.17 | 308,685,577.17 | 298,417,487.07 | **96.67** |
| 3.2 | የፍትሀብሔር ጉዳዮች ፕሮግራም | 5,678,600.00 | 1,201,165.70 | 6,879,765.70 | 6,879,765.70 | 6,418,044.96 | **93.29** |
| 4 | **ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት** | **133,822,300.00** | **20,000,000.00** | **153,822,300.00** | **153,822,300.00** | **140,633,098.28** | **91.43** |
| 4.1 | የመረጃ ቴክኒሎጂ ትግበራ ፕሮግራም | 125,327,600.00 | 20,000,000.00 | 145,327,600.00 | 145,327,600.00 | 133,467,981.23 | **91.84** |
| 4.2 | የመረጃ ፕሮ/ ማሻሻል ፕሮግራም | 8,494,700.00 | - | 8,494,700.00 | 8,494,700.00 | 7,165,117.05 | **84.35** |
| 5 | **የተገልጋዮች ትምህርትና ድጋፍ** | **181,314,350.00** | **-1,819,908.50** | **179,494,441.50** | **179,494,441.50** | **162,745,628.33** | **90.67** |
| 5.1 | የትምህርትና ግንኙነት ፕሮግራም | 32,502,200.00 | 11,808,154.24 | 44,310,354.24 | 44,310,354.24 | 43,161,202.19 | **97.41** |
| 5.2 | የደንበኞች አገልግሎት ፕሮግራም | 148,812,150.00 | -13,628,062.74 | 135,184,087.26 | 135,184,087.26 | 119,584,426.14 | **88.46** |
| **ድምር** | | **2,021,290,810.00** | **1,101,879,565.60** | **3,123,170,375.60** | **3,123,170,375.60** | **2,914,476,154.86** | **93.32** |

### ➡ የውስጥ ኦዲት ስራዎች አፈጻጸም

**የ2014 በጀት ዓመት የሰኔ 30 የፈሰስና ቆጠራ ሪፖርት ማቅረብ፤**

የ2014 በጀት ዓመት የዋ/መ/ቤትና ከአስራ አንድ ቅ/ጽ/ቤቶች የቀረቡ የቆጠራ እና የተጠቃለለ የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት በማጣራት፣ በመመዝገብና በማደራጀት ለሚኒስትሩ በአድራሻ እና በገንዘብ ሚኒስቴር ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በግልባጭ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

**የፋይናንስ፣ የሕጋዊነትና የክዋኔ ኦዲት ሥራ ማከናወን ሪፖርት በማቅረብ፡-**

የ2014 በጀት ዓመት የ4ኛ ሩብ ዓመት፣ የ2015 በጀት ዓመት የአንደኛ፣ የሁለተኛ እና 3ኛ ሩብ ዓመት የበጀት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የሕጋዊነትና የፋይናንስ ኦዲት ሪፖርት፣ ከዋና መ/ቤት አራት (4) እና ከአስራ አንድ ቅ/ጽ/ቤቶች አርባ አራት (44) ሪፖርቶች ተጠቃሎ ቀርቧል። በዋና መ/ቤትና ቅ/ጽ/ቤቶች በበላይ አመራሩ የታዘዙ ልዩ የኦዲት ሥራዎችን በማከናወን ሰባት (7) ሪፖርቶች ቀርበዋል። የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረት ልማቶች እና የታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን እና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት በማድረግ ሁለት ሪፖርቶች ቀርበዋል።

**➡ በዋና መ/ቤትና ቅ/ጽ/ቤቶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ግኝቶች ላይ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ የየሩብ ዓመቱን ሪፖርት የማቅረብ አፈጻጸም**

በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከ2008 እስከ 2013 በጀት ዓመት በግኝት ተይዘው በሙሉ እና በከፊል ማስተካከያ የተደረገባቸው የ2014 በጀት ዓመት 4ኛ፣ በ2015 በጀት ዓመት 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ሩብ ዓመት ግኝቶች ዝርዝር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለፕላን በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለመንግስት ወጭ አስተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ወጪ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት ከሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት ወደ 2015 በጀት ከዞረው በብር 7,762,069,625.42 በቁጥር 246 ግኝቶች የእርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ በቁጥር 52 በከፊል በ63 ግኝቶች ላይ ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን እንዲሁም በገንዘብ ብር 3,266,358,696.03 ላይ ማስተካከያ ተደርጓል።

**ሰንጠረዥ 4 የኋላ ዘመናት የፌዴራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም በዝርዝር**

| ተ.ቁ | የእርምጃ አወሳሰድ | እርምጃ የተወሰደበት የገንዘብ መጠን በምር |
|---|---|---|
| 1 | በገንዘብ የተሰበሰቡ | 1,330,080,102.51 |
| 2 | በመመሪያ ቁጥር 137/2010 እና 64/2012 መቀጫው የተነሳ | 17,452,635.38 |
| 3 | ከተመላሽ ላይ የተካካሰ | 13,684,490.07 |
| 4 | በቀረቡ ሰነዶች ማስተካካያ የተደረገባቸው | 56,472,848.10 |
| 5 | በታክስ ኦዲተሮች የሚወሰን ግብር አለመኖሩ የተረጋገጠ | 281,093.26 |
| 6 | በኦዲት ውሳኔ ላይ ድምር ስህተት በመኖሩ የተስተካከለ | 154,236.86 |
| 7 | ካሳወቁት ክሳራ ላይ የተቀናነሰ | 75,591,026.62 |
| 8 | የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ የተደረገ | 540,543.95 |
| 9 | በፍርድ ቤት ክርክር ላይ በመሆናቸው ከግኝት እንዲወጡ የተደረጉ | 8,254,818.66 |

| ተ.ቁ | የእርምጃ አወሳሰድ | እርምጃ የተወሰደበት የገንዘብ መጠን በምር |
|---|---|---|
| 10 | በፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት ላይ የተቀናነሰ መሆኑ በደብዳቤ የተገለጸ | 1,735,020,817.87 |
| 11 | በታክስ ይግበኝ ኮሚሽን ውሳኔ መሠረት የተካካሰ | 2,791,835.82 |
| 12 | በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተሻረ | 17,717,400.00 |
| 12 | በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ውሳኔ የተስተካከለ | 8,316,846.93 |
| | ድምር | 3,266,358,696.03 |

ለ2015 በጀት ዓመት በተያዘው የመስክ ምልከታ ዕቅድ መሠረት በባህርዳር፣ በሐዋሳ፣ በምስራቅ፣ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛ፣ ድሬደዋ፣ ጅማ፣ አዳማ እና በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በፌደራል ዋና ኦዲተር የ2014 በጀት ዓመት በረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት የቀረቡ ግኝቶች ላይ በአካል በመገኘት ምላሽ ሊቀርብባቸው የሚችሉ ግኝቶች ላይ ቅ/ጽ/ቤቶቹ የተቋሙ የተጠቃለለ የሥራ አመራር ሪፖርት እስኪወጣ ድረስ ማስተካከያ ተደርጎባቸው ምላሽ እንዲቀርብባቸው ከግዥና ፋይናንስ፣ ከገቢ ሂሳቦች አስተዳደር፣ ከታክስ ማስታወቅ፣ ከታክስ ዕዳ እና ከንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳሬክቶሬት በተውጣጡ ባለሙያዎች በአካል በመገኘት የሙያ ድጋፍ በማድረግ እና በቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በተደረገው ክትትል የብር 14,788,507,732.70 ማስተካከያ የተደረገባቸው ሲሆን ዝርዘሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 5 የ2014 የፌዴራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያ አፈጻጸም

| ተ. ቁ | የቅ/ጽ/ቤቱ ስም | በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ረቂቅ የስራ አመራር ሪፖርት ላይ የተያዘ | በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የመጨረሻ የስራ አመራር ሪፖርት ላይ የተያዘ | ማስተካከያ የተደረገበት ግኝት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 13,148,645,988.11 | 4,787,994,578.21 | 8,360,651,409.90 |
| 2 | መካከለኛ | 1,316,574,155.62 | 975,333,663.13 | 341,240,492.49 |
| 3 | ምስራቅ | 1,238,872,616.82 | 823,915,056.94 | 414,957,559.88 |
| 4 | ምዕራብ | 1,937,046,898.00 | 1,191,382,675.09 | 745,664,222.91 |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 1,179,821,587.71 | 524,622,908.49 | 655,198,679.22 |
| 6 | አዳማ | 2,102,955,412.01 | 36,087,402.56 | 2,066,868,009.45 |
| 7 | ባህርዳር | 169,420,175.64 | 47,029,004.36 | 122,391,171.28 |
| 8 | ጅማ | 564,261,425.35 | 48,444,700.72 | 515,816,724.63 |
| 9 | ሐዋሳ | 1,312,308,528.80 | 5,067,527.32 | 1,307,241,001.48 |
| 10 | ድሬዳዋ | 534,960,901.14 | 322,817,337.71 | 212,143,563.43 |
| 11 | ዋናው መ/ቤት | 53,390,981.96 | 7,056,083.93 | 46,334,898.03 |
| | ድምር | 23,558,258,671.16 | 8,769,750,938.48 | 14,788,507,732.70 |

በሚኒስቴሩ ዋና መ/ቤት በውስጥ ኦዲተሮች የተከናወነ የውስጥ ኦዲት ግኝት ክትትል በማድረግ የቀረቡ ምላሾችን በመመዝገብ የ2014 በጀት ዓመት 4ኛ፣ የ2015 በጀት ዓመት 1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት ከማቅረብ አኳያ ከዋና መ/ቤት የቀረቡ የክትትል የኦዲት ግኝት ምላሾች ትክክለኛነት በማረጋገጥ በዋናው መ/ቤት በግዥና ፋይናንስ፣ በንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት፣ በመረጃ ቴክኖሎጂ፣ በሽያጭ መመዝገቢያ እና በሰው ሃብት ዳይሬክቶሬቶች ተመዝግቦ ከሚገኝ በድምሩ ብር 4,278,740,415.46 በቁጥር 139 ግኝት ውስጥ ብር 3,198,302,991.11 እና በቁጥር 27 ግኝቶች 74.75 በመቶ ማስተካከያ ተደርጎ ሪፖርቱ ወጪ ሆኖ ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለሚኒስት ጽ/ቤት እና ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ጽ/ቤት ቀርቧል፡፡

## ➲ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነት ማሻሻል አፈጻጸም

የገቢዎች ሚኒስቴር ከተሰጠው ተልዕኮ እና ከያዘው ርዕይ አንጻር ለግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና አርኪ አገልግሎት በመስጠት ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ ከጊዜው ቴክኖሎጂ ጋር መዘመኑ የምርጫ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድም ቀድሞ ከ20 ዓመት ጀምሮ ሲጠቀምባቸው የነበሩ ለሀገር ውስጥ ግብርና የጉምሩክ ቀረጥ አስተዳደር የሚገለገልባቸውን የተለያዩ የኮር ሲስተሞችና ለአስተዳደራዊ ተግባር የሚገለገልባቸው ስርዓቶች በየጊዜው በማሻሻል፣ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረጸውን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲ እና በአዋጅ ቁጥር 1205/2012 የወጣውን የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ መነሻ ተቋሙ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ርዕይ እውን የሚያደርጉ በርካታ የቴክኖሎጂ ማሻሻያዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የወረቀት አልባ ስርዓትን ከመተግበር አንጻር በውስጥ ባለሙያዎች ለሁለቱም ተቋማት የተሰሩ የኮርፖሬት ስራዎችን የሚደግፉ ስርዓቶች ለምሳሌ፦ የሰው ሀብት አስተዳደር(HRMS)፣ ድህረ ገጽ(www.mor.gov & ecc.gov)፣ የደብዳቤ መጻጻፊያ (Electronics Letter Management system)፣ መልዕክት መለዋወጫ (ITSM)፣ Performance Management and Appraisal(BSC) ማሻሻያ፣ እንዲሁም ለታክስ መረጃ መሰብሰቢያ የሚያገለግሉ እንደ Tax Administration Support System (TASS)፣ የገበያ ዋጋ መሰብሰቢያ ሲስተም(Fare Market Value Collection System) ፣ የFD የሽያጭ ማሽን መሣሪያዎች መመዝገቢያና መከታተያ እና የመሳሰሉት ለአብነት የሚጠቀሱና ተቋሞቹን በተወሰነ ደረጃ ወደ ወረቀት አልባ አሰራር የቀየሩ ልማቶች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በኮር ቢዝነሶች ስርዓቶች ማለትም በSIGTAS እና eCMS ማሻሻያዎች ላይ በየጊዜው በውስጥ ባለሙያዎች ከሚደረጉ መለስተኛ የማሻሻያና የክትትል ስራዎች ጎን ለጎን አዲስ የወጡ አዋጆችና መመሪያዎችን ተከትሎ በታክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ እና በWeb Fountain ባለሙያዎች ድጋፍ የኤክሳይዝና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲስተም ማሻሻያ፣ ኢ-ማስታወቅ ማሻሻያ ፣ ኢ-ክፍያ ከደራሽ ጋር ማሻሻያ፣ የገቢ ትልልፍ (Revenue Sharing) ፣ የዳታ ዌር ሀውስ የሪፖርቲንግ ሥራዎች (RDW)፣ የየዳታ ቤዞቹን አሰራር ቀልጣፋ ማድረግ (Performance Tuning) ፣ የካሽ አልባ ስራን ያቀላጠፈ ከደራሽ በተጨማሪ የቴሌብር ኢንተግሬሽን እና ሌሎች በርካታ የሲስተም ማሻሻያ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

- የኢ-ፋይሊንግ ሲስተምን ወደ ተሻሻለ ቴክኖሎጂ የመቀየር እና ተጨማሪ አፕሊኬሽን ሰርቨሮችን በመጨመር ፍጥነት እንዲኖረው መደረጉ አገልግሎት አሰጣጡ እንዲቀላጠፍ አድርጎታል፡፡ ባጠቃላይ በኢ-ፋይሊንግና በኢፔይመንት ሲስተም ላይ 12 ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡
- ግብርና ሌሎች ክፍያዎችን በቴሌ-ብር ለመክፈል እንዲቻል ለጉምሩክ ኮሚሽን፣ ለአዲስ አበባ ገቢዎች እንዲሁም ለገቢዎች ሚኒስቴር የሚሆን አይፒሴክ ቻናል ተሰርቷል፡፡

- TeleBirr E-Payment Integration API development እና በAPI መረጃ ልውውጥ ሙከራ ተከናውኖ ከየካቲት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተተግብሮ ከበፊቱ የደራሽ ካሽ አልባ የክፍያ ስርዓት በተጨማሪ የTELEBIRR አማራጭ የክፍያ ስርዓት በተሳካ ሁኔታ ተተግብሯል:: እስካሁንም በ1,234 ግብር ከፋዮች ፣ ለ11 የግብር ዓነቶች፣ 3,934 ትራንዛክሽን ተፈጥሮ 1.07 ቢሊዮን ብር በቴሌብር አማካይነት መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፤ የተጠቃሚዎች ቁጥር ለመጨመርና የክፍያ መጠኑን ለማሳደግ ከግለሰብ በተጨማሪ የድርጅት የቴሌብር አካውንት በስርዓቱ ለማካተት በቴሌኮም በኩል እየተሰራ ይገኛል:: ስለሆነም በሚኒስቴሩ በኩል TELEBIRR ፕላትፎርም ስርዓት partial payment እንዲቀበል ቀሪ ስራዎች በቀጣይ የሚጠናቀቁ ይሆናል::
- በተመሳሳይ የኢትዮ ቴሌኮም የTELEBIRR የነዳጅ ክፍያ ስርዓት ደግሞ እስካሁን በትግበራው እንደታየው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላካተተ በመሆኑ፤ በሚኒስቴሩ በኩል ይሄው አስተያየት ለኢቴዮ ቴሌኮም ቀርቦላቸው ስርዓቱ ለግብር አወሳሰን ግብዓት የሚሆን መረጃ መላክ በሚያስችል መልኩ ግብይቱን የሚፈጽሙትን የነዳጅ ማደያውንና የነዳጅ ቀጂውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን አካቶ በመሻሻል ላይ መሆኑና በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ከኢትዮቴሌኮም ተገልጿል::
- በዚህ በጀት ዓመት ብቻ 8 ባንኮች በኢፔይመንት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆኑ ባጠቃላይ 19 ባንኮች እስካሁን ተሳታፊ ሆነዋል:: ሙከራ አከናውነው ያጠናቀቁ 3 ባንኮች ናቸው:: ሙከራ እያከናወኑ ያሉና ቴስት ዶክመንት የተላከላቸው 4 ባንኮች ነበሩ:: ኢፔይመንት ታሳታፊ የሆኑ ነገርግን ተጨማሪ ሙከራ እያደረጉ ያሉ፦ እናት ባንክ፣ ዳሽን ባንክ፣ አቢሲኒያ ባንክ እና ብርሃን ባንክ ናቸው::
- Integration of TIN Number to National ID(FAYDA) API development (Testing Phase) የተከናወነ ሲሆን፤ ቴስት ተደርጎ ወደ ፕሮዳክሽን ስራ እንዲገባ ተደርጓል:: ለNational ID Project ቀደም ሲል ከተሰራው IPSec Tunnel በተጨማሪ ለTest and Production ይፈለጉ የነበሩ ሰርቨሮችን የማገናኘት ስራ ተሰርቷል::
- የ IFMIS(MOFEC) interface schedule ከአሲኩዳ እና ከ eCMS ሲስተም ጋር ያለው ኢንተርፌስ ፣ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል፣
- Ethio Telecom API integration (የደንበኞች መረጃ ከገቢዎች ሲስተም ጋር ማናበብን በተመለከተ ደንበኞች አገልግሎት ሲገዙ በሚያቀርቡት ቲን መሰረት የደንበኛውን ስም፣ አድራሻ ወዘተ በቀጥታ በኦንላይን ማናበብ) በሂደት ላይ ይገኛል::

በመሠረተ-ልማት አንጻር ደግሞ በአውሮፓ ህብረት/GIZ ድጋፍ በተለይ በዳታ ማዕከሉ የሜክሲኮ ዳታ ሴንተር ውስጥ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ የኔትወርክ ዕቃዎች ማለትም ኮር ስዊችና ቶፕ ኦፍ ራክ ስዊች (Core Switch & TOP of Rack Switch) ፣ የሳን ስዊች በአዲስ የመቀየር፣ እንዲሁም የተለያዩ ራውተሮችና እስዊቾች ኮንፊገር መደረጉ፣ በሁለቱም ተቋሚት ያሉት መተግበሪያ ስርዓቶች (Application System) የነበራቸው የመረጃ ቅብብሎሽ ፍጥነት እንዲጨምር ከፍተኛ

አስተዋጽኦ በማበርከቱ አገልግሎት አሰጣጡን ከበፊቱ የበለጠ አቀላጥፎታል፡፡ የኤስኤስኤል ሰርተፍኬት፣ የፎርቲጌት ላይሰንስ እና ዶሜይኖች ዕድሳት ተከናውኗል፡፡

- በዳታ ማዕከል ያሉ ዋና ዋና የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መሣሪያዎች እንደ Storage and Servers, Uninterrupted Power Supply (UPS), Air Conditioner (AC), Core Switches, Routers, Telocom apparatus, Electric Installation እና የመሳሰሉ መሣሪያዎች መደበኛ ጥገናና በተገቢው ሁኔታ ሥራ መስራታቸውን ክትትል ተደርጓል፡፡
- በተቋሙ ለሚገኙ የSIGTAS and the subsystems eFiling, ePayment, DatawareHouse, TASS, CashRegister GPRS & FD, BioDB, ለጉሙሩክ eCMS and its Subsystem TPM, ECVS, ECVS-G2, FACEVET, VDD, and ASYCUDA ስርዓቶች እንዲሁም Internet & Outlook፣ የInternal firewall ሥርዓቶች ዳታቤዝ ባክአፕ መያዝና የክትትል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በተጨማሪ ከትግራይ ወደ ሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት የዞረ የግብር ማዕከል ብዛት 658 ናቸው፣ ስራ ለጀመሩ የመቀሌ ቅርንጫፍና የክልሉ ገቢዎች የሲግታስ የመጠቀሚያ ይለፍ ቃል እንደገና ሪሴት የማድረግና አዲስ ለተጠየቁ ደግሞ እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡ ለትግራይ ክልል ገቢዎች ለአንድ ሳምንት ያክል ለ45 ሰዎች የቲን ፋይዳ/ናሽናል አይዲ ዙሪያ የድጋፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

## 2.4 የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል አፈጻጸም

### ➲ የሀገር ውስጥ አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል

**የተደረገ የሀገር ውስጥ አጋርነት ስምምነት፡-** ከስትራቴጂክ አጋር አካላት ጋር በቅድሚያ ሚናቸውን በመለየት ግንኙነት መፍጠር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም፣ ቋሚ አደረጃጀት መፍጠር፣ የተፈረሙ ስምምነቶችን በጋራ እቅድ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ እና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተል፣ የሚከሰቱ ችግሮች ካሉ በጋራ ለመፍታት ታቅዶ ከ15 አጋር አካላት ጋር (በአጠቃላይ ቁጥር ወደ 36 ከፍ ያደረገ) በጋራና በትብብር መስራት የሚያስችል ስምምነት ተፈርሟል፡፡ ዝርዝሩም፡-

- ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት ስጋትን የመከላከል እና አደጋ መቋቋም የመረጃ ልውውጥ እና ትብብር፣
- ከፋይናንስና መረጃ ደህንነት ማዕከል ጋር በመረጃ ልውውጥ በትብብር ለመስራት፣
- ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከፌዴራል ፖሊስ፣ ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር የታክስና የጉምሩክ ወንጀሎችን ለመከላከል እና አጥፊዎችን በህግ ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል፣
- የታክስ ክፍያ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለማሰባሰብ የሚያስችል የአገልግሎት አሰጣጥ ስምምነት ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና ከ10 ባንኮች (ከደቡብ ግሎባል፣ ከቡና፣ ከእናት፣

ከዓባይ፣ ከንብ ኢንተርናሽናል፣ አንበሳ ኢንተርናሽናል፣ ከአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ ከኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ፣ ከዘምዘም ባንክ፣ ከሂጅራ ባንክ) እና ኢትዮ ቴሌኮም ጋር ተፈርሟል፣

- ከብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል፣
- በኢትዮ ቴሌኮም 7 የተመረጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች የአገልግሎት ስምምነት ረቂቅ ሰነድ ላይ የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች በሰጡት አስተያየት ላይ የጋራ ግንዛቤና አቋም ለመያዝ ውይይት ተደርጎ ቀሪ ስራው የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ተከታትሎ እንዲጨርስ መግባባት ላይ ተደርሷል:: ወደ ትግበራ የገባ ስምምንት፦ የተፈረሙ ስምምነቶችን በጋራ እቅድ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ እና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተል፣ የሚከሰቱ ችግሮች ካሉ በጋራ ለመፍታት በታቀደው መሰረት::
- ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ ከጉምሩክ ኮሚሽን ከገቢዎች ሚ/ር ጋር የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት ስጋትን የመከላከል እና አደጋ መቋቋም የመረጃ ልውውጥ እና ትብብር የሦስትዮሽ መግባቢያ ሰነድ መሠረት የጋራ ፎረም ለማቋቋም ከሚኒስቴር መ/ቤታችን የተወከለውን የማሳወቅ እና ፎረሙ ወደ ትግበራ እንዲገባ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፣
- Association of Chartered Certified Accountants (ACCA) ከታክስ ኦዲት፣ ስልጠና ማዕከልና የሰው ሃብት ጋር እቅድ ለማዘጋጀት እንቅስቃሴ ቢጀመርም ወደ ተግባር መግባት ላይ ክፍተት የሚታይበት መሆኑ፣
- የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎች ማህበር በIFRS ርዕስ ለ281 ታክስ ባለሙያዎች እና በመሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ለ135 ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ መሆኑ፣
- ከአካውንቲንግና ኦዲት ቦርድ ጋር የተቋቋመው ግብረ-ሃይል (ኮሚቴ) ወደ ስራ እንዲገባ ግብረ-ሃይሉ እንደገና ለማደራጀት ከፍተኛ አመራር በሚገኝበት መድረክ ለማዘጋጀት ቦርዱን የማነጋገር ስራ ተሰርቷል፣
- በአጠቃላይ ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ የተፈረሙ የባንኮች ብዛት 19 ሲሆኑ ወደ ስራ የገቡት 18 ሲሆኑ በተጨማሪም ኢትዮ ቴሌኮም በኢ-ክፍያ ስርዓት ወደ ትግበራ ገብቷል፣

➡ **የውጭ ሀገራትና ድርጅቶች አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል**

**የተደረገ የውጭ አጋርነት ስምምነት፦** ተቋሙ ተልዕኮውን ለማሳካት እንዲያስችለው ትብብር መፍጠር አስፈላጊ የሆነባቸውን አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ድርጅቶችን በመለየት፣ ትብብር ለመፍጠር የሚያስችሉ ስምምነቶችን ለማፈራረም በታቀደው መሰረት የሚከተሉት ተግባራት ተፈጽመዋል::

- የአውሮፓ ህብረት ቢዝነስ ፎረም የመግባቢያ ስምምነት ለማደስ ረቂቅ የመግባቢያ ሠነድ ተዘጋጅቶ የፎረሙ እና የስራ ክፍሎች ግብአትና አስተያየት ተካቶበት ለፊርማ ተዘጋጅቷል፣
- የአለም የገንዘብ ድርጅት ፊስካል ጉዳዮች ዲፓርትመንት (IMF-FAD) ቀጣይ የRevenue Mobilization Trust Fund (RMTF) የቴክኒክ እና የዓቅም ድጋፍ ፍላጎት ከሥራ ክፍሎች ጋር ተዳስሷል፣ ከድርጅቱ ምላሽ እየተጠበቀ ይገኛል፣

- የUS OTA በorganizational Health የተጀመረው የቴክኒክ ድጋፍ እንዲቀጥል ለድርጅቱ ጥያቄ (ኢሜይል) ቀርቦ በበጀት ምክንያት እንደማይቀጥል ገልጿል፣
- የUK IFS በታክስ ጥናት እና መረጃ ትንተና ዙሪያ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር በጋራ ለመስራት ውይይት ቢደረግም መቀጠል አልተቻለም፣
- የHMRC የTransfer Pricing Confidentiality Agreement ጥያቄ ላይ በዘርፉ ውሳኔ/አቅጣጫ እንዲሰጥበት ተጠይቋል።

**የተገኘ የውጭ የቴክኒክ ድጋፍ፦** የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮፖዛል መንደፍና ማፀደቅ፣ ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር የአፈጻጸም ሰነድ ማዘጋጀት እና ስለተፈጻሚነቱ ድጋፍና ክትትል ለማድርግ ታቅዶ፦

- በንግስቲቱ ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤት (HMRC) በስጋት ሥራ አመራር እና በዋጋ ትልልፍ ኦዲት ላይ 3 ጊዜ የቴክኒክ ድጋፍ ተመቻችቷል፣ በቀረበው ሪፖርት ላይ አስተያየት/ግብረመልስ እንዲሰጥ ክትትል ተደርጓል፣
- የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) በታክስ ቅሬታ አፈታት (Tax Dispute Resolution) ለ47 ተሳታፊዎች የዓቅም ግንባታ ስልጠና ላይ፣ በGender & Revenue Admin ለ2 የስራ ክፍሎች፣ በስርዓተ-ፆታና ገቢ አስተዳደር ዌብናር ለ3 የስራ ክፍሎች፣ ተመቻችቷል፣
- የUE/GIZ BEIC project (Core switch replacement፣ COBIT and ITIL training የተካሄደ ሲሆን E-Filing Improvement በሂደት ላይ ይገኛል፣
- የBRITACOM (ለ136 ክፍሎች) 'Mobile Applications for the Fulfillment of Tax Obligations by Citizens & Entrepreneurs ሰሚናር ላይ 12 የስራ ክፍሎች፣ 2nd Tax Admimistration Theme Day Activity ሰሚናር ላይ 14 የስራ ክፍሎች፣ በExchange of Information & Inter-Agency Cooperation in Combating Tax Crimes ሰሚናር ለ13 የስራ ክፍሎች፣ በVAT Reform ስልጠና ላይ ለ7 የስራ ክፍሎች፣ በTax Dispute Resolution ለ15 የስራ ክፍሎች፣ በDigitalization of Tax Administration (DTA) ላይ ለ6 የስራ ክፍሎች፣ በTax Payer Service ለ16 የስራ ክፍሎች፣ በRisk Management ለ16 የስራ ክፍሎች፣ በLarge Business Management ላይ ለ8 የስራ ክፍሎች፣ በTaxes Collection & Taxable Capacity Building for Developing Countries ለ13 የስራ ክፍሎች እና በ3rd Theme Day Activity ለ15 የስራ ክፍሎች የኦንላይን ሰሚናር/ስልጠና እንዲሳተፉ፣ በRoundtable Meeting 1 የስራ ክፍል እንዲሳተፍ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፤* የ3ኛ BRITACOF Participation የማመቻቸት ሥራ ተሠርቷል፣
- የቻይና ኢምባሲ (ለ46 ክፍሎች) seminar on Use of IT in Tax Administration for BRI Countries ለ8 ተሳታፊዎች፣ በTax Service & Business Environment for BRI Countries ለ17 የስራ ክፍሎች (ለ19 ተሳታፊዎች) ፣ IT in Tax Admin for African Countries ለ6 ተሳታፊዎች እና mgt & application of Govt big Data in the Cloud environment ሰሚናር ለ5 ተሳታፊዎች፣ በTax Collection & Management እና በ'Tax

Service for Belt & Road Countries" ሰሚናር ላይ 8 ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሳተፉ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፣

- የATI Secretariat (ለ29 ክፍሎች) በRegional Workshop on Tax Expenditures (ኬንያ ገቢዎች ባለስልጣን) ለአንድ ሃላፊ እና በEvidence-Based Fiscal Policy Tools to Improve Equity ዌብናር ለ4 የስራ ክፍሎች፣ Enhancing Tax Accountability through Citizen Participation & Education ዌብናር ለ3 የሥራ ክፍሎች፣ A gendered approach to taxation: Improving the equitability & efficiency of DRM ለ6 ተሳታፊዎች፣ በEnhancing transparency & efficiency in tax expenditures assessment ፓነል ለ5 ተሳታፊዎች ተመቻችቷል፣ በPartner countries' experiences with formulating & implementing national revenue reform strategies ዌብናር ለ5 የስራ ክፍሎች፣ በPolicy Design for Effective Property Taxation ለ5 የስራ ክፍሎች ተመቻችቷል፣

**በራሳቸው ተነሳሽነት የተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ፡** በራሳቸው ተነሳሽነት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ሲገኝ ስለተፈጻሚነቱ ድጋፍና ክትትል ለማድርግ ታቅዶ፦

- የWBG/IMF Tax Sunday (Taxation in times of high inflation) Conference ለ8 ተሳታፊዎች፣
- የATAF 7th General Assembly (GA) Conference ላይ ለ3 ተሳታፊዎች፣
- የIGF Secretariat (10 Ideas to Transform Mining Taxation ዌብናር ለ14 የስራ ክፍሎች 2 ጊዜ እና Financial Benefit Optimization ዌብናር ለ5 ሥራ ክፍሎች፣
- የEAST AFRITAC Artificial Intelligence workshop in Customs Admin (Zanzibar) ለ1 የሥራ ክፍል፣
- የICTD Research with in Tax Administration (Brighton, UK) ላይ ለ2 ሥራ ኃላፊዎች እንዲሳተፉ ድጋፍ ተደርጓል::

## ➲ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች አፈጻጸም

**ሰንጠረዥ 6 የኮሙኒኬሽን ስራዎች አፈጻጸም**

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የ12 ወራት ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ የተፈጠሩ የፌስ ቡክ ተከታዮች | በቁጥር | 20,256 | 19,236 | 95 |
| 2 | አዲስ የተፈጠሩ የዩቲዩብ ተከታዮች | በቁጥር | 840 | 638 | 75.9 |
| 3 | አዲስ የተፈጠሩ የቴሌግራም ተከታዮች | በቁጥር | 7,200 | 9,238 | 128.3 |
| 4 | የተዘጋጁ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች | በቁጥር | 52 | 50 | 96.2 |
| 5 | የተዘጋጁ የሬድዮ ፕሮግራሞች ብዛት | በቁጥር | 52 | 49 | 94.2 |
| 6 | የተዘጋጁ የቴሌቪዥን ስፖቶችና ጭውውቶች ብዛት | በቁጥር | 6 | 6 | 100 |
| 7 | በተግባቦት መንገዶች የተላለፉ መልዕክቶች ብዛት | በቁጥር | 48 | 61 | 127 |
| 8 | በማህበራዊ ሚዲያ የተሰራጩ መረጃዎች ብዛት | በቁጥር | 380 | 426 | 112.1 |
| 9 | በድህረ-ገፅ ተደራሽ የተደረጉ መረጃዎች ብዛት | በቁጥር | 48 | 43 | 90 |

| ተ.ቁ. | ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የ12 ወራት ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የተዘጋጁ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ብዛት | በቁጥር | 4 | 4 | 100 |
| 11 | የተዘጋጁ የእኛ ለእኛ ጋዜጣ ዕትሞች ብዛት | በቁጥር | 12 | 12 | 100 |
| 12 | የተዘጋጁ የገቢያችን ህልውናችን ጋዜጣ ዕትሞች ብዛት | በቁጥር | 12 | 12 | 100 |
| 13 | የተዘጋጁ የዶክመንተሪ ፊልሞች ብዛት | በቁጥር | 4 | 4 | 100 |
| 14 | በዩቲዩብ የተሰራጩ የቪዲዮ መረጃዎች ብዛት | በቁጥር | 52 | 40 | 77 |
| 15 | በቴሌግራም የተሰራጩ መረጃዎች ብዛት | በቁጥር | 204 | 252 | 123.5 |
| 16 | የተዘጋጁ ማስታወቂያዎች ብዛት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 |
| 17 | የተዘጋጀ ዓመታዊ መጽሔት ብዛት | በቁጥር | 1 | 1 | 100 |
| 18 | የተዘጋጀ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ሪፖርት ብዛት | በቁጥር | 12 | 12 | 100 |
| 19 | የተዘጋጀ የሚዲያ ጉብኝት /ሚዲያ ቱር/ ብዛት | በቁጥር | 3 | 2 | 66.6 |

## 2.5 ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረግ ድጋፍና ክትትል ማሻሻል አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም፣ የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም፣ የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም፣ በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም እና ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ስራዎችን በመስራት የዘርፉ ዕቅድ ከተጠሪ ተቋማት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

### ➲ ከክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ገቢ ተቋማት ከድጋፍ አንጻር የተሰሩ ስራዎች

#### ❖ ስልጠናዎች

ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ባለሙያዎች እና የስራ ኃላፊዎች በተለያዩ 18 ርዕሶች ለ1681 ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1560 ስልጠናውን የወሰዱ ሲሆን የዕቅዱን 92.8 በመቶ ተከናውኗል፡፡ ከዚህ ውስጥ በማዕከል የተሰጠ 673 ሲሆን በአካል በክልሎች በመገኘት ደግሞ 887 ነው፡፡

ሰንጠረዥ 7 በ2015 በጀት ዓመት ስልጠና የወሰዱ የክልሎች /ከተማ አስተዳደሮች

| ተ.ቁ. | ክልል/ከተማ አስተዳደር | ዕቅድ | ክንውን | | | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በስልጠና ማዕከል | በአካል በመገኘት | ድምር | |
| 1 | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | 527 | 86 | 429 | 515 | 97.72 |
| 2 | ኦሮሚያ | 318 | 118 | 214 | 332 | 104.40 |
| 3 | አማራ | 146 | 74 | 37 | 111 | 88.18 |
| 4 | ሲዳማ | 126 | 72 | 45 | 117 | 92.86 |
| 5 | ደቡብ ብ/ብ ህዝቦች | 246 | 98 | 145 | 243 | 98.78 |
| 6 | ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር | 31 | 23 | 0 | 23 | 74.19 |
| 7 | ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | 45 | 33 | 0 | 33 | 73.33 |
| 8 | ጋምቤላ | 48 | 38 | 0 | 38 | 79.17 |
| 9 | ቤንሻንጉል ጉምዝ | 33 | 23 | 0 | 23 | 69.70 |
| 10 | ሀረሪ | 60 | 27 | 17 | 44 | 73.33 |
| 11 | አፋር | 48 | 37 | 0 | 37 | 77.08 |
| 12 | ሶማሌ | 53 | 44 | 0 | 44 | 83.01 |

| ተ.ቁ. | ክልል/ከተማ አስተዳደር | ዕቅድ | ክንውን | | | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በስልጠና ማዕከል | በአካል በመገኘት | ድምር | |
| ድምር | | 1681 | 673 | 887 | 1560 | 92.80 |

❖ **የተሰጡ የመረጃ ቴክኖሎጂ አገልግሎት ድጋፎች**

- የአማራ፣ ኦሮሚያ እና ሀረሪ ክልሎች ገቢ ተቋማት ወደ ኤሌክትሮኒክ ታክስ ስርዓት /E-Tax/ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ወደ ኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስርዓት/E-Payment/ እንዲገባ ተደርጓል፡፡
- ኦሮሚያ እና ሀረሪ ክልሎች ገቢ ተቋማት የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዩችን የግብር አወሳሰኑ በቀጣይ 2016 በጀት ዓመት በሲግታክስ ሲስተም እንዲታገዝና ክፍያም በኢ-ታክስ ታክስ እንዲሰበሰብ የሙከራ ስራ ተጠናቅቆ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡
- የአማራ፣ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ እና የሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ለገቢ ተቋማት 63 / ስድሳ ሶስት/ የታክስ ማዕከል በጥያቄዎቻቸው መሠረት እንዲከፈትላቸው ተደርጓል፡፡
- የኦሮሚያ እና አማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ ለ7 ባለሙያዎች የሲግታስ የይለፍ ቃል /Password/ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡
- የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት ገቢዎች ቢሮ በገኘው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ውክልና ለተሰጣቸው ወኪሎች መለያ ኮድ / Prefix Code/ ለ7 የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ለ3 ልማት ድርጅቶች እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡
- ለአማራ ገቢዎች ቢሮ የንግድ ስራ ያቋረጡ 5814 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎችን ፋይል በሲስተም (D-Activate) እንዲደረግላቸው ተደርጓል፡፡
- የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን ለ17 ባለሙያዎች IP address እንዲከፈትላቸው ተደርጓል፡፡

❖ **የቁሳቁስ ድጋፎች**

- ለጋምቤላ ክልል 2 ሞተር ሳይክል ፣ 2 የጣት አሻራ ማሽን እና 10 ዴስክቶፕ ኮምፒውተር ፣ ለቤንሻንጉል ክልል 2 ሞተር ሳይክል እና 10 ዴስክቶፕ ኮምፒውተር የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር 10 ኮምፒተሮች እና ለሲዳማ ክልል 10 ዴስክቶፕ ኮምፒውተር ድጋፍ ተደርጓል፣
- በስራ ላይ ያሉ የታክስ ህጎች (አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሰርኩላሮች) ታትመው የወጡ 6 ጥራዞች ለሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በሶፍት ኮፒና ሀርድ ኮፒ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
- የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት መስተዳደር የገቢዎች ቢሮ ለደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች የዕለት ሽያጭ ገቢ ግምት መሰብሰቢያ የተለያዩ ቅጻቅጾች ህትመት እንዲታተምላቸው ተደርጓል፡፡
- አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ የታክስ ከፋዮች ትምህርት በሞጁል ዝግጅት ድጋፍ በጠየቁት መሰረት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

- ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የገቢዎች ቢሮ የታክስ ዕዳ ክትትል ማድረጊያ እንዲፈቀድላቸው በጠየቁት መሰረት እንዲሰጣቸው እና በሲስተሙ አጠቃቀም ዙሪያም ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ የተሻሻው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 283/2014 በማውጣት የቅድመ ዝግጅት ሥራ አጠናቀው ዋናውን የምዝገባ ሰርተፍኬት አትሞ ለግብር ከፋዮች ለመስጠት ፈቃድ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡
- ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከግል ድርጅቶች የሚሰበሰበው የቤት ኪራይ ገቢ ግብር እና ሌሎች ታክሶች አሰባሰብ የቀረበ መነሻ የጥናት ሰነድ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ በተጠየቁት መሠረት የላኩትን መረጃ በማደራጀት ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡
- የታክስ መረጃ ለማጥራት የተዘጋጀ መርሀ ግብርና ማመሳከሪያ ሰነድ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 2016 የገቢ ዕቅድን ለማሳካት ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ የተላከውን ሰነድ በመነሻነት ተጠቅመው የራሳቸውን አዘጋጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ተልኮላቸዋል፡፡
- ከቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ለደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ክልላዊ መንግስት የገቢ ቢሮዎች የገቢ ትልልፍ መረጃ የማጥራት ሥራን በመደገፍ የታየው ልዩነት እንዲከፈላቸው ተደርጓል፡፡
- የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ከተለያዩ ከክልሉ ተቋማት የተወጣጡ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ካፒታል ጌይን ገቢ አሰባሰብ ስርዓት ዙሪያ ልምድ እንዲያገኙ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በአዲስ አበባ እና በሌሎች ክልሎች ስራ ላይ ለተሰማሩ የትግራይ ክልል ታክስ ከፋዮች ታክስ የሚከፍሉበትና የተለያዩ አገልግሎት የሚያገኙበት አሰራር እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

❖ **የታክስ ስርዓትን ከማጣጣም አንጻር የተሰሩ ሌሎች ስራዎች**

- በፌዴራል የወጡ የታክስ ህጎች በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የገቢ ተቋማት ተጣጥመው እንዲወጡ በሪፖርት ጊዜው 3 ክልሎች የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እንዲሁም አፋር እና ሀረሪ 8 መመሪያዎች እንዲያወጡ ተደርጓል፡፡
- ከፌደራል የልማት ድርጅቶች ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀጽ 96 መሰረት የፌደራል ስለመሆኑ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡
- በወጥነት መተግበር የሚገባቸው በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና በተቋማችን የወጡ 42 ሰርኩላሮች በወጥነት እንዲፈፀሙ ተላልፏል፡፡
- የፌደራል ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በየክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ገቢ ተቋማት የስራ ኃላፊዎች የተሳተፉበት በ5 አጀንዳች (የግለሰብ ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አስተዳደር ሪቂቀ መመሪያ፣ የገቢ እቅድ አፈጻጸም (2 ጊዜ) ፣ ቅንጅታዊ የስምምነት ሰነድ አፈጻጸም እና መረጃ ማጥራት) ዙሪያ (zoom) ውይይት ተደርጓል ችግሮች የሚፈቱበት አቅጣጫ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡
- ከታክስ ደረሠኝ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን ለይተው መፍትሄ ለመስጠት ገቢዎች ከፌዴራል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የኦሮሚያ የገቢ ተቋማት የተቋቋመ የባለሙያዎች ቡድን ጥናት እየደረገ ይገኛል፡፡

- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ገቢዎች ባለሥልጣን ጥያቄ መነሻነት የማዕድን ገቢ ባለቤትነት በሚመለከት አነስተኛና መካከለኛ-አነስተኛ ለክልሎች እንዲሆን ከፍተኛው ደግሞ ለፌዴራል እንዲሆን በህገ መንግስቱ መሰረት ውሳኔ ተላልፏል፡፡
- ኦሮሚያ እና ሀረሪ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ቢሮ ከደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች የሚሰበሰበው የቁርጥ ግብር አወሳሰን በሲግታስ ሲስተም አማካኝነት እንዲሆን ለተዘረጋው አሰራር ትግበራ የሚያግዝ የአሰራር ማንዋል ተዘጋጅቶ ተልኮላቸዋል፡፡
- ከቀጥተኛ ታክሶች የሚሰበሰበውን የጋራ ገቢ ለማከፋፋል እንደማከፋፈያ መስፈርት ጥቅም ላይ የሚውለው በታክስ ከፋዮች የሚቀርብ የሠራተኛ ወጪ ማስታወቂያን በተመለከተ ለፌዴራል ቅ/ጽ/ቤቶች ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡
- መስከረም 04 እና 05 የፌዴራል፣ የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ገቢ ተቋማት እንዲሁም ህዳር 18 እና 19 ቀን 2015 ዓ.ም የገቢ፣ የፋይናንስ፣ የፕላን እና የሌሎች ዘርፎች የጋራ 02 የውይይት መድረኮች ተካሄደዋል፡፡ እንዲሁም በመደረኮች የተነሱ ጉዳዮች እንዲፈቱ ኮሚቴ እንዲቋቋምና ወደስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡
- የክልሎችና የፌደራል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተቀናጅተው የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድን ሲዳማ እና ለደቡብ ምዕራብ ክልሎች ከሀዋሳ እና ከጅማ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲፈራረሙ ተደርጓል፡፡
- የፌደራል ታክስ ከፋዮች የሆኑ ድርጅቶች ላይ በክልሎች የሚደረጉ ጫናዎች በተመለከተ የቀረቡ ቅሬታዎችን እንዲፈቱ ለማድረግ ለኦሮሚያ፣ ለደቡብ ምዕራብ ለጋምቤላ እና ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የተፈጠሩትን ችግሮች እንዲፈቱ ጥሪት ተደርጓል፡፡
- ለሶማሌ ክልል አንድ የባለሙያዎች ቡድን በአካል ወደ ክልሉ ገቢዎች ቢሮ በመገኘት የቢሮውን የታክስ አስተዳደር (የቢሮውን፣ የዞኖች፣ የወረዳዎች እና የከፍተኛ ታክስ ከፋይ ቅ/ጽ/ቤት መዋቅር እና የእነዚህ የስራ መደብ/ manning በተመለከተ የተዘጋጁ 5 ሰነዶች ለክልሉ ተልኮ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡
- ለድሬዳዋ፣ ለሀረሪ፣ ለኦሮሚያ እና ለአዲስ አበባ የገቢ ተቋማት በአካል በመገኘት ችግሮችን በመለየት በሚፈቱበት አግባብ ዙሪያ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ሪፖርትም ለሁሉም ተልኳል፡፡
- ከማዕድን፣ ጋዝ ፔትሮልየም የሚገኝ የታክስ ገቢን ከመሰብሰብ አንጻር ያለውን የአሰራር ችግር ለመፍታት የሚያስችል የውሳኔ ሀሳብ ለከፍተኛ አመራር ቀርቦ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤታችን የሀገራችን የ10 ዓመት የታክስ ገቢ አሰባሰብ አፈጻጸም ውጤታማነት በተመለከተ የተጠናው የጥናት ሰነድ ለግብዓትነት እንዲጠቀሙ ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተደዳሮች ተልኳል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤታችን የሀገራችን በአገር አቀፍ ደረጃ የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ግምገማ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የተጠናው የጥናት ሰነድ ለግብዓትነት እንዲጠቀሙ ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተደዳሮች ተልኳል፡፡
- የኦሮሚያ እና አማራ ክልል ገቢዎች የገጠር መሬት አጠቃቀምና ግብርና ገቢ ግብር አዋጅ መሻሻያ ያዘጋጁት ድራፍት ሰነድ ላይ ውይይት ተደርጎ የተጣጣመ አዋጅ እንዲወጣ

እንዲያግዝ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ እና ግብርና ገቢ ግብር ረቂቅ ሞዴል እንዲሆናቸውና የራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ለክልሎች ገቢ ተቋማት እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

## 2.6 የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ክትትል ሥራዎች ማሻሻል አፈጻጸም

የሥነ-ምግባር ሞራል ዕሴቶች ስልጠና የተሰጣቸው ሠራተኞች ብዛት ለ 5,763 (ወ 2,995፣ ሴ 2,768) ሠራተኞች በዲጂታል የሀብት ምዝገባ (DARS) አሰራር፣ በመንግስት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም፤ የስራ ላይ ስነ-ምግባር፣ በጥቆማ ምንነትና አቀራረብ፣ በሥነ-ምግባር ፅንሰ ሀሳብ እና ሞራል ዕሴቶች፣ በሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 136/2010 እና በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ 155/2000፣ በሥነ-ምግባር ችግሮችና ሙስና፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ በአመራር ሰጪነት ጥበብ፣ በሚስተዋሉ የሙስና አዝማሚያዎች፣ ወዘተ ርዕሶች ዙሪያ ለአመራሮች እና ለሠራተኞች እንዲሁም ለግብር ከፋዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በተለያዩ 82 ርዕሶች ማለትም በሥነ-ምግባር ፅነሰ ሀሳብ፣ በሀብት ምዝገባ አስፈላጊነት፣ በሙስና ጽንሰ ሀሳብ፣ በሙስና መገለጫዎች፣ ሙስና በሚያስከትላቸው ጉዳቶች፣ በሙስና ወንጀሎች፣ በጥቆማ አቀራረብ ወዘተ ዙሪያ የተዘጋጁ ብሮሽሮች ከ6184 በላይ ኮፒ ለአመራሮች እና ለሠራተኞች እንዲሁም ለግብር ከፋዮች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡ በሙስና አስከፊነት፣ በጥቅም ግጭትና ማስወገጃ ስልቶች፣ በሞራል ዕሴቶች፣ የፀረ-ሙስና ትግል ወዘተ በሚሉ ርዕሶች የተዘጋጁ መልዕክቶች ለ 3980 ተከታዮች በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ እና በቴሌግራም እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

ሙስና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ተገልጋዮች እና ሠራተኞች ጥቆማዎችን ማቅረብ የሚችሉበትን የጥቆማ መስጫ ሳጥኖች፣ የጥቆማ ማቅረቢያ ቅፃ ቅፆች፣ የቢሮ ስልኮች፣ የቴሌግራም ገፆች፣ ኢሜይል፣ ኤሌክትሮኒክ የድምፅ አስተያየት/ጥቆማ መስጫ መሳሪያ/ሳጥን ግልፅና አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ በማስቀመጥና የማስተዋወቅ ሥራ ተሰርቷል፤

በበጀት ዓመቱ ሀብት ማስመዝገብ ከሚጠበቅባቸው 4744 አመራሮች እና ሠራተኞች ውስጥ 2232 (983 ወ፣ 1249 ሴ) አመራሮች እና ሠራተኞች በዲጅታል ሲስተም አማካኝነት ሃብት ምዝገባ እንዲያስመዘግቡ የይለፍ ቃል ተሰጥቷቸው በማስመዝገብ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ 107 (71 ወ፣ 36 ሴ) ሠራተኞች የአገልግሎት ማቋረጥ ሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲያከናውኑ በማድረግ የክሊራንስ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ የውስጥ ኦዲት ግኝቶችን በስጋት ደረጃቸውና ሊያስከትሉት በሚችሉት ጉዳት በመለየትና ቅደም ተከተል በመስጠት በትኩረት ተሰጥቶ በ 54 ግኝቶች ላይ ክትትል ተደርጓል፡፡

በዋና መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተለያዩ የስራ ክፍሎች በ120 የአሰራረ ክፍተቶች ላይ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 116 ወይም 97 በመቶ አሠራሮች ላይ የሚስተዋሉ የህግና የአሠራር ክፍተቶችን በዳሰሳ ጥናት በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ 2014 በጀት ዓመት በተለያዩ የስራ ክፍሎች በተካሄዱ 10 እና አዲስ በተጠኑ 35 ጥናቶች መሠረት በቀረቡ የመፍትሄ እርምጃዎች መሠረት የተወሰዱ የማስተካከያና የእርምት እርምጃዎችን ክትትል ተደርጓል፡፡ ያስገኟቸው ፋይዳዎችም ለመዳሰስ ተችሏል፡፡ በተቋሙ የኤሌክትሪኒክስ ታክስ ክፍያ አሰራር በተስተዋሉ ክፍተቶች ላይ የአሰራር ስርዓት የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ተላልፏል፡፡

በቀረቡ ጥቆማዎች እና በተደረጉ የክትትል ሥራዎች የተወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች አፈጻጸምን በተመለከተ 2 (1 ወ፣ 1 ሴ) ሠራተኛ ከተቋሙ ከስራ እንድትሰናበት ተደርጓል፣ 3 (2 ወ፣ 1 ሴ) ሠራተኛ ከደረጃና ደሞዝ ዝቅ በማድረግ ተቀጥቷል፣ 5 (3 ወ፣ 2 ሴ) ሠራተኞች በደሞዝ ተቀጥተዋል፣ 9 (8 ወ፣ 1 ሴ) ሠራተኞች በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተቀጥተዋል፣ 6 (4 ወ፣ 2 ሴ) ሠራኞች በቃል ማስጠንቀቂያ ተቀጥተዋል፣ 6 ሠራተኞች የሥነ-ምግባር ሁኔታቸው አጠራጣሪ ሆኖ በመገኘቱ በሠራተኞች አስተዳደር ደንብ መሰረት የተጋላጭነት ስጋት ደረጃ ዝቅ ወዳሉ ክፍሎች እንዲዛወሩ የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ 3ቱ ተፈፃሚ ተደርጓል:: እንዲሁም 6 ጉዳዮች የወንጀል ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ወንጀል የመመርመር ስልጣን ላላቸው አካላት ተላልፈዋል::

በዋና መ/ቤት የተሽከርካሪ ስምሪትና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንደወሰድ ለስራ ክፍሉ ተላልፏል:: የ 40 አዲስ ተቀጣሪዎችን የሥነ-ምግባር ሁኔታ ወደ ስራ ቦታቸው ሄዶ በማጣራት ለሚመለከተው ክፍል የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል::

አንድ የተጭበረበረ የሥራ ልምድ ማስረጃ በማቅረብ፣ አንድ ተወዳዳሪ ደግሞ ከመቀጠሩ በፊት አላግባብ የተቋሙን ንብረት በመገልገል በድምሩ 2 ዕጩ ተወደዳሪዎች የቅጥር ሂደቱ እንዲቋረጥ ተደርጓል::

የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ ክንውን በሀሰተኛ የህክምና ማስረጃ የቀረበን የደሞዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄን በማስቆም/እንዲመክን በማድረግ ብር 44,924.00 ማዳን ተችሏል:: የውሎ ገብ አበል አከፋፈል ሥርዓት ላይ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ግኝት መሠረት የውሎ ገብ አበል ሊከፈል በማይገባ የሥራ መደብ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች የተከፈል አበል ብር 13,838.00 ወደ መንግስት ካዝና እንዲመለስ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ሥራ ተከናውኗል:: በዕቃ ግዥ ጨረታ ላይ የተስተዋለን የአሰራር ክፍተት በጥናት በመለየት በግኝቶቹ ላይ ከሚመለከተው ኃላፊዎችና ሥራ ክፍሎች ጋር ውይይት በማድረግ ህጉን ወይም የግዥ መመሪያ ሳይከተል ተገዝተው ቅ/ጽ/ቤት ንብረት ክፍል የገቡ ንብረቶችን በመለየት ተመላሽ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በዚህም ምክንያት ብር 40,579.78 የሚያወጣ ንብረት ተመላሽ ተደርጓል:: ሌሎች ጉዳዮች በሂደት ላይ ይገኛል::

የተለዩና የተተነተኑ ስጋቶች ብዛት በዋና መ/ቤት 12 አሰራሮች ላይ የስጋት አመላካቾች ተለይተዋል፤ የስጋት ደረጃቸውን ለመተንተን ስራዎች የተጀመሩ ሲሆን በታክስ ኦዲት አሰራር ላይ ለማከናወን የዳሰሳ ጥናት ተጀምሯል:: በመካከለኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት 7 የሥራ ሂደቶችን በከፍተኛ የስጋት ደረጃነት ተለይተዋል:: በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ7 የስራ ክፍል አሰራሮች ማለትም በታክስ ኦዲት፣ በታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት፣ በኢንቨስቲጌሽን ኦዲት፣ በታክስ ስሌት፣ በታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣ በታክስ ዕዳ ክትትል እና በሪከርድ ስራ አመራር አሰራሮች ላይ የስጋት ትንተና ተከናውኖ የመከላከያ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ለስጋት ባለቤቶች የማስተላለፍ ስራ ተከናውኗል::

## 2.7 የሴቶችና ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሻሻል አፈጻጸም

የሴት ሰራተኞችን የመፈጸም፣ የመወሰንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ ለዋናው መ/ቤት እንዲሁም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለ1739 ሴት አመራሮችና ሰራተኞች በአስተሳሰብ ለውጥ፣ በራስ መተማመን፣ በመግባባት ችሎታ እና በደንበኞች አያያዝ ዙሪያ ስልጥና ለመሰጠት ታቅዶ ለ2310

ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት ለሚገኙ 144 (ሴት 83 እና ወንድ 61) ወጣት ሰራተኞች በአስተሳሰብ ለውጥ፣ በደንበኞች አያያዝና የስራ ላይ ስነምግባር ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዋናው መ/ቤት እና አዲስ አበባ ከሚገኙ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተውጣጡ ሴት 134 ወንድ 94 በድምሩ ለ228 ወጣቶች ለታክስ ያላቸው ሚና ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በመጡ ሙሁራን ውይይትና እና በህይወት ክህሎት ዙርያ እንዲሁም መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት ለሚገኙ 90 ሴት እና 80 ወንድ በድምሩ 170 ወጣት ሰራተኞች በአስተሳሰብ ለውጥና በስሜት ብልህነት ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተቋሙ ለሚገኙ 214 ሴት አመራሮች (Ethical Leadership, Decision Making, Problem Solving & Team Work) ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ጾታ፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና ወጣቶች ጉዳዮች የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ለዚሁም እንዲረዳ ለ30 የዋናው መ/ቤት እና በአዲስ አበባ ለሚገኙ አምስቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የዕቅድ፣ የሰው ሀብት እና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቡድን ተጠሪዎች በአካል ጉዳተኛ ጉዳይ በዕቅድ አካቶ ከመስራት አኳያ የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በቅጥር ወቅት የሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶችም አገልግሎት ጠይቀው ለሚመጡ አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

በዋናው መ/ቤት የሚገኘው የሴቶች ፎረም አዲስ አባል ተመርጦ ከአባላቶቹ ጋር ቀጣይ ስለሚኖራቸው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ ውይይት የተደረገና በፎረም 50 ተማሪዎችን የማስተማር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በተቋሙ ከኤች አይቪ ፈንድ ድጋፍ ተደርጎላቸው የሚማሩ ህፃናት ብዛት 76 ናቸው፡፡ እንዲሁም በዋናው መ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የህጻናት ማቆያ ላይ አገልግሎት የሚያገኙ ህፃናት በ9 ህጻናት ማቆያ ማዕከል ውስጥ 203 ህጻናት አገልግሎት እያገኙ ይገኛሉ፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ47 ጊዜ የተከበረው አለማቀፍ የሴቶች ቀን የዋናው መ/ቤትና አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች 120 ሠራተኞች በተገኙበት አመራር ላይ ያሉ ሴቶች ልምዳቸውን በማካፈል እና በተለያዩ ዝግጅቶች በዓሉ ተከብሯል፡፡ በሀገር አቀፍ ስፖርት ከሁሉም ፌዴራል መስርያ ቤቶች ለሚደረገው ውድድር ተቋሙን በመወከል፣ በእግር ኳስ፣ በሩጫ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ እና በቼዝ ተቋሙን በመወከል ቅደመ ዝግጅት በማድረግ ውድድሩ ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ በጠረጴዛ ቴኒስ ሴት ተወዳዳሮች በሁለተኛነት ደረጃ ውድድሩን አጠናቀዋል፡፡ በሴቶች ሩጫ የሁለተኛነት ደረጃ አግኝተው አጠናቀዋል፡፡

የኤች.አይ. ቪ. መከላከልና ድጋፍ አፈጻጸምን አጠናክሮ በመተግበር ለ76 ሰራተኞች በአካል የስነ ልቦና የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በኤድስ ፈንድ የሚረዱ 20 የተቋሙ የሰራተኛ ልጆችና ከቦሌ ክ/ከተማ የተቀበላቸው ተማሪዎች ያሉበት የትምህርት መረጃ፣ የጤና፣ የማህበራዊ ሁኔታ በስልክና በአካል ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የትምህርት መረጃ ተደራጅቷል፡፡ ለ779 ሰራተኞች (ለ312 ወንድና ለ467 ሴት) በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፤ የምክር አገልግሎት ያገኙ ሰራተኞች በቁጥር ዕቅድ 68 ክንውን 76 ወይም 111.76 በመቶ ነው፡፡

የተለያዩ ኃላፊነቶችን ከመወጣት አንጻር 140 በጎ ፈቃድ ሰራተኞች ደም ለግሰዋል፣ በሀገር አቀፍ ስፖርት ለሁሉም ከሁሉም ፌዴራል መስርያ ቤቶች ለሚደረገው ውድድር ተቋሙን በመወከል፣በእግር ኳስ፣ በሩጫ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ እና በቼዝ ተቋሙን በመወከል ቅደመ ዝግጅት በማድረግ ውድድሩ ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ:: በጠረጴዛ ቴኒስ ሴት ተወዳዳዎች በሁለተኛነት ደረጃ አጠናቀዋል::በሴቶች ሩጫ የሁለተኛነት ደረጃ አግኝተው አጠናቀዋል::

## 2.8 የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ማሻሻል አፈጻጸም

- ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 ድረስ ላሉ ሰራተኞች የአዲስ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ ለ1,491 የተቋሙ ሠራተኞች በ3,475,521.00 ብር ተገዝቶ ለእያንዳንዳቸው የ50 ኪሎ ጤፍ ድጋፍ በተቋሙ በኩል ተደርጓል::
- ለመሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅት ከዋናው መ/ቤት ሠራተኞች እና አመራሮች የተለገሰ ግምታቸው 18 ሺህ 535 ብር የሚያወጡ የትምህርት መሣሪያ፣ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ እና የተለያዩ አልባሳት ዕርዳታ ተበርክቷል::
- ለዋናው መ/ቤት 95 ሠራተኞች የትምህርት መሳሪያ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ሰራተኞቹ መቸገራቸውን ገልጸው እንዲቀርብላቸው በጠየቁት መሰረት 1920 ደብተሮችን ከአስመጪዎች በማምጣት በዝቅተኛ ዋጋ በማከፋፈል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል::
- በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ቦረና ዞንና አካባቢው በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ለተጎዱ አካባቢዎች በማኔጅመንት ውሳኔ መሰረት የከብት መኖ ድርቆሽ ብዛት 15,000 ቦንዳ /እስር/ እና የነጭ ዱቄት ብዛት ባለ 25 ኪ.ግ 1700 በድምሩ የብር መጠን 10,940,500.00 (አስር ሚሊየን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ አምስት መቶ ብር) የሚያወጣ ድጋፍ ተደርጓል::
- በኤች.አይ. ቪ ቫይረስ በደማቸው ላለ እና በቫይረሱ ምክንያት ወላጅ እና አሳዳጊያቸውን ላጡ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለ4 ሰራተኞችና ለ2 ህጻናት በድምሩ ለ6 ተረጂዎች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል::
- በቫይረሱ ለተያዙ ድጋፍና እንክብካቤ ለሚደረግላቸው 19 ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው፣ ከቦሌ ክ/ከተማ ለተቀበላቸው 8 ህጻናት በአጠቃላይ ለ27 ተረጂዎች አስራ ሁለት ወራት የተደረገ የድጋፍ ገንዘብ ክፍያ ብር 158,400.00 ሲሆን ከ12 ቅ/ጽ/ቤትች ለተረጂዎች የተደረገ ቋሚ ድጋፍ 603,100.00 ከኤድስ ፈንድ ወጭ ሆኖ ተከፍሏል::
- በአጠቃላይ ለ83 ህፃናት እና ለ33 ሰራተኞች በድምሩ ለ116 ተረጂዎች 761,500.00 ወጪ ተደርጓል::
- ቋሚ ያልሆነ ድጋፍ በምዕራብ እና በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለተረጂዎች አዲስ ዓመት መዋያና ለተማሪዎች የት/ቤት ወጪ 30,000.00 ድጋፍ ተደርጓል:: ለተረጂዎች ተጨማሪ ድጋፍና ለተማሪዎች የት/ቤት ቁሳቁስ እና አልባሳት ግዥ 126,820.00 በድምሩ 156,820.00 ወጪ ተደርጓል::
- ለ105 ሰራተኞች በአካል የስነ ልቦና የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ተሰጥቷል::

- በኤድስ ፈንድ የሚረዱ 20 የተቋሙ የሰራተኛ ልጆችና ከቦሌ ክ/ከተማ የተቀበላቸው ተማሪዎች ያሉበት የትምህርት መረጃ፣ የጤና፣ የማህበራዊ ሁኔታ በስልክና በአካል ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የትምህርት መረጃ ተደራጅቷል፡፡
- ለ779 ሰራተኞች (ለ312 ወንድና ለ467 ሴት) በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤት በኤች አይቪ ኤድስ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡፡
- የሁለት ዓመታት አጠቃላይ የኤድስ ፈንድ የስራ አፈጻጸም በዋና መ/ቤት እና በመካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት በሚገኙ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጓል፡፡
- በበጀት ዓመቱ ለ14 ተረጂዎች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- በዋና መ/ቤት በቫይረሱ ለተያዙ ድጋፍና እንክብካቤ ለሚደረግላቸው 19 ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው፣ ከቦሌ ክ/ከተማ ለተቀበላቸው 8 ህፃናት፣ በአጠቃላይ ለ27 ተረጂዎች የተደረገ የድጋፍ ገንዘብ ክፍያ ብር 209,700.00 ከኤድስ ፈንድ ወጭ ሆኖ ተከፍሏል፡፡
- ከ12 ቅ/ጽ/ቤቶች በዓመት ውስጥ ለተረጂዎች የተደረገ ቋሚ ድጋፍ 838,300.00 በአጠቃላይ በዓመት ውስጥ ለ86 ህፃናት እና ለ33 ሰራተኞች በድምሩ ለ119 ተረጂዎች 1,048,000.00 ቋሚ ድጋፍ ወጪ ተደርጓል፡፡ ለተረጂዎች ተጨማሪ ድጋፍ፣ ለተማሪዎች የት/ቤት ቁሳቁስ፣ አልባሳት ግዥ፣ ህክምና እና የበዓላት መዋያ እና ብድር 203,611.00 ቋሚ ያልሆነ ድጋፍ ወጪ ተደርጓል፡፡ ከዋና መ/ቤት ከሰራተኛ የተሰበሰበ ብር 377,841.11 እና ከ12 ቅ/ጽ/ቤቶች ከሰራተኞች ደመወዝ 1,071,644.74 በአማካይ በድምሩ 1,449,485.85 ገቢ መሰብሰቡ ክትትል ተደርጓል፡፡
- በአመት ውስጥ ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ ብር 40.5 ሚሊዮን ነው፡፡
- አረንጓዴ አሻራ /ችግኝ መትከል በሁለቱም ተቋማት በጋራ 160 ሺ ችግኝ ተተክሏል፡፡
- ለአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ በጋራ ሁለቱም ተቋም በወሰኑት መሰረት ለ1000 ተማሪዎች ለመማሪያ የሚውል ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በግንቦት ወር ሁለቱ ተቋማት በቀረበው ፕሮፖዛል በገቢዎች ሚንስተር በበጀት ጥሬ ገንዘብ አዲስ አበባ ላይ በ6 ሚሊየን፣ ከአዲስ አበባ ውጪ በተመረጡ ክልሎች 6 ሚሊየን ብር (አዲስ አበባ ላይ ለ5 አባወራ/እማወራ፣ በተመረጡ ክልሎች 5 አባወራ/እማወራ ቤት የማደስ ስራ ተከናውኗል፡፡

# ክፍል ሦስት

## 3 በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና

### 3.1 ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ስርዓትን የማጎልበት ስራዎች አፈጻጸም

#### 3.1.1 የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልዕቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም

**➲ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ አፈጻጸም**

በበጀት ዓመቱ የወጡ የህግ ማዕቀፎች እና የአሰራር ስርዓቶች አፈጻጸም፡፡

- የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ(ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር 520/2014፣
- ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011 የማሻሻያ ሀሳብ በማቅረብ መመሪያው ተሸሽሏል፡፡
- የክፍያ ስምምነት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 179/2015
- የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 180/2015፣
- የታክስ ከፋዮች ምዝገባና ስረዛ የአሰራር ማንዋል የማሻሻልና ማንዋሉ ተግባራዊ ከተደረገበት ወዲህ የተቀረጹ ከምዝገባና ስረዛ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ሰርኩላሮች በማንዋሉ የማካተትና ውቅታዊ በማድረግ ለቅ/ጽ/ቤቶች ለመላክ ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡
- የሪከርድ ስራ አመራር የአሰራር ማንዋል፡፡
- የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ አሰራር ስርዓት ማንዋል ፀድቆ ለቅ/ጽ/ቤቶች ለአፈጻጸም ተላልፏል፡፡
- የአገልግሎት ኦዲት ማንዋል የቅ/ጽ/ቤቶች ግብዓት ታክሎበት ለአፈጻጸም ተላልፏል፡፡
- ኢ-ፋይል ያደረጉና ዝርዝር ሰነድ ቀርቦ የሚረጋገጥ ስራ ለመስራት የሚያስችል ማንዋል የቴሌ ብር ማስፈጸሚያ ጋይድ ላይን ለአፈጻጸም ተላልፏል፡፡
- በዋናው መ/ቤት የወጭና ገቢ እንዲሁም የማስታወሻዎች (Internal Memos) ስርጭት (MOR Letter Management System) አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡
- ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመሆን e-Registeration ፣ e- Clearance ቢዝነስ ፍላጎት እንዲሁም የንግድ ሚኒስቴር ዋና ምዝገባ መረጃ ከሲግታስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መረጃ ጋር የማቀናጀት (Interface) ፍላጎት መጠየቂያ ተዘጋጅቶና አስተያየት

ተሰጥቶበት የቴክኖሎጅ ማልማትና የማቀናጀት (Interface) የማድረግ ስራ በመከናወን ላይ ነው፡፡

- የጉዞ ወኪሎች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሲጠቀሙ ጠቅላላ የትኬት ሽያጭ በገቢ እንዲያዝና የትኬት ሽያጩ ገንዘብ የተለለፈው ከIATA የሚገኘው መረጃ መሠረት በወጪ በመያዝ አፈጻጸሙ በወጥነት ተግባራዊ እንዲሆን ስርዓት የተዘረጋ ሲሆን በጉዞ ወኪልነት ስራ የሚሰሩ ማህበራት በተዘረጋው ስርዓት መሰረት እንዲስተናገዱ ለአፈጻጸም ለቅ/ጽ/ቤቶች ተላልፏል፡፡
- ያላስታወቁ ታክስ ከፋዮች መመዝገቢያ፣ መከታተያ እና ሪፖርት ማቅረቢያ (Tracker Tool) ተቀርጾ ስራ ላይ ውሏል፡፡
- የአገልግሎት ኦዲት ማንዋል የቅ/ጽ/ቤቶች ግብዓት ታክሎበት ለአፈጻጸም ተላልፏል፡፡
- የታክስ ማስታወቂያ መረጃ ማደራጃ ቡድን የስራ ሚና ለማሻሻል ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከኢ ፋይሊንግ ጋር በተያያዘ መጣራት የሚገባቸውን አመላካች ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ተጨማሪ ስራ ስምሪት የሚሰጥ አሰራር ጸድቶ ለአፈጻጸም ለቅ/ጽ/ቤቶች ተላልፏል፡፡ የሰው ሀይል ስራ አመራርም የስራ ክፍሉ በስራ መዘርዝር እና የተፈላጊ ችሎታ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ተልኳል፡፡
- ኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት ምርት ተመላሽ ሲጠየቅ የሚስተናገድብት የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ለውይይትና ግብዓት ለማሰባሰብ የቅ/ጽ/ቤቶች እና ለዳይሬክቶሬቶች ተልኳል፡፡
- በገንዘብ ሚኒስቴር የወጣው መመሪያ ቁጥር 7/2011 እና መመሪያ ቁጥር 8/2011 ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ለማቅረብ የማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለውይይትና ግብዓት ለማሰባሰብ የቅ/ጽ/ቤቶች እና ለዳይሬክቶሬቶች ለመላክ ተዘጋጅቷል፡፡
- የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት መመሪያ ቁጥር 71/2004 ለማሻሻል ረቂቅ የተዘጋጀ ሲሆን ግብዓት ማሰባሰቢያ እየተዘጋጀ ነው፡፡

በሌላ በኩል በዕቅድ ተይዞ ያልተከናወነው የኤክሳይዝ ታክስ የቁጥጥር ኦዲት (Control Audit) ማስፈጸሚያ ማንዋል ማዘጋጀት በIMF Expert የሚሰጠው ስልጠና አለመጠናቀቁ እና አስስመንት ማንዋል ማዘጋጀት ነው፡፡ በታክስ አስተዳደር ወጥ አሰራር እንዲኖር ለቅ/ጽ/ቤቶችና ለክልል ታክስ ባለስልጣናት የተላለፉ አሰራርና ማብራሪያ በተመለከተ በበጀት ዓመቱ የተላለፉት እነደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ከገንዘብ ሚኒስቴር ተወስነው የተላኩ የታክስ ጉዳዮች ግልጽ የአፈጻጸም ስርዓት ተመላክቶ 42 ጉዳዮች ለአፈጻጸም ለቅ/ጽ/ቤቶች ተላልፏል፡፡
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ለተመላሽ አፈጻጸም የሚረዱ 39 የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶች ተዘጋጅቶ ለአፈጻጸም ለቅ/ጽ/ቤቶች ተላልፏል፡፡
- ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ከግብር ከፋዮች ወይም ከመ/ቤቶች 86 የማብራሪያ ጥያቄዎች ቀርቦ ከታክስ ማስታወቅ፣ ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተመላሽ እና ከገቢ ግብር እፍይታ ጋር የተያያዙ ከታክስ ህግና ከመመሪያዎች አንጻር ታይቶ ምላሽ (ማብራሪያ) ተሰጥቷል፡፡

### ➲ የተከናወኑ የጥናት ሥራዎች አፈጻጸም

ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ የታክስ አስተዳደር አፈጻጸም ክፍተቶችን በመለየት ለማረምና አሰራሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ከ8 ያላነሱ የሚከተሉት ጥናቶች ተካሂደዋል።

- **የታክስ ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ዳሰሳ ጥናት፣** የጥናቱ ዓላማ በተቀመጠው ስታንዳርድ /ቻርተር/ መሰረት አገልግሎት እየተሰጠ ስለመሆኑ መፈተሽ፤ ተገልጋዮች ያላቸውን የእርካታ ደረጃ ማወቅ እና በተገልጋዮች የሚነሱ ችግሮችን በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ በማሻሻል የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ የሚያስችል ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ነው። በዚሁ መሠረት ከሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በናሙና ከተመረጡ ታክስ ከፋዮች መረጃዎችን በመሰብሰብ የጥናት ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን የዳሰሳ ጥናት ውጤቱ የሚያሳየው ለታክስ ከፋዮች አገልግሎቱን በስታንዳርዱ ከመስጠት አንጻር በአማካይ አፈጻጸሙ በ2014 ከነበረበት 84.1 በመቶ በ2015 ወደ 86.1 በመቶ እና የተገልጋዮችን እርካታ ከማረጋገጥ አኳያ ደግሞ በ2014 ከነበረበት 79.5 በመቶ በ2015 ወደ 81.8 በመቶ ከፍ ያለ መሆኑን ነው።
  በሌላ በኩል አገልግሎት በስታንዳርዱ ከመስጠትና የተገልጋዩን እርካታ ከማሳደግ አንጻር አፈጻጸሙ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም በተለይ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት፣ በክሊራንስ አገልግሎት፣ በታክስ ተመላሽ አገልግሎት እና በኦዲት አገልግሎት ከአማካዩ (81.8 በመቶ) በታች እርካታ የተመዘገበባቸው በመሆኑ ተቋሙ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ እነዚህን አገልግሎቶች የበለጠ ለማሻሻል የሚያስችሉ ተከታታይ እርምጃዎችን መውሰድ የሚጠበቅበት መሆኑን የዳሰሳ ጥናቱ ያመለክታል።
- **የታክስ አሰባሰብ ውጤታማነት ግምገማ ጥናት/2005-2014/፣** የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ እንደ ሀገርና በፌደራል ደረጃ ያለውን የታክስ አሰባሰብ ውጤታማነት በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለቸው መስፈርቶች በመገምገም ችግሮቹን መለየትና ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ነው። በዚሁ መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎች ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ ከገቢዎች ሚኒስቴር የመረጃ ቋት እና ከመረጃ መረብ የሌሎች የአፍሪካ አገሮች አፈጻጸም በመሰብሰብና በመተንተን በሀገራችን ታክስ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት በቀጣይ ችግሮችን በመፍታት አፈጻጸሙን ለማሻሻል የሚረዳ ምክረ ሃሳብ የያዘ ጥናት ሰነድ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል።
- **የጉምሩክ የዋጋ ትመና ሥርዓት በአገር ውስጥ ታክስ አሰባሰብ ላይ ባሳደረው ተጽእኖ ዙሪያ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣** የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጉምሩክ ዋጋን ከዕቃው ዋጋ በታች አሳንሰው ወይም ከዕቃው ዋጋ በላይ አስበልጠው በሚያቀርቡ አስመጪዎች/ ግብር ከፋዮች ሳቢያ በአገር ውስጥ ታክስ አሰባሰብ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መቃኘት ነው። በዚሁ መሠረት ጥናቱ ተካሂዶ የጥናት ሰነዱ በቀጣይ አፈጻጸም ለማሻሻል እንዲረዳ ለሚኒስቴር ጽ/ቤትና ለጉምሩክ ኮሚሽን ቀርቧል።
- **የታክስ ማስታወቅ የህግ ተገዥነት ዳሰሳ ጥናት፣** የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የፌዴራል ታክስ ከፋዮች የታክስ ማስታወቅ የህግ ተገዥነት ያለበትን ደረጃ በመገምገም ችግሮቹን በመለየት

የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የፌዴራል ታክስ ከፋዮች የታክስ ማስታወቅ የህግ ተገዥነትን ደረጃ የሚያሳይ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ በቀጣይ የታክስ ማስታወቅና ክፍያ ህግ ተገዥነትን ለማሻሻል በግብዓነት ጥቅም ላይ እንዲውል ለሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ ለታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ እና ለታክስ ሥርዓት ዘርፍ የስራ ክፍሎች እንዲደረስ ተደርጓል፡፡

- *የጉምሩክ የዋስትና ሂሳቦች አስተዳደር አፈጻጸም ግምገማ ጥናት፣* የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የጉምሩክ የዋስትና ሂሳቦች አስተዳደር አፈጻጸም በመገምገም የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ችግሮቹ ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጭ የመፍትሔ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎችን ከጉምሩክ ዋናው መ/ቤት፣ ከተመረጡ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ከፋይናንስና ኢንሹራንስ ተቋማት በመሰብሰብና እና መረጃዎችን በመተንተን የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት የጥናቱ ሰነዱን በቀጣይ የአፈጻጸም ክፍተትን ለማሻሻል እንዲረዳ ለጉምሩክ ኮሚሽንና ሌሎች ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ቀርቧል፡፡
- *የደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳዳር ዳሰሳ ጥናት፣* የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጠቃላይ ደረሰኝ ከመፍቀድ ጀምሮ እስከ ማስወገድ ድረስ ያለውን አሰራር እና የሀሰተኛ ደረሰኝ ቁጥጥር ያለበትን ደረጃ በመገምገም ችግሮቹን መለየትና የመፍትሔ ሃሳብ ማመላከት ነው፡፡ በዚህም መሰረት መረጃዎች ከሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶችና ከተመረጡ ክልሎች መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን በደረሰኝ ዙሪያ ያሉ ዋና ዋና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ምክረ ሃሳብ የያዘ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለቀጣይ አፈጻጸም በግብዓትነት እንዲጠቀሙበት ለሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ ለዘርፎችና ለሚመለከታቻው የስራ ክፍሎች ሁሉ እንዲደረሳቸው ተደርጓል፡፡
- *የታክስ ሥርዓት መጣጣም ግምገማ ጥናት፣* የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሀገራችን የታክስ ስርዓት በፌዴራልና በክልሎች እንዲሁም በክልሎች መካከል ከታክስ ህግና ከታክስ አስተዳደር/ከታክስ ህግ አተገባበር/ አንጻር ሥርዓቱ እየተጣጣመ ስለመሆኑ በመገምገም ችግሮቹን በመለየት ችግሩቹን ለመቅረፍ የሚያስችል ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ሲሆን በዚሁ መሠረት መረጃዎች ከገቢዎች ሚኒስቴር እና ከክልሎች በመሰብሰብና በመተንተን በታክስ ሥርዓት መጣጣም ዙሪያ ያሉ ችግሮችን በመለየት ምክረ ሃሳብ በማካተት የጥናት ሰነዱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡
- *የሎተሪ ፈቃድና ቁጥጥር ሥራዎች አደረጃጃት ጥናት፣* የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የሎተሪ ወይም የዕድል ጨዋታ ሥራዎች ፈቃድና ቁጥጥር ሥራ ከሎተሪ አገልግሎት ሥራው ተነጥሎ ለገቢዎች ሚኒስቴር በመሰጠቱ የሎተሪ ሥራዎች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ሥራ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል የአደረጃጀት ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጥናቱ ተካሂዶ የአደረጃጃት ምክረ ሃሳብ ለታክስ ሥርዓት ዘርፍ ቀርቧል፡
- *የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ቁጥጥር ግምገማ ጥናት፣* የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመንግስት የተሰጡ የቀረጥ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ ስለመሆኑ በመገምገም ችግሮቹን በመለየት የመፍትሔ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎች ከተመረጡ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ከጉምሩክ ዋናው መ/ቤት እና ከመብቱ ተጠቃሚዎች

በመሰብሰብና በመተንተን ረቂቅ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት የቀረበ ሲሆን የጥናት ደረጃው 95 በመቶ ላይ ደርሷል።

## ➲ ለፍትህ አካላት የሚቀርቡ የፍትሀብሔር ጉዳዮች በመዝገብ የመርታት አቅምን ማሳደግ

**የግብር ይግባኝ ክርክር አፈጻጸም፡-** የ2015 በጀት ዓመት አጠቃላይ ሪፖርት የግብር ይግባኝ ክርክር አፈጻጸም በተመለከተ ከ2014 በጀት ዓመት ወደ 2015 በጀት ዓመት የዞሩ መዝገቦች ብዛት 228 ሲሆኑ በ2015 በጀት ዓመት አዲስ የመጡ መዝገቦች ብዛት 375 ናቸው። በ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ የግብር ይግባኝ ክርክር ላይ የነበሩ መዝገቦች ብዛት ሲታይ በግብር ይግባኝ ኮሚሽን 404 መዝገቦች፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት 118 መዝገቦች እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት 60 መዝገቦች፣ በሰበር ሰሚ ችሎት 21 መዝገቦች ሲሆኑ በጠቅላላው 603 የታክስ ክርክር መዝገቦች የነበሩ ሲሆን የገንዘብ መጠን 16,980,954,589.93 ነበር።

**በ2015 በጀት ዓመት አጠቃላይ እልባት የተሰጠባቸው የግብር ይግባኝ መዝገቦችን** በተመለከተ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን 222 መዝገቦች፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት 71 መዝገቦች እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት 52 መዝገቦች፣ በሰበር ሰሚ ችሎት 16 መዝገቦች ሲሆኑ በጠቅላላው 361 በክርክር እልባት ወይም ፍርድ የተሰጠባቸው ሲሆኑ አጠቃላይ የገንዘብ መጠኑ 8,385,999,842.13 ነው።

**በግብር ይግባኝ ክርክር የመርታት አቅም ምጣኔ፡-** በ2015 በጀት ዓመት ከተወሰኑት 361 የግብር ይግባኝ ክርክር መዝገቦች ውስጥ ለሚኒስቴሩ የተወሰኑ 277 የታክስ ክርክር መዝገቦች የብር መጠን 7,392,523,883.04 ነው። ለግብር ከፋዮች ደግሞ 56 መዝገቦች የገንዘብ መጠን 540,703,166.75 ነው። ወደ ስር የተመለሱ መዝገቦች 20 ሲሆኑ የገንዘብ መጠኑ 414,189,890.81 ነው።

በ2015 በጀት ዓመት ክርክር ተደርጎ ፍርድ የተሰጠባቸው 8 መዝገቦች የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ጉዳይ ሲሆኑ የግብር አወሳሰኑ የህግ ስህተት ያለበት ወይም ትርፉ ለካፒታል ማሳደጊያ ተደርጎ እያለ አስፈላጊው ሰነድ ባለመቅረቡ ብቻ በባለ አክሲዮኖች ላይ ግብር የተወሰነባቸው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በሚኒስቴሩ ግብር ውድቅ በማድረግ ፍርድ የሰጠ ስለሆነ ወደ ቀጣይ ፍርድ ቤትም ክርክር የማይደረግበት ጉዳይ ነው። እነዚህ መዝገቦች የያዙት የገንዘብ መጠን ብር 38,582,901.53 ነው። ስለሆነም የመርታት አቅም ምጣኔ በመዝገብ ብዛት 85 በመቶ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ 94 በመቶ ነው። ወደ ሚቀጥለው ጊዜ የዞረ መዝገብ ብዛት በዝርዝር ሲታይ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን 182 መዝገቦች፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት 47 መዝገቦች እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት 8 መዝገቦች፣ በሰበር ሰሚ ችሎት 5 መዝገቦች ሲሆኑ በጠቅላላው 242 ሲሆኑ የገንዘብ መጠናቸው 8,594,954,747.8 ነው።

**የቀጥታ ክስ ክርክር አፈጻጸም በተመለከተ፡-** በ2015 በጀት ዓመት በቀጥታ ክስ ክርክር ላይ የነበረ መዝገብ በተመለከተ ወደ 2015 በጀት ዓመት የዞረ መዝገብ ብዛት 51 ሲሆን የገንዘብ መጠኑ 137,607,522.00 ነው። በ2015 በጀት ዓመት አዲስ የመጣ መዝገብ ብዛት 66 ሲሆን የገንዘብ መጠን 680,307,257.29 ነው። በጠቅላላው በቀጥታ ክስ ክርክር ላይ የነበረ መዝገብ ብዛት 117 ሲሆን የገንዘብ መጠን 817,914,779.29 ነው።

**በቀጥታ ክስ ክርክር የመርታት አቅምን ማሻሻል በተመለከተ፡-** ከተወሰኑት 55 ቀጥታ ክስ ክርክር መዝገቦች ውስጥ ለሚኒስቴሩ የተወሰኑ 37 መዝገቦች ሲሆኑ የገንዘብ መጠን ደግሞ 238,967,722.35 ነው:: በሚኒስቴሩ ላይ የተወሰነ መዝገብ 15 ሲሆን የገንዘብ መጠኑ 234,315,372.90 ነው:: ወደ ስር የተመለሰ መዝገብ 3 ነው የገንዘብ መጠን የለውም፣ አንድ መዝገብ ለጊዜው የተዘጋ ነው:: የመርታት አቅም ምጣኔ በመዝገብ ብዛት 73 በመቶ ሲሆን በገንዘብ መጠን ደግሞ 51 በመቶ ነው:: ወደ ሚቀጥለው ወር የዞረ መዝገብ ብዛት 62 ሲሆን የገንዘብ መጠኑ 344,631,684.04 ነው::

**የህግ ረቂቅ፣ ምክርና አስተያየት በተመለከተ፡-** በ2015 በጀት ዓመት 7 ረቂቅ መመሪያዎች የተዘጋጁ ሲሆን፣ ከተዘጋጁት ረቂቅ መመሪያዎች 4 መመሪያዎች በበጀት ዓመቱ ጸድቆ ሥራ ላይ መዋል ጀምሯል:: 3ቱ በሂደት ላይ ነው:: እንዲሁም 7 ከባለድርሻ አካላት በቀረበው የህግ እና የመግባቢያ ስምምነት ረቂቅ ላይ የህግ አስተያየት ተሰጥቷል:: በ2015 በጀት ዓመት 64 የህግ አስተያየት ማብራሪያ ተጠይቆ ለ63ቱ አስተያየትና ማብራሪያ ጥያቄዎች መልስ ተሰጥቷል:: አፈጻጸሙ በመቶኛ 98.43 በመቶ ነው::

### 3.1.2 የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን የማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም

#### የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር አፈጻጸም

- 4000 ከአቅራቢው ድርጅት በሰራተኛ የመጣ ሜሞሪ የመረከብ ስራ ተሰርቷል::
- 201 ከሚሞሪ ላይ መረጃ ለማስነበብ ለግብር ከፋዮች ተሰጥተዋል::
- 188 ከሜሞሪ ላይ መረጃ አስነብበው የመለሱ ግብር ከፋዮች እንደገና የመረከብ ስራ ተሰርቷል::
- በአጠቃላይ በአመቱ ከአስራ ስድስት ዘርፎች 2848 መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ16 ዘርፎች 2848 /100%/ ከተመረጡት የገበያ ቦታዎች ተመሳሳይ የተገኙላቸው ከአራት እስከ ስድስት ናሙናዎችን ተመሳሳይ ያልተገኘውን አንድ ናሙና በአካል፣ በስልክና በዌብ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል::
- የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለጠየቁ 17,007 ግብር ከፋዮች ፈቃድ ተሰጥቷል::
- የደረሰኝ ማስወገድ አገልግሎት ለጠየቁ 2,487 ግብር ከፋዮች በሙሉ አገልግሎት አግኝተዋል::
- አምራች አከፋፋይ /ሽያጭ/መረጃ ከመሰብሰብ አንጻር ከ 6,655 ድርጅት ታቅዶ ከ 6,327 (95 በመቶ) ድርጅቶች የተሰበሰበ ሲሆን አፈጻጸሙን በመረጃ ለማሳየት 1,754192 መረጃ ተሰብስቧል::
- ከግብር ከፋዮች የግዢ መረጃ በመሰብሰብ ረገድ ከ 28,863 ድርጅቶች ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ 25,848 ድርጅቶች (89.5 በመቶ) 628,580 መረጃ ተሰብስቧል::
- ከመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤት ግዢ መረጃ ከመሰብሰብ አንጻር ከ344 መስሪያ ቤት ለመሰበሰብ ታቅዶ ከ292 (85 በመቶ) በመረጃ 44,026 መረጃ ተሰብስቧል::
- ከNGO ግዢ መረጃ መሰብሰብ በተመለከተ ከ 1,739 NGO የግዥ መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ 1,733(100%) መሰበሰብ ተችሏል::
- የሶስተኛ ወገን የግዢና ሽያጭ መረጃ በየወሩ እየሰበሰቡ ወደ መረጃ ቋት ማስገባትንና ተደራሽ ማድረግን በሚመለከት በበጀት አመቱ ውስጥ 2,416,108 መረጃ ወደ መረጃ ቋት ለማስገባት

ታቅዶ 2,414,281 (100%) በውስጥ ኢንኮደሮች ማስገባት የተቻለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ 5,499,942 መረጃ በመረጃ መረብ /online/ ተሰብስቧል። በድምሩ 7,914,223 የግዥና ሽያጭ መረጃ ወደ መረጃ ቋት ገብቷል።

- የመረጃ ጥራት ቁጥጥርን በተመለከተ በዋና መ/ቤት የተሰራውን ጨምሮ በ 5,579,121 መረጃዎች ላይ ለመስራት ታቅዶ 6,047,141 (108 በመቶ) ለመስራት የተቻለ ሲሆን በጥራት ቁጥጥር ወቅት ስህተት የተገኘባቸው 146,076 መረጃዎች ላይ ዕርማት/ማስተካከያ ማድረግ/ ድግግሞሽ መረጃን ማጥፋት/ ስራ ተሰርቷል።
- ከኮንስትራክሽን ድርጅቶች መረጃ ከመሰብሰብ አንጻር 226 ድርጅት የኮንስትራክሽን አገልግሎት ክፍያ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን የ 70 ድርጅቶች ለፌደራልና ለክልል ገቢዎች መረጃው ተደራጅቶና ተተንትኖ ተሰራጭቷል።
- ከ 32 ዩንቨርሲቲ የወጪ መጋራት መረጃ ተሰብስቧል።

ሰንጠረዥ 8 የውጭ ምንዛሪ ተፈቅዶ ማሽን ማስመጣት የጀመሩ አቅራቢዎች

| ተ. ቁ | አቅራቢ | ያስገቡትና መለያ ኮድ ተስጥቷቸው ለገበያ የቀረቡ | ለግብር ከፋይ ተደራሽ የሆኑ (የተሸጡ) |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንዶ | 1,050 | 1,050 |
| 2 | አይፖስ | 1,650 | 1,003 |
| 3 | ስኬት | 810 | 646 |
| 4 | አምባሰል | 2,750 | 1,964 |
| 5 | ሀሮን | 4,406 | 2,111 |
| 6 | ዲያንካ | 600 | 597 |
| 7 | ኢግልድ | 545 | 0 |
| 8 | ኦሜዳድ | 776 | 450 |
| 9 | ቢፍቱ አዱኛ | 114 | 65 |
| ድምር | | 12,701 | 7,886 |

- በተጨማሪ አምባሰል 1,716 ሀሮን 2,023 ማሽኖች አስገብተው ከጉምሩክ ለማውጣት በሂደት ላይ ሲሆን በአጠቃላይ 16,440 ማሽኖች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተዋል።

➲ **የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች አፈጻጸም**

- የቢዝነስ አመቺነትን ከመፍጠር አንጻር የተሸጡ የሽ/መ/መሳሪያዎች በሙሉ በ3 ቀናት ውስጥ መተከል ያለባቸው ሲሆን በበጀት አመቱ ከተሸጡ 5876 መሳሪያዎች ውስጥ 5739 ወይም 98 በመቶ በ3 ቀናት ሊተከሉ ችለዋል፣
- አመታዊ እድሳት ፈልገው ከገቡ 85080 ማሽኖች ውስጥ 84824 (100%) በ48 ሰዓት ውስጥ መታደስ ችለዋል፣
- የጥገና አገልግሎት ፈልገው ከገቡ 30191 ማሽኖች ውስጥ 29845 (99 በመቶ) በ48 ሰዓት ተጠግነው ወጥተዋል፣

➲ **ከውጭ ባለድርሻ አካላት አንጻር የተሰሩ ስራዎች**

- ከጉና ንግድ ስራዎች ወደ አምባሰል ንግድ ስራዎች በማዛወር በአፋር ክልል ተቋርጦ የነበረውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሽያጭና አገልግሎት በቦታው በመገኘት እንዲጀመር ተደርጓል::
- አዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የጠፉ ደረሰኞችን ሲስተም ላይ ስለሚመዘግቡበት ሁኔታ የስራ ላይ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ዩዘር ኔምና የይለፍ ቃል በመስጠት ራሳቸውን ችለው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል:: የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያን በሚመለከት ከሱዳን ለመጡ ልኡካን የልምድ ማካፈል ስራ ተሰርቷል::
- ኢንቮይስንና ሌሎች ቴክኖሎጂ ውጤቶችን በሚመለከት ተሞክሮ ለመውሰድ ከኢንሳ ጋር የውጭ ጉዞ ተደርጓል::
- ከኢቲዮ ቴሌኮም ጋር የኤምቱኤም ሲም ካርድ አስተዳደርን በሚመለከት ለ4 ጊዜ ያላነሱ ውይይቶች ተደርዋል::
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የቴክኖሎጂ ለውጥ ጋር ተያይዞ ለሚጠናው ጥናት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሶፍትዌር አቅራቢዎች የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብዓት ተሰብስቧል::

### ➲ የግብር ከፋዮች የታክስ ህግ ተገዥነትን ማሻሻል

የህግ ተገዥነትን ከማስፈን አንጻር በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጠንካራ የቁጥጥር ስራ በመስራት በበጀት አመቱ በ37509 ግብር ከፋዮች ላይ የቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ታቅዶ በ 38214 ላይ 102 በመቶ ቁጥጥር ማድረግ ተችሏል:: በተደረገው የቁጥጥር ስራም 1738 ግብር ከፋዮች ህግን ተላልፈው የተገኙ ሲሆን ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በተጨማሪ ቁጥጥሩ ማንዋል ደረሰኝንም ያካተተ ስለነበር ግኝት ከተገኘባቸው 1738 ግብር ከፋዮች ውስጥ 101(አንድ መቶ አንድ) ግብር ከፈዮች ማለትም የምስራቅ 37 ከአድራሻ ውጭ አሳትመው የሚጠቀሙ፣ ምዕራብ 8፣ መካከለኛ ግብር ከፋዮች 47፣ ሰሜን ምዕራብ 5፣ ኮምቦልቻ 2፣ ጅማ 1 በድምሩ 63 ግብር ከፋዮች ሳያስፈቅዱ አሳትመው የሚጠቀሙ የነበሩ ሲሆን የአዳማ 1 ግብር ከፋይ ፎርጅድ የማንዋል ደረሰኝ እያተመ የሚሸጥ ድርጅት በቁጥጥር ስር እንዲውል ተደርጎ ለሌሎች መማሪያ ይሆን ዘንድ በ ሚዲያ ጭምር ተላልፏል:: በዚህም በአጠቃላይ ብር 67,354,000.00 የቅጣት ውሳኔ ተላልፎ ብር 14,436,803.16 መሰብሰቡን የቅርንጫፎች መረጃ ያሳያል::

ሰንጠረዥ 9 ከሽመመ ቁጥጥር የተጣለና የተሰበሰበ መቀጫ

| ተ. ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | የተጣለ መቀጫ | የተሰበሰበ መቀጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 2,795,000.00 | 1,220,000.00 |
| 2 | መካከለኛ | 11,615,000.00 | 2,207,000.00 |
| 3 | ምሥራቅ | 23,604,000 | 5,885,227 |
| 4 | ምዕራብ | 8,585,000.00 | 563,000.00 |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 9,050,000 | 2,129,578.52 |
| 6 | አዳማ | 1,800,000.00 | 445,000.00 |
| 7 | ሀዋሳ | 2,445,000.00 | 269,497.64 |
| 8 | ባሕርዳር | 5,500,000.00 | 1,515,000.00 |
| 9 | ድሬዳዋ | 675,000.00 | 142,500.00 |

| ተ. ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | የተጣለ መቀጫ | የተሰበሰበ መቀጫ |
|---|---|---|---|
| 10 | ኮምቦልቻ | 1,085,000.00 | 45,000.00 |
| 11 | ጅማ | 200,000.00 | 15,000.00 |
| ድምር | | **67,354,000.00** | **14,436,803.16** |

- የ754 ድርጅት 870 የጠፉ ደረሰኞችን በማደራጀት በደብዳቤ ለሚመለከታቸው አካል ማለትም ለታክስ ማጭበርበር፣ ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡
- የጠፉ፣ የተቃጠሉና የተወገዱ 1753 የሽ/መ/መሳሪያ አገልግሎት እንዳይሰጡ በመስጋት እና ተጨማሪ ሽያጭ እንዳይከናወን END Command ሰርቨር ላይ የተቀመጠ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 1119 ኙ ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በአድራሻ ያልተገኙ እና የጠፋ ማሽኖች ተብለው ሪፖርት የተደረጉ ናቸው፡፡
- ማሽን መግዛት የሚጠበቅባቸውን ግ/ከፋዮች አዲስ ሽ/መ/መ ከማስገዛት አንጻር 2951 ታቅዶ 2877 ግ/ከፋዮችን /97.5 በመቶ ለማስገዛት/ ተችሏል፡፡

### ➲ የመረጃ ማጥራት ስራዎች አፈጻጸም

በData Quality Tool 19 Parameter በ12 ወሩ 45004 ችግሮች የማስተካከል ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የ12 ወሩ አፈጻጸም 92 በመቶ የደረሰ ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዩ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣ ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣ የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስ ህጎችን ማስከበር፣ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃትና በወቅቱ ለመሰብሰብ የተሟላ ጥራቱን የጠበቀና በአግባቡ የተደራጀ መረጃ አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል፡፡
- በመሆኑም በሲግታስ ስርዓት የሚገኝ የታክስ ከፋይ መረጃ በማጥራት የታክስ ከፋዩን ፋይል እንደ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ በመጠቀም ወደ ሲግታስ ያልገቡ እንዲገቡ በማድረግ ተቋሙ የተደራጀ፣የተሟላ፣ አስተማማኝና ጥራቱ የተጠበቀ የታክስ መረጃ እንዲኖረው እና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በተደራጀ ሁኔታ ሲከናወኑ እንደነበር እና የማይናቅ ውጤት እንደመጣ ይታወቃል፡፡
- በዚሁ መሰረት በጋት ደረጃ ተለይቶ በተከናወነ የመረጃ ማጥራት ስራ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ 96.9 በመቶ፣ መካከለኛ የስጋት ደረጃ 85 በመቶ፣ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ 50 በመቶ እና ስጋት ያልወጣላቸው 31 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ ሶስት እና ከሶስት አመት በላይ ያላስታወቁ 3122 ታክስ ከፋዮች መረጃ በማጥራት ወደዘላቂ ማቆያ ለማስገባት ታቅዶ 1991 ማስገባት የተቻለ ሲሆን የቀሩት እዳ፣ ደረሰኝ፣ ካሽ ሪጅስተር፣ በአንድ የታክስ አይነት በማስታወቃቸውና በመሳሰሉ ምክንያቶች ማስገባት አልተቻለም፡፡ በፋይል ያለ መረጃን ከሲስተም ጋር ማስታረቅን በተመለከተ

35,877 ከሲግታስ እንዲሰረዙ፣ 20,556 በሲስተም እንዲስተካከል፣ 24,954 ወደ ሲስተም የገባ፣ 14313 በፋይል ውስጥ ኖሮ በሲተም ውስጥ የሌለ መረጃ በግብር ከፋዩ እንዲመጣ ተደርጎ ተስተካክሏል:: በተመሳሳይ ከ250,000 በለይ unassessed declaration እንዲጠራ ተደርጓል::

- በአጠቃላይ የታክስ መረጃ ለማጥራት ሰፊ ርብርብ ቢደረግም አሁንም በመረጃ ማጥራት ዙርያ ቀሪ ያደሩ ስራዎች እና የጠሩ የታክስ መረጃዎች በቀጣይ ጥራታቸው ተጠብቆ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ስልት መቅረጽ የያስፈልጋል::

ሰንጠረዥ 10 የመረጃ ማጥራት ስራዎች አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ስትራቴጂካዊ ግብ | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም መነሻ | የ2015 በጀት ዓመት ዒላማ | የ12 ወር ክንውን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመረጃ አስተዳደር አፈጻጸምን ማሻሻል | የጠራ የግብር ከፋይ መረጃ በመቶኛ | 64 በመቶ | 90 በመቶ | 92 በመቶ |

### 3.1.3 የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም

#### ➲ የኤሌክትሮኒክስ ታክስ ስርዓት አጠቃቀምን ከማሳደግ አንጻር የተሰሩ ስራዎች

በኤሌክትሮኒክ ታክስ የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻን ከማሳደግ አንጻር የኤሌክትሮኒክ ማሳወቅ (E-Filling) አፈጻጸም ሲታይ በበጀት ዓመቱ የግብር ከፋይ የኢ-ፋይሊንግ ስልጠናን በተመለከተ 10,967 ታቅዶ 11,263 (103 በመቶ) የተሰጠ ሲሆን 8,212 ድርጅቶች የይለፍ ቃል (Passward) ወስደዋል:: የኢ-ፋይሊንግ ሽፋንን 82 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እስከ አሁን 40,842 ግብር ከፋዮች እያሳወቁ በመሆናቸው ሽፋኑን (93 በመቶ) ማድረስ ተችሏል:: ከግብር ከፋዮች ቁጥር 54,314 ውስጥ 10,204 ማለትም (4,204 ፈቃድ ያላወጡ፣ 757 የመዝጊያ ጥያቄ አቅርበው በሂደት ላይ ያሉ፣ 516 ንዑስ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (Sub TIN) ያላቸው እና 4,724 ከ3 ዓመት በላይ ያላስታወቁ በመሆናቸው ወደ ዘላቂ ማቆያ (Archive) የገቡ በኤሌክትሮኒክስ ታክስ ማስታወቅ ሥርዓት (E-filing) ስልጠና መስጠት የማይቻል በመሆኑ) ስልጠና እንዲወስዱ የማይጠበቁ መሆኑ ተለይቷል::

ሰንጠረዥ 11 የኢ-ፋይሊንግ ስልጠና እና የይለፍ ቃል አፈጻጸም

| ተ/ቁ | ቅ/ጽ/ቤት | የ12 ወራት ስልጠና | | | እስከ አሁን የሰለጠኑ | በዓመቱ የይለፍ ቃል የወሰዱ | እስከ አሁን የይለፍ ቃል የወሰዱና እያሳወቁ (እየተጠቀሙ) ያሉ ግብር ከፋዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | መቶኛ | | | |
| 1 | ከፍተኛ | 43 | 55 | 128 | 642 | | 641 |
| 2 | መካከለኛ | 4 | - | | 3,579 | | 3,516 |
| 3 | ምሥራቅ | 1,740 | 1,938 | 111 | 12,004 | 1,938 | 11,454 |
| 4 | ምዕራብ | 2,688 | 2,049 | 76 | 10,990 | 1,636 | 10,990 |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 1,200 | 1,495 | 125 | 8,047 | 1,522 | 7,387 |
| 6 | ባህርዳር | 2,175 | 2,519 | 116 | 2,519 | 2553 | 2,378 |
| 7 | ሐዋሳ | 900 | 925 | | 1,625 | 925 | 1,416 |
| 8 | አዳማ | 523 | 662 | 127 | 1,010 | 589 | 942 |
| 9 | ጅማ | 678 | 703 | 104 | 1,051 | 703 | 1,051 |
| 10 | ድሬዳዋ | 367 | 275 | 75 | 486 | 275 | 450 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 649 | 642 | 99 | 782 | 624 | 617 |

| ድምር | 10,967 | 11,263 | 103 | 42,735 | 10,765 | 40,842 |
|---|---|---|---|---|---|---|

ሰንጠረዥ 12 የኢ-ፋይሊንግ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ቅ/ጽ/ቤት | ጠቅላላ የግብር ከፋይ ቁጥር የነሃሴ ወር | አጠቃላይ በተለያየ ምክንያት ወደ ኢ-ፋይሊንግ ስርዓት መግባት የማይችሉ ግብር ከፋዮች ድምር | የኢ-ታክስ ሥልጠና መውሰድ የሚገባው የተጣራ ግብር ከፋይ | እስከአሁን ስልጠና የወሰዱ ግብር ከፋዮች ብዛት | ቀሪ ስልጠና መውሰድ የሚገባቸው እቅድ | እስከአሁን ወደ ስርዓቱ የገቡና እያስታወቁ ያሉ ግብር ከፋዮች ብዛት | የእስከአሁን ሽፋን በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 642 | 0 | 642 | 642 | 0 | 641 | 100 |
| 2 | መካከለኛ | 3877 | 293 | 3584 | 3579 | 5 | 3516 | 98 |
| 3 | ምሥራቅ | 14257 | 2069 | 12188 | 12004 | 184 | 11454 | 94 |
| 4 | ምዕራብ | 13319 | 2121 | 11198 | 10990 | 208 | 10990 | 98 |
| 5 | ሰሜን/ም | 10233 | 2162 | 8071 | 8047 | 24 | 7387 | 92 |
| 6 | ባህርዳር | 4000 | 1220 | 2780 | 2519 | 261 | 2378 | 86 |
| 7 | ሐዋሳ | 2249 | 522 | 1727 | 1625 | 102 | 1416 | 82 |
| 8 | አዳማ | 1364 | 238 | 1126 | 1010 | 116 | 942 | 84 |
| 9 | ጅማ | 2334 | 915 | 1419 | 1051 | 368 | 1051 | 74 |
| 10 | ድሬዳዋ | 658 | 118 | 540 | 486 | 54 | 450 | 83 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 1381 | 546 | 835 | 782 | 53 | 617 | 74 |
| ድምር | | 54,314 | 10,204 | 44,110 | 42,735 | 1,375 | 40,842 | 93 |

**የኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-payment) አፈጻጸምን በተመለከተ፦** 2015 በጀት ዓመት ታክስ በማሳወቅ ከከፈሉ 27,204 ታክስ ከፋዮች 21,746 ወይም 80 በመቶ በኢ-ክፍያ ከፍለዋል:: በዓመቱ በኢ-ክፍያ ለመሰብሰብ ከታየዘው ዕቅድ ብር 32.50 ቢሊየን አንጻር ብር 75.75 ቢሊየን በመሰብሰቡ በገንዘብ በብልጫ ብር 43.25 ቢሊየን ተሰብስቧል::አዲስ ወደ ኢ ክፍያ ሥርዓት መግባት ያለባቸውን ታክስ ከፋዮች በተመለከተ 12,104 በዕቅድ ተይዞ 9,102 በማስገባት የዕቀዱ 75 በመቶ ተፈጽሟል:: በዓመቱ በማሳወቅ ከከፈሉ 26,978 ታክስ ከፋዮች 5170 ወይም 19 በመቶ በማኑዋል መክፈላቸው ለዕቅዱ ዝቅ ማለት አስተዋጽኦ አበርክቷል::

**ኢ-ክፍያ ከተጀመረ ጀምሮ ያለው አፈጻጸምን በተመለከተ፦** በኢ-ፋይሊንግ በማሳወቅ ላይ ካሉ 40,842 ታክስ ከፋዮች መካከል 23,366 በኢ-ክፍያ በመክፈል ላይ ይገኛሉ:: ይህም በመቶኛ ሲታይ 57 በመቶ ነው:: ለዕቅዱ ማነስ እንደ ዋና ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱ ጉዳዮች ሁሉም ኢ-ፋይል የሚያደርጉ ታክስ ከፋዮች ከክፍያ ጋር የማይመጡ መሆኑ እና በዓመት በማሳወቅ ከሚከፍሉ ታክስ ከፋዮች 19 በመቶ ያህል በማኑዋል አሳውቀው የሚከፍሉ መሆኑ ናቸው::

ሰንጠረዥ 13 የኤሌክትሮኒክ ክፍያ (E-payment) የእስከ አሁን አፈጻጸም

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | የግብር ከፋይ ብዛት | እስከ አሁን የተጠቃሚ ብዛት | ሽፋን በመቶኛ | በኢ-ፋይሊንግ በማሳወቅ ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች ብዛት | የኢ-ክፍያ ሽፋን ከኢ-ማሳወቅ አንፃር | የትራንዛክሽን ብዛት | የክፍያ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 642 | 639 | 99.53 | 641 | 100 | 39,472 | 87,501,095,769.00 |
| 2 | መካከለኛ | 3,584 | 3,226 | 90.01 | 3,516 | 92 | 120,134 | 27,503,803,228.00 |
| 3 | ምሥራቅ | 12,188 | 6,623 | 54.34 | 11,454 | 58 | 131,381 | 7,910,758,457.00 |
| 4 | ምዕራብ | 11,198 | 6,076 | 54.26 | 10,990 | 55 | 120,020 | 10,107,179,535.00 |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 8,071 | 3,821 | 47.34 | 7,387 | 52 | 57,744 | 3,206,713,005.00 |

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | የግብር ከፋይ ብዛት | እስከ አሁን የተጠቃሚ ብዛት | ሽፋን በመቶኛ | በኢ-ፋይሊንግ በማሳወቅ ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች ብዛት | የኢ-ክፍያ ሽፋን ከኢ-ማሳወቅ አንፃር | የትራንዛክሽን ብዛት | የክፍያ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ባህርዳር | 2,780 | 1,022 | 36.76 | 2,378 | 43 | 5143 | 1,240,307,543.94 |
| 7 | ሀዋሳ | 1,727 | 578 | 33.47 | 1,416 | 41 | 3,464 | 632,830,650.00 |
| 8 | መቀሌ | | 11 | 0 | | 0 | 164 | 13,448,550.00 |
| 9 | አዳማ | 1,126 | 575 | 51.07 | 942 | 61 | 5,215 | 1,815,460,839.90 |
| 10 | ጅማ | 1,419 | 343 | 24.17 | 1,051 | 33 | 1,884 | 431,429,301.00 |
| 11 | ድሬደዋ | 540 | 143 | 26.48 | 450 | 32 | 925 | 845,944,531.00 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 835 | 309 | 37.01 | 617 | 50 | 1,549 | 350,981,900.00 |
| ድምር | | 44,110 | 23,366 | 52.97 | 40,842 | 57 | 487,095 | 141,559,953,309.84 |

ሰንጠረዥ 14 የቴሌብር ኤሌክትሮኒክ ክፍያ(E-payment) አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | በቴሌ ብር የከፈሉ ግብር ከፋዮች ብዛት | የትራንዛክሽን ብዛት | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 2 | 20 | 2,300,700,955.00 |
| 2 | መካከለኛ | 26 | 111 | 1,812,034.00 |
| 3 | ምስራቅ | 651 | 2,548 | 15,832,599.00 |
| 4 | ምዕራብ | 269 | 1,434 | 8,546,550.00 |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 316 | 1,155 | 5,948,802.00 |
| 6 | ባህርዳር | 189 | 367 | 4,010,772.00 |
| 7 | ሐዋሳ | 51 | 100 | 1,407,792.00 |
| 8 | መቀሌ | 0 | 0 | 0 |
| 9 | አዳማ | 64 | 108 | 1,255,516.00 |
| 10 | ጅማ | 11 | 17 | 201,442.00 |
| 11 | ድሬደዋ | 40 | 73 | 929,622.00 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 28 | 53 | 701,869.00 |
| ድምር | | 1,647 | 5,986 | 2,341,347,953.00 |

ይህ ካለይ የተገለጸው መረጃ የሚያሳየው በኢ-ፋይሊንግ አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮችን ብቻ ነው ነገር ግን ውዝፍ ክፍያ ወደ ሥርዓቱ ቢገባ መጠኑ በቁጥርም ሆነ በገንዘብ ይጨምረዋል፡፡

### 3.1.4 የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ ስራዎች አፈጻጸም

#### ➲ የታክስ ከፋዮች ምዝገባ እና አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም

ከብሄራዊ መታወቅያ ፕሮጀክት ጋር በጣት አሻራ የተደገፈ ግብር ከፋይ መታወቅያ ለመስጠት የሚያስችል ስራዎች በመሰራት ላይ ነው፡፡ የብሄራዊ መታወቅያ ካርድ የሚሰጥባቸው የምዝገባ ጣብያዎች አገልግሎት ላይ የሚውሉ 200 የምዝገባ መሳራያዎቹን በየምዝገባው ጣብያ ስም on board የማድረግ ስራ በመከናወን ክልሎች መሳሪያውን እንዲረከቡ ተደርጓል፡፡ የብሄራዊ መታወቅያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እየተገለገለበት ያለውን Fayda System ከሲግታስ ጋር ማቀናጀትና ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በግለሰቦች እንዳይያዝ Duplicator Checker Software የማከናወን ስራ በመከናወን ላይ ነው፡፡ ቢኒሻንጉል ግሙዝ፣ ሀረሬ፣ ድሬደዋ፣ ጋምቤላ ክልል ገቢ መስርያ ቤቶች FAYD NO በመጠቀም በቀን በአማካይ ለ334 ግብር ከፋዮች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እየተሰጠ ነው፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር የተገልጋዮች ቻርተር ሠነድ የዋናው መ/ቤት ዳይሬክቶሬቶች፣ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የሚመለከታቸው ኃለፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ 3000 (ሶስት ሺህ) የቻርተር መጽሄት ታትሟል። ቻርተሩን ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በዋናው መ/ቤት ለሚገኙ የስራ ክፍሎች እና ለ21 ሚኒስትር መ/ቤቶች ለ2 ኮሚሽኖች እና 1 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በድምሩ 864 ተሰራጭቷል። በቻርተር ስታንዳርድ የተሰጠ አገልግሎት በተመለከተ በአጠቃላይ በ12 ወር ለ1,020,439 አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን 518,882 ከስታንዳርዱ ባነሰ፣ 484,244 በስታንደርድ፣ 17 በላይ (በመዘግይት) አገልግሎት ተሰጥቷል። ለ73,260 ታክስ ከፋዮች የክሊራንስ አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን በስታንዳርዱ የተሰጠ ብዛት 3,405፣ ከስታንዳር በታች ብዛት 38,958፣ ከስታንዳርድ በላይ የተሰጠ ብዛት 251 ናቸው።

በአመቱ 10,609 ግብር ከፋዮችን ወደ ታክስ መረቡ ለማስገባት ታቅዶ በ12 ወሩ 12204 ግብር ከፋዮች የተመዘገቡ ሲሆን በራስ ፈቃዳቸው አመልክተው የተሰረዙ 1072 ናቸው። አጠቃላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብር ከፋይ ቁጥር 56,432 ደርሳል። በ12 ወሩ በስታንዳርድ መሰረት 3344 ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግበዋል።

ሰንጠረዥ 15 የግብር ከፋዮች ምዝገባ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የቅርንጫፉ ስም | ጠቅላላ ግብር ከፋይ ከባለፈው በጀት ዓመት የዞረ | በ12 ወር አዲስ የገባ | ከሌላ ቅ/ጽ/ቤት የመጣ | ከማቆያ የወጣ | ንግድ ፈቃድ ስላመጡ የተከፈተ | በመረጃ ማጥራት የተደመረ | ድምር | በበጀት ዓመቱ የተሰረዘ | ወደ ሌላ ቅ/ጽ/ቤት የዞረ | ወደ ማቆያ የገባ | በመረጃ ማጥራት የተቀነሰ | ከ3 ወር በላይ አካውንት ስላልከፈቱ የተዘጋ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | **643** | **0** | **2** | **0** | **0** | **0** | **645** | **2** | **1** | **0** | **0** | **0** | **642** |
| 2 | መካከለኛ | 3795 | 1 | 7 | 0 | 0 | 0 | 3803 | 32 | 4 | 14 | 0 | 0 | 3753 |
| 3 | ምስራቅ | 12097 | 3072 | 114 | 79 | 232 | 36 | 15630 | 401 | 174 | 329 | 0 | 469 | 14257 |
| 4 | ምዕራብ | 12664 | 2867 | 64 | 132 | 0 | 666 | 16393 | 199 | 408 | 713 | 0 | 1754 | 13319 |
| 5 | ሰ/ምዕራብ | 8470 | 2094 | 544 | 0 | 42 | 0 | 11150 | 155 | 106 | 0 | 145 | 511 | 10233 |
| 6 | ባህርዳር | 3656 | 1584 | 4 | 46 | 198 | 6 | 5494 | 143 | 3 | 370 | 5 | 973 | 4000 |
| 7 | ሐዋሳ | 1806 | 461 | 3 | 14 | 35 | 0 | 2319 | 29 | 13 | 14 | 0 | 85 | 2178 |
| 8 | መቀሌ | 2313 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2313 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2313 |
| 9 | አዳማ | 1165 | 276 | 1 | 10 | 15 | 0 | 1467 | 39 | 4 | 18 | 1 | 41 | 1364 |
| 10 | ጅማ | 1919 | 1149 | 14 | 3 | 46 | 0 | 3131 | 24 | 0 | 11 | 0 | 762 | 2334 |
| 11 | ድሬዳዋ | 669 | 134 | 8 | 0 | 12 | 49 | 872 | 23 | 0 | 32 | 0 | 159 | 658 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 1270 | 566 | 12 | 16 | 73 | 28 | 1965 | 25 | 3 | 77 | 1 | 478 | 1381 |
| ጠቅላላ | | **50467** | **12204** | **773** | **300** | **653** | **785** | **65182** | **1072** | **716** | **1578** | **152** | **5232** | **56432** |

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አንድ አለቅ (One stop) ምዝገባ መዕከል ለ133 የውጭ ባለሀብቶች ምዝገባ በማከናወን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ተሰጥቷል። በርቀት የጣት አሻራ ምዝገባ (Remote Registration) ከተለያዩ ሀገራት የተላኩ 876 የዲያስፖራ ግብር ከፋዮች መረጃ አጥርቶ ወደ ሲግታስ በማስገባት የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እንዲያገኙ ተደርጓል። በሲስተም መለየት ያልቻሉ 4875 የጣት አሻራ መረጃዎችን በማኑዋል የመለየት (Manual Validation) እና በስልክና ITSM የመጡ 655 ጉዳዮች ተስተናግደዋል። በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት (Procedure Manual)

መሰረት በወሩ ተገቢው ማጣራት ተደርጎ 1578 ወደ ዘላቂ ማቆያ የገባ ሲሆን::22 ታክስ ከፋዮች ከዘላቂ ማቆያ እንዲወጡ ተደርጓል::

መሰረታዊ የምዝገባ መረጃቸው ወቅታዊ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች 6,091 ናቸው:: የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ወስደው ከሶስት ወር በላይ የንግድ/ኢንቨስትመንት ፈቃድ ባለማውጣታቸው 5,232 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲዘጋ (Suspend) ተደርጓል 23,111 ታክስ ከፋዮች የተሟላና ጥራቱን የጠበቀ የምዝገባ መረጃ እንዲኖራቸው ተደርጓል::

## ➲ የአገልግሎት ኦዲት ስራዎች አፈጻጸም

የዞረውና በ12 ወሩ ከቀረበው የአገልግሎት ኦዲት ጥያቄ 5,220 አንጻር ሲታይ የተቋረጠው 467 ተቀንሶ 4,753 ውስጥ የተከናወነው 4,661 (98 በመቶ) ሲሆን ሽፋኑ 98 በመቶ ለማድረስ በታቀደው መሰረት ተፈጽሟል:: ከቀረበው የአገልግሎት ጥያቄ 92 (2 በመቶ) ለቀጣይ ወር ዞሯል:: ከአገልግሎት ኦዲት በገንዘብ በፍሬ ግብር ብር 2,153,980,916.36 ለመወሰን ታቅዶ ፍሬ ግብር ብር 2,225,758,590.61 በመወሰን የዕቅዱን 103 በመቶ ማሳካት ተችሏል:: ወሳኔዉ ፍሬ ግብር፣ ወለድና መቀጫን ጨምሮ ብር 3,280,966,372.89 ዉጤት ተገኝቷል:: የአገልግሎት ስታንዳርዱ 90 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ሲታይ ከተወሰነው 4,661 ውስጥ 4,481 (96 በመቶ) በተቀመጠው ስታንዳርድ ጊዜ ውስጥ ሲስተናገዱ፣ 180 (4 በመቶ) ከስታንዳርዱ ጊዜ በላይ የወሰደ መሆኑ ታይቷል::

ሰንጠረዥ 16 የአገልግሎት ኦዲት አፈጻጸም በማህደር

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | ከባለፈው ዓመት የዞረ | በ12 ወር የቀረበ | ድምር | የተቋረጠ ማህደር | ቀሪ ማህደር | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ | በስታንዳርዱ የተስተናገደ | ወደ ቀጣይ የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 0 | 405 | 405 | 0 | 405 | 405 | 100 | 405 | 0 |
| 2 | መካከለኛ | 7 | 623 | 630 | 61 | 569 | 567 | 99.65 | 514 | 2 |
| 3 | አዳማ | 1 | 99 | 100 | 1 | 99 | 98 | 98.99 | 97 | 1 |
| 4 | ኮምቦልቻ | 0 | 68 | 68 | 1 | 67 | 67 | 100 | 60 | 0 |
| 5 | ምዕራብ | 10 | 1134 | 1144 | 123 | 1021 | 1013 | 99.22 | 948 | 8 |
| 6 | ድሬዳዋ | 0 | 35 | 35 | 0 | 35 | 35 | 100 | 35 | 0 |
| 7 | ምስራቅ | 112 | 1696 | 1808 | 350 | 1458 | 1454 | 99.73 | 1365 | 4 |
| 8 | ጅማ | 5 | 81 | 86 | 0 | 86 | 83 | 96.51 | 83 | 3 |
| 9 | ሰ/ምዕራብ | 10 | 1,019 | 1029 | | 1029 | 1,024 | 99.51 | 964 | 5 |
| 10 | ባህርዳር | | 464 | 464 | 18 | 446 | 378 | 84.75 | 378 | 68 |
| 11 | ሐዋሳ | 1 | 618 | 619 | | 619 | 618 | 99.84 | 613 | 1 |
| | **ድምር** | **146** | **6242** | **6388** | **554** | **5834** | **5742** | **98.42** | **5462** | **92** |

## ➲ የተመላሽ ስራዎች አፈጻጸም

የተጠቃለለ የተመላሽ አፈጻጸምን በተመለከተ በ2015 በሁሉም የታክስ ዓይነት ጠቅላላ ከቀረበው 2,941 ጥያቄ ውስጥ 87 በሙሉ ውድቅ የተደረገ፣ 304 የተቋረጠ፣ 1,887 በገንዘብ እንዲመለስ የተወሰነ፣ 533 ለዕዳ የተካካሰ በጠቅላላው 2,811 ወይም 96 በመቶ ተከናውኗል:: ቀሪው 130 ጥያቄ ወደ ሚቀጥለው ጊዜ የዞረ ነው:: ስታንዳርዱ የ95 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ሲታይ ከተከናወነው 2,811 ጥያቄ ውስጥ 2,765 ወይም 98 በመቶ በስታንዳርዱ መሰረት የተከናወነ ነው::

ሰንጠረዥ 17 የተጠቃለለ የተመላሽ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የተመላሽ አይነት | የቀረበ የተመላሽ ጥያቄ | ክንውን | ውድቅ የተደረገ | የተቋረጠ | በገንዘብ የተመለሰ | ለዕዳ የተካካሰ | ለቀጣይ የዞረ የተመላሽ ጥያቄ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተጨማሪ እሴት ታክስክስ | 1,486 | 1,374 | 43 | 117 | 1,146 | 68 | 112 |
| 2 | የቅድመ ግብር | 967 | 950 | 21 | 140 | 343 | 446 | 17 |
| 3 | ኤክሳይዝ | 5 | 5 | 0 | 2 | 3 | 0 | 0 |
| 4 | በስህተት /በብልጫ | 483 | 482 | 23 | 45 | 395 | 19 | 1 |
| **ድምር** | | **2,941** | **2,811** | **87** | **304** | **1,887** | **533** | **130** |

ከገንዘብ አኳያ በ12 ወራት በጠቅላላ ተመላሽ የተጠየቀ ብር 10,677,259,743.23 ሲሆን ከዚህ ውስጥ በገንዘብ ተመላሽ የተደረገ ብር 5,875,857,509.12፣ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ውድቅ የተደረገ ብር 2,469,030,185.43፣ ለሌሎች የታክስ እዳዎች የተካካሰ ብር 975,314,736.54፣ እና በተለያየ ምክንያት አገልግሎቱ የተቋረጠ ብር 992,360,318.15 ይሄ.ል:: በሌላ በኩል ጥያቄ ቀርቦበት በሂደት ላይ በቀጣይ የሚከናወን የዞረ የብር መጠን ብር 364,696,993.99 የያዘ ነው::

## ➲ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት አፈጻጸም

ከ2014 በጀት ዓመት የዞሩ 64 የግብር ከፋይ ብር 1,885,559,337.55 የያዙ ቅሬታዎች ሲሆኑ በ2015 በጀት ዓመት አዲስ የቀረቡ ብር 27,702,577,615.71 የያዙ 1816 አዲስ ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን በአጠቃላይ በድምሩ ብር 29,588,136,953.26 የያዙ የ 1880 የግብር ከፋይ ቅሬታዎች ቀርበዋል:: በ2015 በጀት ዓመት ውስጥ የ1828 ግብር ከፋዮች ቅሬታዎች ብር 27,606,986,129.22 የያዘ ውሳኔ ተወስኖ ለግብር ከፋይ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን ወደ 2016 በጀት ዓመት የዞሩ የ52 የግብር ከፋይ ቅሬታዎች ብር 1,981,150,824.04 የያዙ ሆነዋል::

ሰንጠረዥ 18 የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አፈታት አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የነበሩ | | በዓመቱ የተጨመሩ (አዲስ) | | በወሩ የነበሩ መዝገቦች | | ውሳኔ ያገኙ ማህደራት | | ወደ ቀጣይ የዞሩ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በድርጅት | በገንዘብ | በድርጅት | በገንዘብ | በድርጅት | በገንዘብ | በድርጅት | በገንዘብ | በድርጅት | በገንዘብ |
| 1 | ከፍተኛ | 11 | 930,974,168.33 | 179 | 13,336,274,757.92 | 190 | 14,267,248,926.25 | 184 | 13,850,888,977.60 | 6 | 416,359,948.65 |
| 2 | ምሥራቅ | 11 | 64,507,659.53 | 353 | 2,932,946,555.67 | 364 | 2,997,454,215.20 | 346 | 2,638,596,708.25 | 18 | 358,857,506.95 |
| 3 | ምዕራብ | 14 | 44,718,613.64 | 166 | 1,402,277,556.24 | 180 | 1,446,996,169.88 | 178 | 1,421,261,782.52 | 2 | 25,734,387.36 |
| 4 | መካከለኛ | 6 | 632,577,030.01 | 352 | 5,615,528,949.81 | 358 | 6,248,105,979.82 | 355 | 5,608,738,674.81 | 3 | 639,367,305.01 |
| 5 | ሰሜን/ም | 1 | 19,874,376.66 | 212 | 1,143,225,088.42 | 213 | 1,163,099,465.08 | 210 | 1,161,972,223.01 | 3 | 1,127,242.07 |
| 6 | አዳማ | 2 | 20,003,055.48 | 95 | 615,627,910.07 | 97 | 635,630,965.55 | 93 | 620,355,369.92 | 4 | 15,275,595.63 |
| 7 | ጅማ | 1 | 2,115,876.07 | 33 | 60,884,370.79 | 34 | 63,000,246.86 | 33 | 62,361,616.53 | 1 | 638,630.33 |
| 8 | ድሬዳዋ | 1 | 2,566,031.25 | 53 | 222,061,621.02 | 54 | 224,627,652.27 | 53 | 216,206,924.46 | 1 | 8,420,727.81 |
| 9 | ሐዋሳ | 1 | 35,524,406.25 | 78 | 928,177,493.41 | 79 | 963,701,899.66 | 79 | 963,701,899.66 | 0 | - |
| 10 | መቀሌ | 4 | 6,637,063.81 | 1 | 372,424.36 | 5 | 7,009,488.17 | 5 | 7,009,488.17 | 0 | - |
| 11 | ባሕር ዳር | 11 | 48,935,227.32 | 215 | 1,011,726,217.73 | 226 | 1,060,661,445.05 | 217 | 554,842,928.76 | 9 | 505,818,516.29 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 1 | 77,125,829.20 | 79 | 433,474,670.27 | 80 | 510,600,499.47 | 76 | 501,049,535.53 | 4 | 9,550,963.94 |
| **ድምር** | | **64** | **1,885,559,337.55** | **1816** | **27,702,577,615.71** | **1880** | **29,588,136,953.26** | **1828** | **27,606,986,129.22** | **52** | **1,981,150,824.04** |

በአጠቃላይ የተወሰኑት 1828 ውሳኔዎች ይዘት ሲታይ፦

- የ920 ግብር ከፋይ ቅሬታዎች (50%) ከታክስ ኦዲት ተወስነው ቅሬታ የቀረበባቸው ሲሆኑ፣
- የ652 ግብር ከፋይ ቅሬታዎች (36%) ከአወሳሰን፣ ከካሽ ሬጅስተር፣ቅጣት እና ሌሎችም ውሳኔ የሚሰጡ ስራ ክፍሎች ተወስነው ቅሬታ የቀረበባቸው ሲሆኑ፣

- የ139 ግብር ከፋይ ቅሬታዎች (8%) ቅሬታዎች ከኢንቬስትጌሽን ኦዲት ተወስነው ቅሬታ የቀረበባቸው ናቸው፣
- የ117 ግብር ከፋይ ቅሬታዎች (6%) ቅሬታዎች ከተመላሽና ከአገልግሎት ኦዲት የሚመጡ ቅሬታዎች ናቸው::

ሰንጠረዥ 19 በ2015 በጀት ዓመት ዉሳኔ ያገኙ ጉዳዮች

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | እስከ አሁን ውሳኔ ያገኙ ቅሬታዎች/ድርጅቶች | ውሳኔ ያገኙ ቅሬታዎች የያዟቸው ኬዞች | ለተቋም የተወሰኑ ኬዞች ብዛት | ለግብር ከፋይ የተወሰኑ ኬዞች ብዛት | በከፊል/በሙሉ የተሻሻሉ ኬዞች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 184 | 651 | 478 | 0 | 173 |
| 2 | ምሥራቅ | 346 | 1047 | 414 | 189 | 444 |
| 3 | ምዕራብ | 178 | 515 | 222 | 20 | 273 |
| 4 | መካከለኛ | 355 | 735 | 301 | 134 | 300 |
| 5 | ሰሜን/ም | 210 | 424 | 231 | 19 | 174 |
| 6 | አዳማ | 93 | 245 | 146 | 58 | 41 |
| 7 | ጅማ | 33 | 65 | 30 | 19 | 16 |
| 8 | ድሬዳዋ | 53 | 106 | 41 | 23 | 42 |
| 9 | ሐዋሳ | 79 | 205 | 108 | 32 | 65 |
| 10 | መቀሌ | 5 | | | | |
| 11 | ባሕር ዳር | 216 | 352 | 260 | 23 | 69 |
| 12 | ኮምቦልቻ | 76 | 157 | 104 | 7 | 46 |
| **አጠቃላይ ድምር** | | **1828** | **4502** | **2335** | **524** | **1643** |

በ2015 በጀት ዓመት ውስጥ ከተወሰኑት ከ1828 የግብር ከፋይ ፋይሎች በአጠቃላይ 4502 ኬዞች የያዙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2335 ኬዞች (52%) ለተቋም የተወሰኑ ሲሆን 524 ኬዞች (12%) ለግብር ከፋይ የተወሰኑ ናቸው:: ሌሎች 1643 ኬዞች (36%) በድጋሚ ተጣርተው የሚሻሻሉ ሆነው ተወስነዋል:: በአጠቃላይ በ 2015 በጀት ዓመት በቅ/ጽ/ቤቱ እጅ ላይ ከነበሩት 1879 ፋይሎች ውስጥ 1828 (97%) ሲወሰኑ ቀሪው 51 ፋይሎች (3%) ወደ ቀጣይ በጀት ዓመት የዞሩ ናቸው::

ሰንጠረዥ 20 በ2015 በጀት ዓመት በታክስ ኦዲት ተስተካክለዉ የተመለሱ ፋይሎች

| ተ.ቁ | ቅ/ጽ/ቤት | ተስተካክሎ የተመለሰ ፋይል | ቅሬታ የቀረበበት የገንዘብ መጠን በብር | በቅሬታ ውሳኔ መሰረት በታክስ ኦዲት የተስተካከለ የብር መጠን | የተስተካከለ የብር መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 12 | 1,372,978,883.25 | 667,750,478.78 | 705,228,404.47 |
| 2 | ምሥራቅ | 138 | 1,827,806,750.40 | 699,698,135.20 | 1,128,108,615.20 |
| 3 | ምዕራብ | 60 | 210,535,528.26 | 65,522,597.00 | 145,012,931.26 |
| 5 | መካከለኛ | 105 | 1,096,303,271.02 | 629,304,831.23 | 466,998,439.79 |
| 7 | ሰሜን ምዕራብ | 52 | 203,543,093.36 | 47,782,637.50 | 155,760,455.86 |
| 8 | አዳማ | 35 | 126,332,421.96 | 52,457,385.04 | 73,875,036.92 |
| 9 | ጅማ | 19 | 28,077,331.71 | 14,575,604.44 | 13,501,727.27 |
| 10 | ድሬዳዋ | 46 | 155,159,071.95 | 48,233,553.92 | 106,925,518.03 |
| 11 | ሐዋሳ | 35 | 903,392,992.70 | 880,053,494.56 | 23,339,498.14 |
| 12 | ባሕር ዳር | 49 | 148,563,331.57 | 96,632,262.73 | 51,931,068.84 |
| 13 | ኮምቦልቻ | 23 | 131,563,403.50 | 78,045,746.88 | 53,517,656.62 |
| **ድምር** | | **574** | **6,204,256,079.68** | **3,280,056,727.28** | **2,924,199,352.40** |

በ2015 በጀት ዓመት በታክስ ኦዲት ተስተካክለዉ የተመለሱ ፋይሎችን በመለከተ የ574 ግብር ከፋዮች ውሳኔ ብር 6.2 ቢሊየን የያዙ ቅሬታ ቀርቦባቸው በቅሬታ ውሳኔ መሰረት እንዲተስተካከሉ የተደረገ ሲሆን በታክስ

ኦዲት ተስተካክሎ የተወሰነ ብር 3.28 ቢሊዮን ሲሆን በልዩነቱ ብር 2.9 ቢሊዮን (47%) የጋሸበ ውሳኔ ተወስኖ እንደነበር ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 21 የክስና ጉምሩክ መረጃ፣ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ስራዎች አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባራት | መለኪያ | ዕቅድ | የቀረቡ ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ሌሎች ጉዳዮች | ክንውን | አፈጻጸም (%) ከቀረቡት አንፃር | ስታንዳርድ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ባነሰ | እኩል | በበለጠ |
| 1 | ቀርበው የተስተናገዱ የሀገር ውስጥ ታክስ መረጃ፣ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ጥያቄዎች ብዛት | ስልክ | 6912 | 5192 | 5192 | | 886 | 4257 | 49 |
| | | ፅሁፍ | 96 | 35 | 35 | | | 31 | 4 |
| | | ኢ-ሜይል | | 484 | 484 | | 87 | 397 | |
| | | በግንባር(በአካል) | 288 | 615 | 615 | | 110 | 505 | |
| | | በግንባር(በአካል) | 816 | 615 | 615 | | 110 | 505 | |
| | | ድምር | 8112 | 6326 | 6326 | 100% | 1083 | 5190 | 53 |
| 2 | ቀርበው የተስተናገዱ የጉምሩክ መረጃ፣ ማብራሪያና ምክር አገልግሎት ጥያቄዎች ብዛት | ስልክ | 3456 | 1458 | 1458 | | 787 | 585 | 86 |
| | | ኢ-ሜይል | 576 | 321 | 321 | | 154 | 133 | 34 |
| | | በግንባር(በአካል) | 864 | 414 | 414 | | 219 | 146 | 49 |
| | | ድምር | 4896 | 2193 | 2193 | 100% | 1160 | 864 | 169 |
| 3 | በሀገር ውስጥ ታክስ የቀረቡ እና ምላሽ የተሰጠባቸው ቅሬታዎች ብዛት | በቁጥር | 115 | 110 | 110 | " | 23 | 81 | 6 |
| | በጉምሩክ የቀረቡ እና ምላሽ የተሰጠባቸው ቅሬታዎች ብዛት | በቁጥር | | | | | | | |
| | | ድምር | 115 | 110 | 109 | | 23 | 81 | 6 |
| 4 | የአጭር መልዕክት አገልግሎት (በታ/ከፋዩ የሞባይል ስልክ ቁጥሮች በኩል) | በቁጥር | | 519,769 | 519,769 | 100 | 155930 | 311862 | 51977 |
| 5 | ሼር 8 (\\10.12.0.8) ላይ የተቀመጡ ህጎችና የአሰራር ስርዓቶች | በቁጥር | | 98 | 98 | 100 | 3 | 73 | 22 |
| 6 | ዌብሳይት ላይ እንዲቀመጡ የተደረጉ ህጎችና የአሰራር ስርዓቶች እንዲሁም ቅፃች | በቁጥር | | 32 | 32 | 100 | | 12 | 20 |
| 7 | በተቋሙ ዋና መግቢያ በሮች የተሰጡ የባለ ጉዳዮች ድጋፍና የመረጃ አቅርቦት አገልግሎት በቁጥር | በቁጥር | 21,000 | 23,019 | 23,019 | 100 | ወንድ (18202) | ሴት (18202) | በስታንዳርዱ መሰረት የተሰጠ አገልግሎት |

## 3.2 የግብር ከፋዮች የታክስ ህግ ተገዥነት ማሻሻል ስራዎች አፈጻጸም

### 3.2.1 የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብ ማጠናከር ስራዎች አፈጻጸም

➲ **የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቅ አፈጻጸም**

በበጀት ዓመቱ 31,002 ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፍ ማሳወቅ ከሚጠበቅባቸው ውስጥ 26,453 ወይም 85.33 በመቶ አሳውቀዋል:: በ2014 የማስታወቅ አፈጻጸም 79 በመቶ በመሆኑ በግብር ዘመኑ ማስታወቂያ አቀራረብ መሻሻል አሳይቷል:: ከቀረቡት የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያዎች ውስጥ 10,717 (40.5 በመቶ) በክፍያ የቀረበ ማስታወቂያ ሲሆን የተሰበሰበ የገንዘብ መጠን ብር 54,531,499,776,378 መሆኑ፣ 4,901 (18.53 በመቶ) ኪሳራ፣ 768 (2.90 በመቶ) ተመላሽ እና 10,067 (38 በመቶ) ባዶ የያዘ የታክስ ማስታወቂያ ነው:: በ2014 የቀረበው የታክስ ማስታወቂያ መካከል የክፍያ ድርሻ 44 በመቶ የነበረ በመሆኑ አፈጻጸሙ እየቀነሰ መምጣቱ በቀጣይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው::

ከሚቀርቡ የንግድ ትርፍ ማሳወቂያዎች ውስጥ ከክፍያ ጋር የሚቀርበው ድርሻ 65 በመቶ እንዲደርስ ታቅዶ በክፍያ የቀረበው 40.5 በመቶ ስለሆነ በዓመቱ የቀረቡ የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያዎችን ትክክለኛነት የክፍያ መጠን ማስታወቃቸው የማረጋገጥ ስራ በስፋት መሠራት እንዳለበት ማየት ተገቢ ነው:: በክፍያ የሚቀርቡ የንግድ ትርፍ ማሳወቂያዎች ቁጥር እየጨመረ እንዲመጣ ቀድሞ የደረሰኝ ቁጥጥር ስራዎች እና የታክስ ከፋዩን ሰነዶች በወቅቱ ጥራት ላይ ትኩረት በማድረግ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ከቀረቡ ማስታወቂያዎች ውስጥ 15,736 (59.5 በመቶ) የሚሆነው ኪሳራ፣ ተመላሽ እና ባዶ በመሆኑ የታክስ ከፋዮች ሰነድ ሲጣራ ጥራት ላይ ትኩረት ካልተደረገ ታክስ ከፋዩ እንደማይደረስበት ግንዛቤ እየወሰደ ስለሚመጣ ኪሳራ፣ ተመላሽ እና ባዶ የማሳወቅ ሁኔታዎች ልምድ እየሆኑ እንዳይቀጥሉ የተሰማሩበትን የሥራ ዘርፍ መሠረት በማድረግ ልዩ ትኩረት በመስጠት ዓመታዊ የትርፍ ኪሳራ መግለጫቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::

ሰንጠረዥ 22 የንግድ ትርፍ ግብር ማስታወቅ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | አጠቃላይ የግብር ከፋይ ቁጥር | ከክፍያ ጋር ያስታወቁ | ከቀረቡ ማስታወቂያዎች የክፍያ አፈጻጸም በመቶኛ | የክፍያ መጠን ብር | ኪሳራ ያስታወቁ | ተመላሽ ያስታወቁ | ባዶ ያስታወቁ | ያስታወቁ (ድምር) | ያሳወቁ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 632 | 458 | 73.40 | 44,027,960,760.05 | 27 | 132 | 4 | 624 | 98.73 |
| 2 | ምሥራቅ | 9244 | 3316 | 43.72 | 754,340,751.99 | 2453 | 0 | 1815 | 7584 | 82.04 |
| 3 | ምዕራብ | 6809 | 1654 | 30.99 | 1,146,819,132.81 | 610 | 183 | 2891 | 5338 | 78.40 |
| 4 | መካከለኛ | 3453 | 1719 | 61.59 | 5,634,222,721.00 | 511 | 353 | 208 | 2791 | 80.83 |
| 5 | ሰሜን/ም | 4393 | 1302 | 28.67 | 586,137,402.58 | 257 | 0 | 2982 | 4541 | 103.37 |
| 6 | አዳማ | 967 | 329 | 46.27 | 447,900,000.00 | 124 | 23 | 235 | 711 | 73.53 |
| 7 | ጅማ | 1018 | 242 | 38.54 | 100,773,265.00 | 94 | 24 | 268 | 628 | 61.69 |
| 8 | ድሬዳዋ | 441 | 145 | 36.16 | 630,096,341.57 | 0 | 53 | 203 | 401 | 90.93 |
| 9 | ሐዋሳ | 1254 | 557 | 44.85 | 148,112,761.87 | 251 | 0 | 434 | 1242 | 99.04 |
| 10 | ባሕር ዳር | 2116 | 746 | 36.57 | 844,846,885.41 | 426 | 0 | 868 | 2040 | 96.41 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 675 | 249 | 44.78 | 210,289,754.50 | 148 | | 159 | 556 | 82.37 |
| **ድምር** | | **31002** | **10717** | **40.51** | **54,531,499,776.78** | **4901** | **768** | **10067** | **26453** | **85.33** |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው ከክፍያ ጋር ለማቅረብ የታቀደውን 65 በመቶ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ብቻ 73 በመቶ የተከናወነ ሲሆን የተቀሩት ቅ/ጽ/ቤቶች ከዕቅዱ በታች የተፈጸመ ነው:: ከማስታወቅ አቀራረብ ጋር 85 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አንጻር ከፍተኛ፣ ሰሜን

ምዕራብ፣ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ እና ባህርዳር ከእቅዱ በላይ የተከናወነ ሲሆን የተቀሩት ቅ/ጽ/ቤቶች በእቅዱ መሠረት ያልተፈጸመ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ያሳያል።

### ➲ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች የሂሳብ ጊዜያቸው በድግግሞሽ 118,331 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች በየወሩ እና በየ3 ወራት እንደሚቀርቡ ይጠበቃል። ከዚህ ውስጥ 96,296 (81.38 በመቶ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች ቀርበዋል። በበጀት ዓመቱ በወቅቱ ይቀርባል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘው 85 በመቶ አኳያ ሲታይ በወቅቱ የቀረበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ 81.38 በመቶ በመሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮች በሂሳብ ጊዜያቸው እንዲያሳውቁ የመቀስቀስ እና የማስገንዘብ ስራ ስራ የሚጠይቅ መሆኑን አመላካች ነው። በ2014 የማስታወቅ አፈጻጸሙ 80.61 በመቶ የነበረ በመሆኑ መጠነኛ ማሻሻያ አሳይቷል።

ከቀረቡት አጠቃላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች ውስጥ 37,842 (39.3 በመቶ) በክፍያ የቀረበ የታክስ ማስተወቂያ ሲሆን የተሰበሰበ የገንዘብ መጠን ብር 56,658,807,150.09 ሲሆን፣ 38,084 (39.55 በመቶ) ተመላሽ እና 20,370 (21.15 በመቶ) ባዶ ናቸው። በ2014 ከክፍያ ጋር የቀረበው ድርሻ 37.2 በመቶ የነበረ በመሆኑ ማሻሻያ ታይቷል።

በክፍያ የሚቀርቡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች 41 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አኳያ 39.3 በመቶ በመሆኑ ለቀጣይ ዓመት ትኩረት የሚፈልግ ይሆናል። በተለይ በየሩብ ዓመቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያሳውቁ ታክስ ከፋዮች በቁጥር በርካታ በመሆኑ እስከሚቀጥለው የማሳወቂያ ጊዜ የቀረቡ ማሳወቂያዎችን ታክስ ከፋዩ ሰነድ እንዲያቀርብ በማድረግ ማረጋገጥ ተመላሽ የሚያሳውቁትን በዘርፍ በመለየት ስቶክ በአካል ቼክ እስከማድረግ ያለውን ስራ መስራት ይጠይቃል።

በተለይ አሁን ላይ እየተተገበረ ያለው የኢ-ማስታወቅ ስራ ታክስ ከፋዩ ታክስ በሚያሳውቅበት ወቅት ሰነድ ስለማያቀርብ በወቅቱ ማረጋገጥ ስለማይቻል ካሳወቀ በኋላ ሰነድ እንዲያቀርብ በማድረግ የማረጋገጥ ስራን በተላለፈ የስራ ስምሪት መሰረት እየለዩ መስራት ያስፈልጋል።

ሰንጠረዥ 23 የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | መቅረብ ያለባቸው ማሳወቂያዎች ብዛት | በክፍያ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | አፈጻጸም በመቶኛ | የክፍያ መጠን በብር | በተመላሽ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | በባዶ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | ጠቅላላ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | የቀረቡ ማስታወቂያዎች አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 7,704 | 4,284 | 56.70 | 34,277,837,817.98 | 2,941 | 329 | **7,554** | **98.05** |
| 2 | ምሥራቅ | 28,300 | 7,412 | 38.10 | 3,049,896,051.11 | 8,753 | 3,308 | **19,473** | **68.81** |
| 3 | ምዕራብ | 23,212 | 6,170 | 35.00 | 2,462,973,867.32 | 4,085 | 7,359 | **17,614** | **75.88** |
| 4 | መካከለኛ | 21,616 | 8,485 | 44.90 | 9,418,254,864.25 | 9,804 | 612 | **18,901** | **87.44** |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 16,865 | 5,778 | 36.90 | 1,419,696,292.00 | 7,688 | 2,176 | **15,642** | **92.75** |
| 6 | አዳማ | 3,873 | 1,394 | 45.00 | 1,293,000,000.00 | 877 | 830 | **3,101** | **80.07** |
| 7 | ጅማ | 3,606 | 589 | 20.80 | 118,549,022.00 | 461 | 1,776 | **2,826** | **78.37** |
| 8 | ድሬዳዋ | 1,323 | 507 | 40.30 | 1,496,069,708.88 | 439 | 312 | **1,258** | **95.09** |
| 9 | ሐዋሳ | 4,633 | 1,164 | 29.30 | 533,213,267.39 | 1,068 | 1,745 | **3,977** | **85.84** |
| 10 | ባሕር ዳር | 4,782 | 1,365 | 33.80 | 2,125,404,469.05 | 1,470 | 1,203 | **4,038** | **84.44** |

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | መቅረብ ያለባቸው ማሳወቂያዎች ብዛት | በክፍያ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | አፈጻጸም በመቶኛ | የክፍያ መጠን በብር | በተመላሽ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | በባዶ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | ጠቅላላ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | የቀረቡ ማስታወቂያዎች አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ኮምቦልቻ | 2,417 | 694 | 36.30 | 463,911,790.11 | 498 | 720 | **1,912** | **79.11** |
| ድምር | | 118,331 | 37,842 | 39.30 | 56,658,807,150.09 | 38,084 | 20,370 | 96,296 | 81.38 |

ከላይ ከሠንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው በማስታወቂያ አቀራረብ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ያየነው እንደሆነ ጠቅላላ መቅረብ ከሚጠበቅባቸው 85 በመቶ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያዎች አኳያ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ እና ሰሜን ምዕራብ ከዕቅዱ በላይና በዕቅዱ መሠረት ሲሆን ቀሪዎቹ ቅ/ጽ/ቤቶች በትኩረት ሊሰሩ ይገባል። ከክፍያ ጋር የቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎችም 41 በመቶ ከማድረስ አኳያ የከፍተኛ ፣ መካከለኛ እና አዳማ የተሻለ አፈጻጸም ሲታይ ቀሪዎቹ ቅ/ጽ/ቤቶች ከዕቅዱ በታች ስለሆኑ በቀጣይ በጀት ዓመት የሚቀርቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል። በክፍያ የቀረቡትንም ትክክለኛነት ማረጋገጥ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

### ➲ የኤክሳይዝ ታክስ አፈጻጸምን በተመለከተ

**የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ቁጥጥርና መስክ ስራ አፈጻጸምን በተመለከተ፦** እስከ አሁን ፈቃድ የተሰጣቸው 627 ቢሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1287/2015 መሠረት ነጻ በመደረጋቸው ፈቃዳቸው ያልተሰረዙ ቴሌቭዥን መገጣጠም 30 ድርጅቶችና ኤሌክትሮንክስ 10 ድርጅቶች በጠቅላላ 40 ድርጅቶች ፈቃዳቸው በቀጣይ የሚሰረዙ ይሆናል።

በመስክ ምልከታ (Inspection) የኤክሳይዝ ታክስ ተመዝጋቢ ድርጅቶች ላይ 100% ለመድረስ በየቅ/ጽ/ቤቱ ካላቸው በየወሩ ድርጅቶች ላይ ቁጥጥር መደረጉን ታቅዶ እንደ ተቋም ካለው 627 ታክስ ከፋይ አንጻር ፈቃድ ለመውሰድ የጠየቁትን ጨምሮ 1233 ለመጎብኘት ታቅዶ 1235 ድርጅቶች የመስክ ምልከታ የተደረገ በመሆኑ አፈጻጸሙ 100% ያሳያል። በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች በክትትል በ61 ታክስ ከፋዮች ላይ የተገኘ ግኝት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲወሰን ለስሌት ስራ ክፍል የተላለፈ መሆኑ የመስክ ስራው በልዩነት ታክስ ሊወሰንባቸው የሚገቡ ታክስ ከፋዮች ለመለየት የሚረዳ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

### የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ አሰጣጥ

**ሰንጠረዥ 24 የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ አሰጣጥ**

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | በ2014 ዓ.ም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የወሰዱ | መስፈርት ባለማሟላታቸው ፈቃድ ያልወሰዱ ለ2015 ዓ.ም የዞረ | ከሐምሌ 1/2014 እስከ ሰኔ 2015 ዓ.ም ፈቃድ ለማግኘት አዲስ የመመዝገቢያ ማመልከቻ ፎርም የወሰዱ | በ2015 ዓ.ም ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው ድምር | ከሀምሌ 1/2014 እስከ ሰኔ 30/2015 ዓም ፈቃድ የተሰጣቸው ብዛት | አጠቃላይ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የወሰዱ ብዛት | መስፈርቱ ባለመሟላቱ ፈቃድ ያልወሰዱ ለሐምሌ /2015 የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | **53** | **5** | **0** | **5** | **5** | **58** | **0** |
| 2 | መካከለኛ | 124 | 5 | 0 | 5 | 4 | 127 | 2 |
| 3 | ሰ/ምዕራብ | 152 | 5 | 22 | 27 | 27 | 178 | 1 |
| 4 | ምዕራብ | 83 | 11 | 18 | 34 | 29 | 112 | 5 |
| 5 | ምስራቅ | 39 | 1 | 17 | 18 | 18 | 57 | 0 |
| 6 | ባህር ዳር | 12 | 0 | 7 | 7 | 7 | 21 | 0 |

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | በ2014 ዓ.ም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የወሰዱ | መስፈርት ባለማሟላታቸው ፈቃድ ያልወሰዱ ለ2015 ዓ.ም የዞረ | ከሐምሌ 1/2014 እስከ ሰኔ 2015 ዓ.ም ፈቃድ ለማግኘት አዲስ የመመዝገቢያ ማመልከቻ ፎርም የወሰዱ | በ2015 ዓ.ም ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው ድምር | ከሀምሌ 1/2014 እስከ ሰኔ 30/2015 ዓም ፈቃድ የተሰጣቸው ብዛት | አጠቃላይ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የወሰዱ ብዛት | መስፈርቱ ባለመሟላቱ ፈቃድ ያልወሰዱ ለሐምሌ /2015 የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | አዳማ | 21 | 0 | 1 | 1 | 1 | 22 | 0 |
| 8 | ሀዋሳ | 26 | -1 | -1 | -1 | -1 | 25 | 0 |
| 9 | ኮምቦልቻ | 10 | 0 | 4 | 4 | 4 | 14 | 0 |
| 10 | ድሬዳዋ | 8 | 0 | 1 | 1 | 1 | 9 | 0 |
| 11 | ጅማ | 3 | 0 | 1 | 1 | 1 | 4 | 0 |
| | ድምር | 531 | 26 | 70 | 102 | 96 | 627 | 8 |

## የኤክሳይዝ ታክስ የመስክ ምልከታና ቁጥጥር ስራዎች

ሰንጠረዥ 25 የኤክሳይዝ ታክስ ለፈቃድ አሰጣጥ ወይም ለክትትል የተካሄደ መስክ ስራ

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | አጠቃላይ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የወሰዱ ብዛት | በ2015 በ12 ወራት ክትትልና ጉብኝት የተደረገባቸው ብዛት በድግግሞሽ | | | በክትትል የተገኘ ግኝት ለታክስ በማስታወቅ ስራ ሂደት በኩል ለውሳኔ ለስሌት የተላለፈ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ | |
| 1 | መካከለኛ | 127 | 156 | 207 | 100 | 13 |
| 2 | ሰሜን ምዕራብ | 178 | 166 | 165 | 99 | 17 |
| 3 | ምዕራብ | 112 | 82 | 76 | 96 | 10 |
| 4 | ከፍተኛ | 58 | 378 | 378 | 100 | 10 |
| 5 | ምስራቅ | 57 | 84 | 84 | 100 | 2 |
| 6 | ሀዋሳ | 25 | 75 | 75 | 100 | 2 |
| 7 | አዳማ | 22 | 65 | 68 | 100 | 5 |
| 8 | ባህር ዳር | 21 | 101 | 71 | 71 | 0 |
| 9 | ድሬዳዋ | 9 | 47 | 36 | 91 | 0 |
| 10 | ኮምቦልቻ | 15 | 79 | 75 | 95 | 2 |
| 11 | ጅማ | 3 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | ጠቅላላ ድምር | 627 | 1233 | 1235 | 100 | 61 |

### ➡ የኤክሳይዝ ታክስ ማሰታወቅ አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ 7,143 የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ እንደሚቀርቡ የሚጠበቅ ሲሆን 6,854 (95.95 በመቶ) ማስታወቂያዎች ቀርበዋል፡፡ የታክስ ማስታወቅ አቀራረብ 95 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አንጻር በእቅዱ መሠረት መፈጸሙን ማየት ይቻላል፡፡ በ2014 የማስታወቅ አፈጻጸሙ 92.11 በመቶ የነበረ በመሆኑ እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከቀረቡት ማስታወቂያዎች ውስጥ በክፍያ 4510(66 በመቶ) ወይም በገንዘብ ብር 24,426,265,833.93 ሲሆን፣ 2314 (33.76 በመቶ) ባዶ እና 30 (0.44 በመቶ) ተመላሽ አሳውቀዋል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ በ12 ወራት ከክፍያ ጋር መቅረብ ካለባቸው 70 በመቶ አንጻር ከክፍያ ጋር መቅረብ ያለባቸው የታክስ ማስታወቂያዎች አኳያ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በ2014 የክፍያ ድርሻ 68 በመቶ የነበረ እና በዚህ በጀት ዓመት የቀነሰ በመሆኑ ምክንያን ለይቶ የመስክ ስራ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ 95 በመቶ እንዲያስታውቁ

ከሚጠበቀው አንጻር 95.95 በመቶ የተሻለ ቢሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የመስክና የቁጥጥር ሥራው መጠናከር ይኖርበታል፡፡

ሰንጠረዥ 26 የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም

| ተ.ቁ. | ቅርንጫፍ | መቅረብ ያለባቸው ማሳወቂያዎች ብዛት | በክፍያ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | አፈጻጸም በመቶኛ | የክፍያ መጠን ብር | በተመላሽ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | በባዶ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | ጠቅላላ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | የቀረቡ ማስታወቂያዎች አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 631 | 542 | 85.90 | 17,974,859,591.02 | 16 | 73 | 631 | 100.00 |
| 2 | ምሥራቅ | 672 | 299 | 48.23 | 901,966,973.04 | | 321 | 620 | 92.26 |
| 3 | ምዕራብ | 1132 | 674 | 65.37 | 124,941,608.58 | | 357 | 1031 | 91.08 |
| 4 | መካከለኛ | 1517 | 1076 | 71.26 | 656,344,888.89 | 2 | 432 | 1510 | 99.54 |
| 5 | ሰሜን/ም | 2136 | 1345 | 64.32 | 337,334,905.00 | | 746 | 2091 | 97.89 |
| 6 | አዳማ | 245 | 107 | 48.64 | 115,131,239.21 | 0 | 113 | 220 | 89.80 |
| 7 | ጅማ | 42 | 14 | 37.84 | 780,149.35 | | 23 | 37 | 88.10 |
| 8 | ድሬዳዋ | 108 | 80 | 78.43 | 411,911,718.74 | | 22 | 102 | 94.44 |
| 9 | ሐዋሳ | 291 | 190 | 68.84 | 443,630,021.79 | 8 | 78 | 276 | 94.85 |
| 10 | ባሕር ዳር | 219 | 114 | 58.76 | 3,402,622,635.68 | 4 | 76 | 194 | 88.58 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 150 | 69 | 48.59 | 56,742,102.63 | | 73 | 142 | 94.6 |
| | **ድምር** | **7,143** | **4,510** | **65.80** | **24,426,265,833.93** | **30** | **2,314** | **6,854** | **95.95** |

ከላይ ከሠንጠረዡ ለማየት እንደሚቻለው ከክፍያ ጋር ለማቅረብ የታቀደውን 70 በመቶ በከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤቶች በእቅዱ መሠረት የተከናወነ ሲሆን የተቀሩት ቅ/ጽ/ቤቶች ከዕቅድ በታች የተፈጸመ ነው፡፡ ከማስታወቅ አቀራረብ ጋር 95 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አንጻር አዳማ፣ ጅማ እና ባህርዳር ከእቅዱ በታች የተከናወነ ሲሆን የተቀሩት ቅ/ጽ/ቤቶች በእቅዱ መሠረትና በላይ የተፈጸመ በመሆኑ በ3ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በቀጣይ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ያሳያል፡፡

### ➲ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም

በበጀት ዓመቱ ከሚጠበቀው 76,523 የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ውስጥ 62,625 (82 በመቶ) ማስታወቂያ የቀረበ በመሆኑ ከዕቅዱ 80 `በመቶ አንጻር የተሻለ መሆኑን፣ በ2014 የማስታወቅ አፈጻጸሙ 76.66 በመቶ የነበረ በመሆኑ የተሻለ ለውጥ መታየቱን ማየት ይቻላል፡፡

ከዚህ ውስጥ 13,008 (21 በመቶ) በክፍያ ከቀረበ የታክስ ማስታወቂያ ብር 102,352,604.96 መሰብሰቡን ያሳያል፡፡ በታክስ ዓይነቱ ባዶ የቀረበው የታክስ ማስታወቂያ 49,617 (79 በመቶ) የያዘ በመሆኑ በጣም በርካታ በመሆናቸው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በ2014 የክፍያ ድርሻ 22.27 በመቶ የነበረና አሁን የቀነሰ በመሆኑ ትኩረት የሚሻ ሲሆን ከዓመት ዓመት የክፍያ ድርሻ ብዙ ለውጥ የማይታይበት ስለሆነ ታክሱ ሚጠበቅባቸው ታክስ ከፋዮች የዘርፍ ሁኔታ በዝርዝር ማየት ይፈልጋል፡፡

በታክስ አይነቱ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ከታክስ ስርዓት ዘርፍ ጋር በጋራ መስራቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ከፋዮቹን ዓመታዊ ተርን ኦቨር መረጃ ማጥራት እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የሚያስመዘግባቸው ከሆነ ወደ ስርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ደረጃ ዜሮ አሳዋቂ ቁጥር በርካታ ስለሆነ ፋይላቸው ከ3ኛ ወገን መረጃ ጋር መገናዘብና ማስተካከያ በወቅቱ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ሚናቸው ቀላል ባለመሆኑ እንደሌሎች ታክሶች ሁሉ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል፡፡

ሰንጠረዥ 27 የተርንኦቨር ታክስ ማስታወቅ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | ማሳወቅ ያለባቸው በታክስ ማስታወቂያ ብዛት | በክፍያ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | አፈጻጸም በመቶኛ | በባዶ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | ጠቅላላ የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | የቀረቡ ማስታወቂያዎች አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምሥራቅ | 21,636 | 2,929 | 19 | 12,619 | 15,548 | 72 |
| 2 | ምዕራብ | 10,817 | 2,335 | 23 | 7,846 | 10,181 | 94 |
| 3 | መካከለኛ | 142 | 59 | 52 | 54 | 113 | 80 |
| 4 | ሰሜን/ም | 16,428 | 2,643 | 19 | 11,540 | 14,183 | 86 |
| 5 | አዳማ | 1,517 | 458 | 36 | 830 | 1,288 | 85 |
| 6 | ጅማ | 1,380 | 195 | 18 | 894 | 1,089 | 79 |
| 7 | ድሬዳዋ | 1,812 | 245 | 17 | 1,218 | 1,463 | 81 |
| 8 | ሐዋሳ | 5,243 | 768 | 17 | 3,676 | 4,444 | 85 |
| 9 | ባሕር ዳር | 13,814 | 2,651 | 23 | 9,036 | 11,687 | 85 |
| 10 | ኮምቦልቻ | 3,734 | 725 | 28 | 1,904 | 2,629 | 70 |
| | **ድምር** | **76,523** | **13,008** | **21** | **49,617** | **62,625** | **82** |

ከላይ ከሠንጠረዡ ለማየት እንደሚቻለው ከክፍያ ጋር ለማቅረብ የታቀደውን 25 በመቶ መካከለኛ፣ አዳማ እና ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤቶች በእቅዱ መሠረት የተከናወነ ሲሆን የተቀሩት ቅ/ጽ/ቤቶች ከዕቅዱ በታች የተፈጸመ ነው፡፡ ከማስታወቅ አቀራረብ ጋር 80 በመቶ ለማድረስ ከታቀደው አንጻር ምስራቅ፣ ጅማ እና ኮምቦልቻ ከእቅዱ በታች የተከናወነ ሲሆን የተቀሩት ቅ/ጽ/ቤቶች በእቅዱ መሠረትና በላይ የተፈጸመ በመሆኑ በ3ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በቀጣይ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ያሳያል፡፡

### ➲ የታክስ ስሌት ስራዎች አፈጻጸም

በታክስ ከፋዮች ከቀረቡት የታክስ ማስታወቂያዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ በኢ-ፋይል አስታውቀው ያልከፈሉትን በመለየት፣ ዘግይተው የሚያስታውቁትን ወለድና መቀጫ በመጨመር ስሌት በመስራት እንዲሁም ክፍያ ሲኖር ማስታወቅ ሲገባቸው ያላስታወቁትን የታክስ ዓይነት (ዲቪደንድ፣ ቴክኒካል ሰርቪስ፣ ሪቨርስ ታክስ ወዘተ) ለይቶ የዴስክ ኦዲት ስራዎች በታክስ ስሌት ስራ ክፍል ውሳኔ የሚወጣባቸው ስራዎች ናቸው፡፡ በበጀት ዓመቱ ብር 32.72 ቢሊዮን የታክስ ስሌት ለመስራት በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ኦዲት (Control Audit) በIMF ድጋፍ 50 ፋብሪካዎች በመስራት 6.8 ቢሊዮን ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ላይ ለመስራት ታቅዶ ከእቅድና ዝግጅት ጋር በተያያዘ የስራ ላይ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ለኦዲት የሚያስፈልጉ መረጃዎች የማጠናከር ስራ ስልጠና ባለመሰጠቱ አልተሰራም፡፡ በመሆኑም በመደበኛው የስሌት እቅድ ብር 25,873,512,823.49 ውስጥ ብር 31,099,457,390.43 የዕቅዱ 120.20 በመቶ ተወስኗል፡፡ ውጤቱም የኤክሳይዝ ቁጥጥር ኦዲት የተያዘውን የሚያካክስ አፈጻጸም መሆኑ አበረታች ነው፡፡ በ2014 ብር 25.17 ቢሊዮን ከተወሰነው ጋር ሲነጻጸር የ23 በመቶ ጭማሪ ያለው መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

### ሰንጠረዥ 28 የ2015 በጀት ዓመት አጠቃላይ የስሌት ስራዎች አፈጻጸም እና በልዩነት የተገኘ የገንዘብ መጠን

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | ስሌት ሳይሰራለት የዞረ ማስታወቂያ ብዛት | በበጀት ዓመቱ ለስሌት የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | ጠቅላላ ለስሌት የቀረቡ ማስታወቂያዎች ብዛት | እስስመንት የተሰራላቸው ማስታወቂያዎች ብዛት | ልዩነት የተገኘባቸው ማስታወቂያ ብዛት | ልዩነት የተገኘባቸው በማስታወቂያዎች ብዛት | | | አጠቃላይ በስሌት የተወሰነ በገንዘብ | | | ስሌት ሳይሰራላቸው ወደ ሚቀጥለው ወር የዞረ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ዕቅድ | ክንዉን | በመቶኛ | ዕቅድ | ክንውን | በመቶኛ | |
| 1 | ከፍተኛ | 0 | 41,305 | 41,305 | 41,255 | 2,520 | 1,860 | 2,520 | **135** | 10,900,000,000.00 | 12,597,036,632.83 | **115.57** | 50 |
| 2 | ምሥራቅ | 0 | 146,430 | 146,430 | 137,047 | 39,557 | 28,236 | 39,557 | **140** | 3,916,649,830.58 | 4,080,861,745.66 | **104.19** | 0 |
| 3 | ምዕራብ | 0 | 110,065 | 110,065 | 95,509 | 18,848 | 13,608 | 18,848 | **139** | 1,456,870,000.00 | 2,348,852,382.07 | **161.23** | 0 |
| 4 | መካከለኛ | 0 | 15,856 | 15,856 | 15,227 | 12,712 | 13,297 | 12,712 | **96** | 6,478,023,690.00 | 7,616,543,908.32 | **117.58** | 0 |
| 5 | ሰሜን/ም | 0 | 79,010 | 79,010 | 79,010 | 13,713 | 14,082 | 13,713 | **97** | 1,309,000,000.00 | 1,515,509,919.70 | **116.00** | 0 |
| 6 | አዳማ | 0 | 11,675 | 11,675 | 11,675 | 1,546 | 1,401 | 1,546 | **110** | 136,744,158.00 | 216,447,695.40 | **158.29** | 0 |
| 7 | ጅማ | 573 | 7787 | 8,360 | 8,360 | 1211 | 975 | 1211 | **124** | 138,265,144.90 | 151,263,918.59 | **109.40** | 0 |
| 8 | ድሬዳዋ | 28 | 3,761 | 3,789 | 3,764 | 484 | 920 | 484 | **53** | 227,000,000.01 | 394,266,828.50 | **173.69** | 25 |
| 9 | ሐዋሳ | 67 | 14,105 | 14,172 | 14,172 | 935 | 3,000 | 935 | **31** | 208,600,000.00 | 329,136,725.13 | **157.78** | 0 |
| 10 | ባሕር ዳር | 0 | 30,419 | 30,419 | 30,419 | 2,881 | 2,916 | 2,881 | **99** | 1,000,000,000.00 | 1,654,969,296.72 | **165.50** | 0 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 0 | 12,528 | 12,528 | 12,528 | 1,724 | 1,724 | 1,724 | **100** | 102,360,000.00 | 194,568,337.51 | **190.08** | 0 |
| **ድምር** | | **668** | **472941** | **473609** | **473534** | **96,131** | **82,019** | **96,131** | **117** | **25,873,512,823.49** | **31,099,457,390.43** | **120.20** | 75 |

### ➡ የስሌት ዉሳኔዎች ዝርዝር ምልከታ

ዘግይተው በቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ላይ (Late Filing Assessment) ብር 8,454,211,825.05 የተወሰነ ውሳኔ መኖሩ ያላስታወቁ ታክስ ከፋዮች ወቅታዊ ክትትል ወሳኝ መሆኑን እና ብር 11,902,446,730.66 በማሳወቂያ ጊዜ ኢ-ፋይል አድርገው ክፍያ ያልከፈሉት ላይ በተሰራ ስሌት (E-filed but not Paid) የሚያሳይ በመሆኑ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ክፍያ ባለመፈጸም የታክሱ የመክፈያ ጊዜው እንዲዘገይ የሚያደርጉ በመሆኑ በተከታታይ በዚህ አግባብ የሚፈጽሙትን ለይቶ መከታተልና ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ ብር 10,303,982,181.56 ሌሎች በዴስክ ኦዲት የተሰራ የታክስ ስሌት (Other Desk Tax Assessment) መኖሩ ማህደራቱን በየጊዜው በመፈተሸ ሊጣራ እንደሚገባ የሚያመላክት ነዉ፡፡

**ሰንጠረዥ 29 ዘግይተው በቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ላይ የተሰራ ስሌት እና የተወሰነ ገቢ**

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | ዕቅድ ጠቅላላ ታክስ | የተወሰነ የታክስ ውሳኔ ገንዘብ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክንውን | | | | |
| | | | ፍሬ ታክስ | ወለድ | መቀጫ | ድምር | በመቶኛ |
| 1 | ከፍተኛ | 256,879,701.00 | 473,043,463.60 | 19,335,135.28 | 35,330,366.17 | 527,708,965.05 | 205.43 |
| 2 | ምሥራቅ | 2,554,460,875.87 | 1,581,947,076.23 | 279,273,486.36 | 49,860,104.26 | 1,911,080,666.92 | 74.81 |
| 3 | ምዕራብ | 836,333,333.33 | 1,088,101,019.61 | 181,461,511.85 | 110,724,304.52 | 1,380,286,835.98 | 185.49 |
| 4 | መካከለኛ | 1,539,570,670.00 | 1,643,470,485.82 | 253,428,888.61 | 202,639,885.68 | 2,099,539,260.11 | 136.37 |
| 5 | ሰሜን/ም | 927,985,244.40 | 807,305,500.59 | 40,996,205.21 | 206,846,577.05 | 1,055,148,282.85 | 107.81 |
| 6 | አዳማ | 44,667,305.49 | 41,534,697.28 | 6,790,282.00 | 22,377,385.45 | 70,702,364.73 | 158.29 |
| 7 | ጅማ | 125,338,537.67 | 74,018,087.35 | 2,618,983.49 | 23,371,915.07 | 100,008,985.91 | 79.79 |
| 8 | ድሬዳዋ | 75,666,666.64 | 38,512,422.86 | 33,249,661.08 | 44,647,708.03 | 116,409,791.97 | 153.85 |
| 9 | ሐዋሳ | 99,360,000.00 | 110,653,861.08 | 8,322,008.73 | 47,914,663.59 | 166,890,533.40 | 167.97 |
| 10 | ባሕር ዳር | 600,000,000.00 | 842,010,688.17 | 15,166,897.48 | 108,692,646.92 | 965,870,232.57 | 160.98 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 65,395,000.00 | 34,036,682.01 | 3,981,179.73 | 22,548,043.82 | 60,565,905.56 | 92.62 |
| **ድምር** | | **7,125,657,334.41** | **6,734,633,984.60** | **844,624,239.82** | **874,953,600.56** | **8,454,211,825.05** | **118.64** |

**ሰንጠረዥ 30 በማሳወቂያ ጊዜ ኢ-ፋይል አድርገው ክፍያ ያልከፈሉት ላይ የተሰራ ስሌት**

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | የተወሰነ የታክስ ውሳኔ በገንዘብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ ጠቅላላ ታክስ | ክንውን | | | | |
| | | ጠቅላላ ታክስ | ፍሬ ታክስ | ወለድ | መቀጫ | ድምር | በመቶኛ |
| 1 | ከፍተኛ | 5,321,560,149.50 | 5,146,350,860.88 | 323,999,358.71 | 540,734,106.57 | 6,011,084,326.15 | 112.96 |
| 2 | ምሥራቅ | 661,988,299.23 | 751,179,441.10 | 122,513,157.69 | 38,307,955.56 | 912,000,554.28 | 137.77 |
| 3 | ምዕራብ | 126,333,333.33 | 205,751,367.98 | 55,899,258.72 | 27,629,905.47 | 289,280,532.17 | 228.98 |
| 4 | መካከለኛ | 3,747,588,850.00 | 3,017,133,107.01 | 226,745,842.14 | 265,050,605.18 | 3,508,929,554.34 | 93.63 |
| 5 | ሰሜን/ም | 197,188,255.60 | 153,295,016.56 | 8,790,907.97 | 62,073,981.20 | 224,159,905.73 | 113.68 |
| 6 | አዳማ | 73,570,315.36 | 78,041,698.07 | 1,971,718.59 | 36,438,543.28 | 116,451,959.94 | 158.29 |
| 7 | ጅማ | 3,056,058.28 | 17,250,652.66 | 247,561.55 | 2,047,618.39 | 19,545,832.60 | 639.58 |
| 8 | ድሬዳዋ | 75,666,666.65 | 68,559,740.70 | 1,452,153.08 | 6,567,743.56 | 76,579,637.34 | 101.21 |
| 9 | ሐዋሳ | 99,360,000.00 | 76,256,658.48 | 1,069,596.95 | 15,139,949.16 | 92,466,204.59 | 93.06 |
| 10 | ባሕር ዳር | 250,000,000.00 | 574,782,937.02 | 5,502,778.71 | 38,818,982.08 | 619,104,697.81 | 247.64 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 21,885,000.00 | 30,386,092.42 | 942,346.94 | 1,515,086.35 | 32,843,525.71 | 150.07 |
| **ድምር** | | **10,578,196,927.96** | **10,118,987,572.88** | **749,134,681.05** | **1,034,324,476.80** | **11,902,446,730.66** | **112.52** |

ሰንጠረዥ 31 ሌሎች በዴስክ የተሰራ የታክስ ስሌት

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | የተወሰነ የታክስ ውሳኔ በገንዘብ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክንውን | | | | |
| | | ዕቅድ ጠቅላላ ታክስ | ፍሬ ታክስ | ወለድ | መቀጫ | ድምር | በመቶኛ |
| 1 | ከፍተኛ | 5,321,560,149.50 | 4,020,954,338.22 | 617,594,348.29 | 1,419,694,655.11 | 6,058,243,341.63 | 113.84 |
| 2 | ምሥራቅ | 719,903,861.52 | 943,984,349.18 | 254,659,880.46 | 59,136,293.41 | 1,257,780,523.13 | 174.72 |
| 3 | ምዕራብ | 142,333,333.33 | 161,929,111.87 | 47,108,718.11 | 31,428,321.38 | 240,466,151.36 | 113.35 |
| 4 | መካከለኛ | 1,190,864,170.00 | 1,120,916,534.56 | 432,725,311.26 | 454,433,248.06 | 2,008,075,093.88 | 168.62 |
| 5 | ሰሜን/ም | 183,826,500.00 | 165,223,260.64 | 21,380,548.68 | 49,600,390.87 | 236,204,200.19 | 128.49 |
| 6 | አዳማ | 18,506,537.14 | 14,989,750.87 | 9,959,454.57 | 4,344,165.28 | 29,293,370.72 | 158.29 |
| 7 | ጅማ | 9,870,548.95 | 22,830,148.93 | 3,196,212.58 | 5,682,738.57 | 31,709,100.08 | 321.25 |
| 8 | ድሬዳዋ | 75,666,666.72 | 79,623,163.31 | 56,236,202.91 | 65,418,033.01 | 201,277,399.23 | 266.01 |
| 9 | ሐዋሳ | 9,880,000.00 | 42,771,790.20 | 10,644,542.46 | 16,363,396.10 | 69,779,728.76 | 706.27 |
| 10 | ባሕር ዳር | 150,000,000.00 | 37,701,233.36 | 6,812,780.48 | 25,480,352.50 | 69,994,366.34 | 46.66 |
| 11 | ኮምቦልቻ | 15,080,000.00 | 44,001,907.71 | 18,988,218.51 | 38,168,780.02 | 101,158,906.24 | 670.82 |
| ድምር | | **7,837,491,767.16** | **6,654,925,588.84** | **1,479,306,218.31** | **2,169,750,374.31** | **10,303,982,181.56** | **179.44** |

የታክስ ኦዲት ስራ ዋና ዓላማው የታክስ ከፋዮችን የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማረጋገጥ ኦዲት የሚያደርግ በመሆኑ የተሻለ ገቢ ከመሰብሰብ አኳያ የታክስ ስሌት ስራ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። በበጀት ዓመቱም ከታክስ ዕዳ አሰባሰብ አንጻር የተሸለ ድርሻ የነበረው መሆኑን ማየት ተችሏል። ስለሆነም በቀጣይ በጀት ዓመት ዘርፎችን በመለየት እና የታክስ ስሌት ስራ ጥራት ላይ ትኩረት በማድረግ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት ከወዲሁ ጥረት ማድረግ ይጠይቃል። እንደ ተቋም ታክስ ከፋዮች ኦዲት የሚደረጉበት ጊዜ እያጠረ በመጣ ቁጥር ከላይ ከተገለጸው የኦዲት ዓላማ በተጨማሪ ተጨማሪ ገቢ የማግኘት ዕድሉ ዝቅተኛ በመሆኑ ገቢ የመሰብሰብ ከፍተኛው ኃላፊነት ታክስ ስሌት ላይ ስለሚያርፍ በዚያው ልክ መዘጋጀትና ወደ ስራ መግባት ያስፈልጋል፡

ሰንጠረዥ 32 መረጃ ወደ ሲስተም መመዝገብ (Data capturing) እና የመረጃ ጥራት ቁጥጥር

| ተ.ቁ | ቅርንጫፍ | በበጀት ዓመቱ ያስታወቁ ግ/ከፋዮች | | | ወደ ሲስተም ሳይገባ የዞረ | አጠቃላይ ወደ ሲስተም መግባት ያለበት ድምር | ወደ ሲስተም የገቡ ብዛት | ቀሪ ወደ ሲስተም ያልገቡ | የጥራት ቁጥጥር መደረግ ያለባቸዉ ማስታወቂያዎች ብዛት | | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ኢ-ታክስ | ማንዋል | ድምር | | | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| 1 | ከፍተኛ | 33,171 | 1,411 | 34,582 | 0 | 1,411 | 1,411 | 0 | | | |
| 2 | ምሥራቅ | 163,699 | 2,392 | 166,091 | 0 | 2,392 | 2,392 | 0 | 2,395 | 2,395 | **100** |
| 3 | ምዕራብ | 163,632 | 9,356 | 172,988 | 0 | 9,356 | 9,356 | 0 | 9,800 | 8,597 | **88** |
| 4 | መካከለኛ | 127,631 | 2,635 | 130,266 | 0 | 2,635 | 2,504 | 131 | 2,521 | 2,459 | **98** |
| 5 | ሰሜን ምዕራብ | 115,619 | 4,579 | 120,198 | 0 | 4,579 | 4,579 | 0 | 117,792 | 117,792 | **100** |
| 6 | አዳማ | 8,455 | 2,916 | 11,371 | 104 | 3,020 | 2,976 | 44 | 11,675 | 11,675 | **100** |
| 7 | ጅማ | 4,124 | 4,057 | 8,181 | 0 | 4,057 | 3,612 | 445 | 5,346 | 5,692 | **106** |
| 8 | ድሬዳዋ | 3,751 | 901 | 4,652 | 0 | 901 | 901 | 0 | 1,175 | 2,060 | **175** |
| 9 | ሐዋሳ | 11,623 | 3,227 | 14,850 | 89 | 3,316 | 3,316 | 0 | 14,939 | 14,896 | **100** |
| 10 | ባሕር ዳር | 14,007 | 14,706 | 28,713 | 0 | 14,706 | 14,706 | 0 | 2,832 | 2,832 | **100** |
| 11 | ኮምቦልቻ | 3,839 | 5,030 | 8,869 | | 5,030 | 5,030 | 0 | 4,025 | 4,025 | **100** |
| ድምር | | **649,551** | **51,210** | **700,761** | **193** | **51,403** | **50,783** | **620** | **172,500** | **172,423** | **100** |

### ➲ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮችን ክትትል አፈጻጸም

#### የንግድ ትርፍ ግብር ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል ስራዎች አፈጻጸም

በ12 ወሩ 11,095 ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ክትትል በማድረግ ግብራቸውን እንዲያሳውቁ ለማድረግ በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 8,983 ግብር ከፋዮች (6,010 ያስታወቁ፣ 2,586 ክትትሉ የተቋረጠ እና 387 በግምት የተወሰነ) በመሆኑ 80.96 በመቶ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ በ12 ወሩ የግምት ታክስ ስሌት ለመስራት በዕቅድ ከተያዘው 465 ግብር ከፋዮች ውስጥ ለ 387 ግብር ከፋዮች ስሌት የተሰራ ሲሆን ይህም 84.30 በመቶ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ በብር 478.73 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 288.64 ሚሊዮን የተወሰነ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 60.29 በመቶ ነው፡፡ ከአለፈው ዓመት የዞረውን ጨምሮ ሳይከናወን ወደ ቀጣይ ወር የተሸጋገር ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2,112 ነው፡፡

#### የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል አፈጻጸም

በ12 ወሩ 16,052 ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ክትትል በማድረግ ግብራቸውን እንዲያሳውቁ ለማድረግ በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 13,630 ግብር ከፋዮች (11054 ያሳወቁ፣ 2349 ክትትላቸው የተቋረጠ እና 227 በግምት የተወሰነ) ሲሆን 84.91 በመቶ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ በ12 ወሩ የግምት ታክስ ስሌት ለመስራት በዕቅድ ከተያዘው 295 ግብር ከፋዮች ውስጥ ለ227 ግብር ከፋዮች ስሌት የተሰራ ሲሆን ይህም 73.56 በመቶ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ በብር 494.69 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 369.78 ሚሊዮን የተወሰነ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 71.92 በመቶ ነው፡፡ ከአለፈው ዓመት የዞረውን ጨምሮ ሳይከናወን ወደ ቀጣይ ወር የተሸጋገር ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2,422 ነው፡፡

#### የተርን ኦቨር ታክስ ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል አፈጻጸም

በ12 ወሩ 10,621 ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ክትትል በማድረግ ግብራቸውን እንዲያሳውቁ ለማድረግ በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 9,192 ግብር ከፋዮች (8076 ያሳወቁ፣ 1092 በክትትል የተቋረጠ እና 24 በግምት የተወሰነ) ሲሆን 86.55 በመቶ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ ከአለፈው ዓመት የዞረውን ጨምሮ ሳይከናወን ወደ ቀጣይ ወር የተሸጋገር ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1,429 ነው፡፡

#### የኤክሳይዝ ታክስ ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል አፈጻጸም

በ12 ወሩ 507 ያላስታወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ክትትል በማድረግ ግብራቸውን እንዲያሳውቁ ለማድረግ በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ 468 ግብር ከፋዮች (374 ያሳወቁ፣ 93 በክትትል የተቋረጠ እና 1 በግምት የተወሰነ) ሲሆን ይህም 92.31 በመቶ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ ከአለፈው ዓመት የዞረውን ጨምሮ ሳይከናወን ወደ ቀጣይ ወር የተሸጋገር ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች ቁጥር 39 ነው፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ግብር ያላስታወቁትን ክትትል በማድረግ 32,273 ግብር ከፋዮች (25514 ያሳወቁ፣ 6120 ክትትሉ የተቋረጠ እና 639 በግምት የተወሰነ) በመሆኑ 38,275 ታቅዶ 84.32 በመቶ ተፈጽሟል፡፡

### 3.2.2 የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ስራዎችን ማጠናከር ስራዎች አፈጻጸም

#### የታክስ ከፋዮች ትምህርት ስራዎች አፈጻጸም

- የታክስና ጉምሩክ ክበብ እና የጥያቄና መልስ ውድድርን የአሰራር ስርዓት እንዲሁም የማስተማሪያ ማኑዋል ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በጋራ ተዘጋጅቶ በከፍተኛ አመራሩ ፀድቆ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከኮሚሽኑ ጋር በመቀናጀት 9 ክላስተሮችን በማደራጀት በ180 የመንግስትና የግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ለተማሪዎችና ለአብቂ መምህራን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት 3 ዙር የጥያቄና መልስ ውድድር በማከሄድ አሸናፊዎችን በመለየት በአገር አቀፍ ደረጃ የአሸናፊዎች አሸናፊ ውድድር ለማከሄድ ተችሏል፡፡
- የታክስ የርቀት ትምህርት እና በሶሻል ሚዲያ የአሰራር ሥርአት ሰነዶች በዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ተፈርመው ለአፈጻጸም ወደ ቅርንጫፎች የተላኩ ሲሆን የኢለርኒንግ የአሰራር ሥርዓት በሚቀጥለው ዓመት አጋማሽ ላይ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ይህም በታክስ ትምህርት ተደራሽነት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል አቅም ይፈጥራል፡፡
- በቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ላይ የተዘጋጁ ሁለት መጽሐፎችን በ20,000 ኮፒ በማሳተም እየተሰራጨ ይገኛል፡፡ የታክስ አስተዳደሩን መጽሀፍ ለማሳተም ዝግጅቱ ተጠናቋል፡፡
- በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ በታክስ ህጎች ላይ የተዘጋጀውን የሞጁላር ሥልጠና ለ90 ሰዓታት ያህል ተከታትለው ለአጠናቀቁ 1,441 ግብር ከፋዮች የምረቃ ስነ-ስርዓት በማካሄድ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በ2015 ዓ.ም በጀት አመት ለሁለተኛ ጊዜ በቀጥተኛ ታክስ፣ ቀጥተኛ ባልሆኑ ታክሶች እና በታክስ አስተዳደሩ ላይ በአጠቃላይ በ13ቱ ሞጁሎች ላይ 3635 ግብር ከፋዮች ለ90 ሰዓታት ያህል የተሠጠውን ስልጠና አጠናቀው ለምረቃ ተዘጋጅተዋል፡፡
- ለ12,932 ሰልጣኞች የሥጋት ሥራ አመራርን እና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአንድ ጊዜ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ13,237 ሰልጣኞች መስጠት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የእቅዱን 102 በመቶ ነው፡፡
- የተለያዩ ማብራሪያዎችን ፈልገው ለመጡ ግብር ከፋዮች በአካልና በስልክ ለ29,525 ያህል ግብር ከፋዮች ማብራሪያ ለመስጠት ተችሏል አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡
- በኢሜይል፣ በፌስቡክ፣ በቴሌግራም እንዲሁም በዩቱዩብ የግብር ከፋዮችን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ መልዕክቶችን የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሠረት የቴሌግራም ግሩፕ አባል 30,888 ፣ፌስቡክ ተከታይ 12,011 እና ዩቱዩብ ሰብስክራይብ ያደረጉ 6,611 ሆነዋል፡፡
- 129 የታክስ ህግና ስነ-ስርዓትን ለማሰልጠን የተዘጋጁ ቪድዮችንና ኦዲዮዎችን በዩቱዩብ ላይ ለመጫን ታቅዶ 170 ቪዲዮዎችን ማለትም የዕቅዱን 131.8 በመቶ ለማናወን ተችሏል፡፡

- በ25 መድረኮች በታክስ ጉዳዮች ላይ ለታክስ ከፋዮች እያዋዙ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ በ19 መድረኮች ላይ ማካሄድ ተችሏል። አፈፃፀሙም የእቅዱን 76 በመቶ ነው። አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት ወጪ ቆጣቢ የበጀት አጠቃቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።
- በ560 የቲቪ እና የራዲዮ ፕሮግራሞች የታክስ ትምህርትን በአማርኛ፣ በኦሮምኛ እና በሶማሊኛ ቋንቋዎች ለማስተላለፍ ታቅዶ 474 ፕሮግራሞችን ማለትም የእቅዱን 84.6 በመቶ ለማስተላለፍ ተችሏል።
- በተደጋጋሚ ግብር ከፋዩ ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች በመነሳት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ 110 ብሮሸሮችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 104 ብሮሸር ለማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም የእቅዱን 94.5 በመቶ ነው።
- በ2015 ዓ.ም በጀት አመት ለሁለት ጊዜ በአዲስ አበባ ውስጥ በመዘዋወር ኤል.ኢ.ዲ ስክሪን ባለው ተሽከርካሪ የታገዘ ቅስቀሳ ተደርጓል። እንዲሁም መስቀል አደባባይ ባሉ አምስት ግዙፍ ኤል.ኢ.ዲ ስክሪኖች ለግብር ከፋዩ የቅስቀሳና ለህብረተሰቡ በታክስ ዙሪያ የድምጽ፣ የምስል፣ እንዲሁም የጽሁፍ መልዕክቶች ተላልፈዋል።

### ➲ የታክስ ስጋት ስራ አመራር ስራዎች አፈጻጸም

የስጋት መምረጫ መስፈርቶች ላይ ማሻሻያ ከማድረግ አንጻር የሰነዶቹን የመጨረሻ ረቂቅ በማዘጋጀት በስጋት ሻምፒዮን ኮሚቴው ውሣኔ የሚቀርቡ ነጥቦች ተለይተው ውይይት እንዲደረግባቸው ተደርጐ ሰነዱን በማጽደቅ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ተላልፎአል። አዲሱን የመካከለኛ ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤትን ጨምሮ በተሰራው የግብር ከፋዮች የሰግመንቴሽን መረጃ መሰረት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በ2016 በጀት ዓመት ስጋት ሊጣልባቸው የሚችሉ እና በተለያዩ ምክንያት ስጋት የማይጣልባቸውን ግብር ከፋዮች በመለየት ስጋት ተጥሏል ።

ሰንጠረዥ 33 አጠቃላይ የግብር ከፋዮች ብዛት ለስጋት ዝግጁ የሆኑና ያልሆኑ እንዲሁም የስጋት ደረጃቸው

| ተ.ቁ | የቅርንጫፍ | የቅ/ጽ/ቤቱ አጠቃላይ የግብር ከፋዮች ብዛት | በ2016 የስጋት ደረጃ የወጣላቸው/የተለዩ ግ/ከ ብዛት | በ2016 የስጋት ደረጃ የወጣላቸው/የተለዩ ግ/ከ ብዛት በመቶኛ | በተለያየ ምክንያት ስጋት የማይጣልባቸው ግብር ከፋዮች | ስጋት ያልተጣለባቸው ግብር ከፋዮች በመቶኛ | ከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ላይ ያረፉ ግ/ከ ብዛት | መካከለኛ የስጋት ደረጃ ላይ ያረፉ ግ/ከ ብዛት | ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ ያረፉ ግ/ከ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 742 | 742 | 10 | 0 | 0 | 185 | 371 | 186 |
| 2 | ምስራቅ | 12617 | 6743 | 53.44 | 5874 | 46.56 | 1685 | 3372 | 1686 |
| 3 | ምዕራብ | 9921 | 4798 | 48.40 | 5123 | 51.60 | 1199 | 2399 | 1200 |
| 4 | መካከለኛ ቁጥር 1 | 4174 | 3897 | 93.40 | 277 | 6.60 | 974 | 1948 | 975 |
| 5 | መካከለኛ ቁጥር 2 | 4077 | 3989 | 98 | 88 | 2 | 997 | 1994 | 998 |
| 6 | ሰ/ምዕራብ | 9161 | 4238 | 46.30 | 4923 | 53.70 | 1059 | 2119 | 1060 |
| 7 | አዳማ | 1129 | 896 | 79.40 | 233 | 20.60 | 224 | 448 | 224 |
| 8 | ባህርዳር | 4001 | 2094 | 52.33 | 1907 | 47.67 | 523 | 1047 | 524 |
| 9 | ድሬዳዋ | 709 | 333 | 47 | 376 | 53 | 83 | 166 | 84 |

| ተ.ቁ | የቅርንጫፍ | የቅ/ጽ/ቤቱ አጠቃላይ የግብር ከፋዮች ብዛት | በ2016 የስጋት ደረጃ የወጣላቸው/የተለዩ ግ/ከ ብዛት | በ2016 የስጋት ደረጃ የወጣላቸው/የተለዩ ግ/ከ ብዛት በመቶኛ | በተለያየ ምክንያት ስጋት የማይጣልባቸው ግብር ከፋዮች | ስጋት ያልተጣልባቸው ግብር ከፋዮች በመቶኛ | ከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ላይ ያረፉ ግ/ከ ብዛት | መካከለኛ የስጋት ደረጃ ላይ ያረፉ ግ/ከ ብዛት | ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ ያረፉ ግ/ከ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ሀዋሳ | 2002 | 1264 | 63 | 738 | 37 | 316 | 629 | 319 |
| 11 | ከምቦልቻ | 1284 | 657 | 51 | 627 | 49 | 164 | 328 | 165 |
| 12 | ጅማ | 1433 | 927 | 65 | 506 | 35 | 231 | 464 | 232 |
| **ድምር** | | **51,250** | **30,578** | **59.70** | **20,672** | **40.30** | **7,640** | **15,285** | **7,653** |

- በ2014 ዓ.ም የህግ ተገዥ ለሆኑ ግብር ከፋዮች ለሚሰጥ ዕውቅናና ሽልማት ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲልኩ በማድረግ ለዕውቅናና ሽልማት ዝግጁ የሆኑ 1151 ግብር ከፋዮች መረጃ በማደራጀት ትንተና ተሰርቶ በመጨረሻም ሽልማቱ እንድሠጥ ተደርጓል

- ይሄም ጥቅምት 10/2015 ዓም የኢፌዴሪ ፕሪዘዳንት ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ዴኤታዎችና የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነሮች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት 400 ግብር ከፋዮች እና ለ14 ላለፉት 3 እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በፕላቲኒየም ደረጃ የተሻለሙ ግብር ከፋዮችን እውቅናና ሽልማት በመስጠት እንዲበረታቱና በህግ ተገዥነታቸው እንዲቀጥሉ እንዲሁም ሌሎችም ይህንን በማየት ወደ ተሻለ የታክስ ህግ ተገዥነት ሁኔታ እንዲመጡ የማድረግ ስራ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡

- በአጠቃላይ 400 ግብር ከፋዮች ተለይተው 40ው የፕላቲኒየም ፣ 120ው የወርቅ እና 240ው የብር ተሸላሚ እንዲሆኑና እውቅና እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ 14 ግብር ከፋዮች 3 ዓመትና ከዚያ በላይ የፕላቲኒየም ደረጃ ተሸላሚ በመሆናቸው እና 1 ድርጅት በበጀት ዓመቱ የተቋሙ ፈተና ከሆነው አንዱ ሙስናን በማጋለጥና ተጨባጭ ውሳኔ እንዲሰጥ በማስቻላቸው የልዩ ሽልማት ተሸላሚ እንዲሆኑ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም 37 በበጀት አመቱ ለግብርና ታክስ አሰባሰቡ የበኩላቸውን አገዛ ያደረጉ አጋር አካላት እውቅና እንዲሰጣቸው ተደርጓል

2015 በጀት ዓመት በሁሉም የአገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የታክስ ኦዲት በሥጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት መፈጸሙን፤ ከመተንተን አንጻር፦ ለ2015 ዓ.ም በሥጋት የተመረጡ ማህደራትን ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችል እያንዳንዱን የሥጋት ዓይነት የሚያሳይ መረጃ/Risk Information/ በማዘጋጀት በታክስ ኦዲት እንዲታዩ ለሁሉም የአገር ውስጥ ታክስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (11 ቅ/ጽ/ቤቶች) በsoft copy ተላልፏል፡፡ ለ2016 በጀት ዓመት የሚውሉ የስጋት መረጃዎች እንዲሁ ተላልፎአል፡፡ በአዲሱ የማህደር ስርጭት የአሰራር ስርዓት መሰረት በቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት የሚደረጉ ማህደራት ለኦዲት እንዲተላለፍ እና ሒደቱን ክትትል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

በ11 ቅ/ጽ/ቤቶች በዘፈቀደ መረጣ /Random selection/ ተመርጠው ለኦዲት የተላለፉ ማኅደራትን ውጤታማነት በመገምገም ሠነድ ከማዘጋጀት አንጻር፦ በ2015 በጀት ዓመት ከሐምሌ እስከ ግንቦት ወራት በዘፈቀደ ከተመረጡ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች 330 ማኅደራት ኦዲት የተደረገ ሲሆን በፍሬ ግብር ብር 690,325,244.86 ውሳኔ የወጣ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት ተደራጅቶ ተላልፏል፡፡ በአጠቃላይ እስከ ግንቦት

ወር በዘፈቀደ ተመርጠው ኦዲት የተደረጉ ማኅደራት ዝርዝር መረጃ ከቅ/ጽ/ቤቶች በመውሰድ መረጃ የተደራጀ ሲሆን በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች 330 ማኅደራት ኦዲት ተደርገዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ 272 ማኅደራት ወይም 82.42 በመቶ ግኝት የተገኘባቸው ሲሆን ቀሪዎቹ 58 ማኅደራት ወይም 17.58 በመቶ ግኝት እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፤

በ2015 በጀት ዓመት በቅ/ጽ/ቤቶች በዳታ ማቺንግ 1064 ማህደራት ለታክስ ኦዲት ፣ በታክስ ስሌት እና ለተመላሽና አገልግሎት ኦዲት ለማስተላፍ በዕቅድ ተይዞ 1,309 ወይም 123 በመቶ ማህደራት የተላለፉ ሲሆን ከተላለፉት 1,309 ድርጅቶች ውስጥ 910 ወይም 70 በመቶ ብቻ በታክስ ኦዲት ፣ በታክስ ስሌት እና በተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የተመረመሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 765 ወይም 84 በመቶ ግኝት የተገኘባቸው እና 145ቱ ወይም 16 በመቶ ግኝት የሌላቸው መሆኑ ሪፖርቱ ያሳያል።

## የታክስ ኦዲት ስራዎች አፈጻጸም

- በ2015 በጀት ዓመት 7,986 ታክስ ከፋዮችን ኦዲት በማድረግ የህግ ተገዥነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 8,017 ታክስ ከፋዮችን ኦዲት በማድረግ ውሳኔ በማሳረፍ ቀጣይ ትምህርት እንዲወሰድ ማድረግ ተችሏል።
- ኦዲት ከተደረጉት ታክስ ከፋዮች በሂሳብ መዝገባቸው የያዙትን ተገቢነት የሌለውን ኪሳራ በማስቀረት ረገድ በተሠራው ሥራ 1,921 ታክስ ከፋዮች በሂሳብ መዝገባቸው የያዙትን ያልተገባ ኪሳራ ብር 12.29 ቢሊዮን በማስቀረት ለገቢ አሰባሰቡ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል።
- ኦዲት ከተደረጉ ታክስ ከፋዮች ውስጥ በሂሳብ መግለጫዎቻቸው የያዙትን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ ግብር (ቅድመ ግብር) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ብር 1.32 ቢሊዮን ለማስቀረት ታቅዶ የነበረ ሲሆን 908 (እንደየቅደም ተከተላቸው 345 እና 563) ታክስ ከፋዮች በሂሳብ መዝገባቸው በታክስ ተመላሽነት የያዙትን ብር 1.926 ቢሊዮን (969.1 ሚሊዮን እና 956.54 ሚሊዮን) ለመከላከል/ለማስቀረት ተችሏል።
- ሃሰተኛ ግብይትን (የደረሰኝን) ከመከላከል/ከማስቀረት አኳያ 220 ታክስ ከፋዮች በሂሳብ መዝገባቸው በሀሰተኛ ደረሰኝ የያዙትን ብር 422.89 ሚሊዮን ውድቅ በማድረግ የታክስ ውሳኔ ተሰጥቷል።
- ታክስ ከፋዮች በፍላጎት አሳውቀው በወቅቱ በመክፈል ያላሳወቁትን ፈልፍሎ በማውጣት ቀሪ ፍሬ ግብር ብር 19.37 ቢሊዮን፣ ወለድ 8.18 ቢሊዮን እና መቀጫ 13.17 ቢሊዮን፤ በድምሩ ብር 40.73 ቢሊዮን በመወሰን የህግ ተገዥነትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ስራዎች ተሰርተዋል።

ሰንጠረዥ 34 የኦዲት አፈጻጸም በማህደር

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | የ2015 በጀት ዓመቱ ዕቅድ | የ2015 በጀት ዓመት ክንውን | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከፍተኛ | 252 | 260 | 103.17 |
| 2 | መካከለኛ | 665 | 700 | 105.26 |
| 3 | ምዕራብ | 1639 | 1712 | 104.45 |
| 4 | ምስራቅ | 1639 | 1634 | 99.69 |
| 5 | ሰሜን-ምዕራብ | 1629 | 1547 | 94.97 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | ሐዋሳ | **375** | **418** | **111.47** |
| 7 | አዳማ | **530** | **519** | **97.92** |
| 8 | ባህርዳር | **464** | **436** | **93.97** |
| 9 | ኮምቦልቻ | **253** | **259** | **102.37** |
| 10 | ጅማ | **268** | **275** | **102.61** |
| 11 | ድሬዳዋ | **272** | **257** | **94.49** |
| | **ድምር** | **7986** | **8017** | **100.38** |

**ሰንጠረዥ 35 የኦዲት አፈጻጸም በገንዘብ(በፍሬግብር)**

| ተ.ቁ. | ቅ/ጽ/ቤት | ዕቅድ | የ12 ወራት የገቢ ክንውን | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፍሬ ግብር | አፈጻጸም በፍሬ ግብር | ወለድ | መቀጫ | የፍሬ ግብር ፣ ወለድና መቀጫ ድምር |
| 1 | ከፍተኛ | 12,931,711,094.52 | 11,692,741,786.58 | 90.42 | 5,106,585,121.86 | 8,056,674,353.91 | 24,856,001,352.77 |
| 2 | መካከለኛ | 4,110,977,160.88 | 2,491,586,971.94 | 60.61 | 1,181,545,200.04 | 1,969,668,123.83 | 5,642,800,356.42 |
| 3 | ምዕራብ | 687,949,640.29 | 1,121,053,526.12 | 162.96 | 429,536,997.66 | 682,928,764.97 | 2,233,519,451.71 |
| 4 | ምስራቅ | 1,315,726,780.50 | 1,772,063,093.85 | 134.68 | 698,745,447.67 | 1,099,495,441.55 | 3,570,304,117.76 |
| 5 | ሰሜን/ም | 900,405,268.80 | 999,146,032.53 | 110.97 | 288,862,828.79 | 468,749,156.81 | 1,756,758,129.11 |
| 6 | ሐዋሳ | 269,436,002.14 | 379,705,281.65 | 140.93 | 136,215,248.92 | 253,177,744.17 | 769,098,415.66 |
| 7 | አዳማ | 236,657,720.56 | 225,561,947.22 | 95.31 | 70,749,930.02 | 141,760,487.41 | 438,072,459.96 |
| 8 | ባህርዳር | 222,743,044.94 | 335,396,602.78 | 150.58 | 129,335,938.18 | 252,017,491.44 | 716,750,182.97 |
| 9 | ኮምቦልቻ | 78,165,011.07 | 74,960,374.17 | 95.9 | 25,283,434.41 | 72,849,271.68 | 173,093,176.16 |
| 10 | ጅማ | 93,528,953.00 | 122,150,721.29 | 130.6 | 48,394,279.91 | 85,543,030.75 | 256,088,162.55 |
| 11 | ድሬዳዋ | 152,699,323.30 | 160,551,408.74 | 105.14 | 67,503,036.96 | 96,744,851.61 | 324,799,402.45 |
| ድምር | | **21,000,000,000.00** | **19,374,917,746.86** | **92.26** | **8,182,757,464.42** | **13,179,608,718.15** | **40,737,284,021.69** |

## ሰንጠረዥ 36 የኦዲት ውጤት በኦዲት ዓይነት፣ የቀነሰ ኪሳራ እና የቀነሰ ተመላሽ

| የኦዲት ዓይነት | የ2015 በጀት ዓመት ክንውን | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ፍሬ ግብር | ወለድ | መቀጫ | የፍሬ ግብር ፣ ወለድና መቀጫ ድምር |
| አጠቃላይ ኦዲት | 18,701,953,668.26 | 7,912,643,172.70 | 12,699,216,004.79 | 39,313,812,845.75 |
| ውስን ኦዲት | 440,454,520.08 | 186,619,385.16 | 307,512,172.39 | 934,586,077.63 |
